# ሐመር

## የአድዋ ድል ቤተ ክርስቲያን በገነባችው የሥነ ልቡና ልዕልና የተገኘ ነው።






በውስጥ ገጾች


- ✞ ለተጎዱት ሰላምታንና ምግብን እንስጥ
- ✞ “በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ”
- ✞ ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው?
- ✞ የአድዋ ድል ቤተ ክርስቲያን በገነባችው የሥነ ልቡና ልዕልና የተገኘ ነው።
- ✞ ዐቃብያነ እምነት/ቀዋምያን
- ✞ ለቤተ ክርስቲያንከወንድሞቻችሁ ጋር በፍቅር ኑሩ
- ✞ የወደቀው መልአክ


የካቲት ፳፻፲፫ ዓ.ም.

# ሐመር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

## የካቲት ፳፻፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመትና
ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋና ክፍል
በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት



## ማውጫ


የማኅበሩ መልእክት
ለተጎዱት ሰላምታንና ምግብን እንስጥ
፫

ዐውደ ስብከት
"በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ"
፭

ትምህርተ ሃይማኖት
ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው?
፱

ዐቢይ ጉዳይ
የአድዋ ድል ቤተ ክርስቲያን በገነባችው የሥነ ልቡና ልዕልና የተገኘ ነው።
፲፩

ዐቢይ ጉዳይ
ዐቃብያነ እምነት/ቀዋምያን ለቤተ ክርስቲያን
፲፱

የጥያቄዎቻችሁ መልስ
፳፫

እናስተዋውቃችሁ
የጮቢ መካነ ሕይወት በዓታ ለማርያም የአንድነት ገዳም
፳፱

ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት
ከወንድሞቻችሁ ጋር በፍቅር ኑሩ
፴

ኪነ ጥበብ
የወደቀው መልአክ
፴፩

ከዓለም ማዕዘናት
ዐቢይ ጾም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት
፵


"ማኅበረ ቅዱሳን" እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና
አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይኽን ስያሜ
አግኝቷል።


## የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ ፲፩፩-፰-፩፪-፪፰-፬፱
ፖ.ሣ.ቁ ፰፲፲፮፰
ኢ-ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት ስልክ
፲፩፩-፩-፭፭-፫፪-፫፱
የልማት ተቋም የስርጭት ክፍል ስልክ
፲፩፩-፩-፪፫፬፭-፪፱
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
፲፱፬፪-፫፰-፩፮-፱፩

### ም/ዋና አዘጋጆች
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አድራሻ፡- ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ
ወረዳ ፲፭ የቤት ቁ. ፮፪፲

### ምክትል ዋና አዘጋጅ
ዲ/ን ኀሊና በለጠ

### ከፍተኛ ሪፖርተር
ዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

### ሌይ አውት ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

### ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ለተጎዱት ሰላምታንና ምግብን እንስጥ

## የማኅበሩ መልእክት

ነቢዩ ሳሙኤል የዘይቱን ብርሌ ወስዶ በሳኦል ራስ ላይ ካፈሰሰ በኋላ ከፊቱ ስለሚገጥመው ነገር እየገለጸ መክሮት ነበር፡፡ ከእርሱ ተለይቶ ወደ ፊት በመሄድ ወደ ታቦር ወደ ትልቁ ዛፍ በደረሰ ጊዜ ሦስት ሰዎችን እንደሚያገኝ ነገረው፡፡ እነርሱም ‹‹ሰላምታም ይሰጡሃል ሁለትም ዳቦ ይሰጡሃል›› አለው፡፡ (፩ ሳሙ. ፲፥፴)፡፡ መንገድን ለጀመረ ተጓዥ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል ሰላምና ስንቅ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በመንገድ ሰላም ከሌለ መንገደኛ ሊጓዝ አይችልም፤ ስንቅ ካልያዘም እንዲሁ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ለተጓዥ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ተረጋግቶ ይኖር ዘንድ የሀገር ሰላምና በልቶ የማደር ጉዳይ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡

እነዚህ ሁለት ነገሮች ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ እንደሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በጸሎቷ የምታስታውሳቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ የምእመናቿ ሰላምና በልቶ የማደር ጉዳይ ዘወትር ቤተ ክርስቲያንን ያስጨንቃታል፡፡ የምእመናቿ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ ብሎም የዓለም ሰላምና የዕለት ምግብም ያሳስባታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሁሉም እንደ መሆኗም ስለ ሀገርና ስለ ዓለም ሰላም ትጸልያለች፡፡ መጋቢ እግዚአብሔር ነውና በመግቦቱ ያስበን ዘንድ ‹‹የዕለት እንጀራችንን ስጠን›› ብለን ወደ እርሱ እንድናንጋጥጥም ታስተምራለች፡፡

ጥቂት ለማይባሉ ላለፉት ዓመታት ሀገራችን ኢትዮጵያ በሰላም እጦት ተቸግራለች፡፡ በአንዱ በኩል የነደደው እሳት ጠፋልኝ ስትል በሌላ በኩል ይነሣል፡፡ ንብረቶች ወድመዋል፤ ዜጎች ለብዙ እንግልትና ሞት ተዳርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን፣ አድባራትና ገዳማት ደግሞ በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ገፈት ቀማሾችና ዋነኛ ዒላማዎች ሆነው ቆይተዋል፡፡ አሁንም የተሰደዱና ያልተቋቋሙ ዜጎች እጅግ ብዙ ናቸው፤ በአንጻራዊ ሰላም ውስጥ ከሚገኙት የሀገራችን ክፍሎች ሁሉ ‹ዳቦንና ሰላምን› የሚጠብቁ ወገኖች አያሌ ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር የቤተ ክርስቲያንን ድምፅ ሰምተው ድጋፍ እያደረጉ ያሉ አካላት አሉ፡፡ ይሁንም እንጂ ከችግሩ ግዝፈትና ክብደት የተነሣ በቂ ሊሆን አልቻለም፡፡ ስለዚህ አሁንም ሰላማችንንና ዳቦአችንን የሚፈልጉ ወገኖች ብዙ ናቸው፡፡ የሰላሙንም ሆነ የምግቡን ጉዳይ ከመንግሥት ጀምሮ መልካም ነገርን ለማድረግ የማይመለከተው አካል ስለሌለ ሁሉም የቻለውን ሊያደርግ ይገባል፡፡

መንግሥት፡- ከምንም በላይ የዜጎች ደኅንነት፣ በሰላም መኖር፣ የዕለት ምግባቸውን ማግኘት መቻል፣ በአጠቃላይ መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶላቸው መኖር መቻል ሊያሳስበውና ሊያስጨንቀው ይገባል፡፡ በመሆኑም ሰላም ማስከበር፣ ከየቤታቸው ተፈናቅለው፣ በባዶ ሜዳ ላይ ወድቀው፣ ሰላማቸውን ተገፍፈው እያዘኑና በረኃብ አለንጋ እየተገረፉ ያሉትን ዜጎቹን ማሰብ ይኖርበታል፡፡ ወንጀለኛን ለሕግ ማቅረብና ለተጎዱትም በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ቤተ ክርስቲያን፡- ከላይ እንደተገለጸው ምንም እንኳን የተጨነቁትን ማረጋጋት፣ የተራቡትን መመገብ፣ ለታመሙት መጸለይ፣ ለሞቱት ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ፣ ወዘተ የዕለት ተዕለት ተግባሯ ቢሆንም ከምንጊዜውም በላይ አሁን እጇን መዘርጋት አለባት:: ከዚህም አንጻር የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ መምህራን፣ ዘማርያን፣ ማኅበራት፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶችና ምእመናን ሁላችን ልንጠነቀቅላቸውና ልናደርጋቸው የሚገቡን ምግባራት አሉ::

የመጀመሪያው፡- የተጎዱ ወገኖቻችንን ሥነ ልቡና መጠበቅ ነው:: ከላይ በተጠቀሱት ክልሎችም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች በተከሠቱ ጦርነቶችና ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች ቀጥተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖች ከአካልና ከንብረት ጉዳቱ በላይ በሥነ ልቡና ተጎድተዋል:: ቤተ ሰቦቻቸውን አጥተዋል፤ የሰው ልጅን ክፋትና ጭካኔ በዓይናቸው አይተዋል፤ ወይም ከቤተሰባቸው አባላት ቢያንስ አንዱ በዚህ ችግር ውስጥ ያለፈ ነው:: በነዚህ ወገኖቻችን ፊት ቆመን ስለ ፖለቲካዊ ምልከታችንና ስለ ተፈጸመው ጉዳት ፖለቲካዊ ቅርጽ መተንተንና መከራከር ሰብአዊነትን አለማስቀደም ነው:: ንግግራችን ሁሉ ማጽናናት ላይ ቢያተኩርና በጸሎታችን ሁሉ ብናስባቸው እጅግ መልካም ነው:: ይህ ባይሆን እንኳን ጥፋተኛ ቢሆንም ባይሆንም በጦር የተወጋን ወገን በቃል ጦር ደግመን እንዳንወጋው ዝም ማለት የተሻለ መፍትሔ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል::

ምናልባትም ከቁሳዊው ጉዳት ይልቅ የመንፈስ ጉዳቱ ቊስሉ የሚጠገን ሳይሆን የሚያመረቅዝ ይሆናል:: ለመፈወስም ዘመናትንና ትውልድን ሊጠይቅም ይችላል:: ስለዚህ ሰላምታችንን ለሚፈልጉት ሁሉ አዘውትረን ሰላምታችንን ልናቀርብላቸው ይገባል:: አቅም ባይኖረን እንኳን አብረናቸው እንደ ሆንን የምናሳይባቸውን መንገዶች ማስፋት ይኖርብናል::

ሁለተኛው፡- በቻሉት አቅም ሁሉ በልተው እንዲያድሩ ማስቻል ይገባል:: በእነዚህ ቦታዎች ላይ የተጎዱ አብያተ ክርስቲያናት፣ የተቋረጡ አገልግሎቶች፣ ከምንም በላይ ደግሞ ዕለት ዕለት የሚራቡና የሚታረዙ በሃይማኖት የሚመስሉንም የማይመስሉንም ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን አሉ:: ችግሩ ከደረሰባቸውም ሆነ ከየአለንበት አህጉረ ስብከቶቻችን ጋር በመመካከር ለእነዚህ ወገኖቻችን ከሰላምታችን ጋር ዳቦአችንንም ልናካፍላቸው ይገባል::

ቃለ ወንጌልን አስተምህሮ ያላመኑትን ለማሳመን፣ የአመኑትን ለማስጠመቅ፣ የተጠመቁትን ለማጽናት፣ ሃይማኖት ባልተስፋፋባቸው ቦታዎች ሁሉ እየተዘዋወሩ ለማስተማር፣ ሰዎች መመገብና በሰላም መኖር አለባቸው:: ስለዚህ ለሰዎች ሰላምና በልቶ ማደር እጅግ አብዝተን መጨነቅ አለብን::

አባቶቻችን በሃይማኖትና በሀገር ላይ የመጣ ጠላትን ታቦት ይዘው ዘምተው በአድዋ መመከታቸውን የምንዘክርበት ወር ላይ መገኘታችን ደግሞ ለዚህ ጥሩ የማንቂያ ደወል ነው:: ዛሬ በሥውር እንጂ እንደ ጥንቱ በግልጽ የሚመጣ ጠላት ላይኖር ይችላል:: እኛም ግልጹን ብቻ ሳይሆን ሥውሩንም፣ ግዙፉን ብቻ ሳይሆን ረቂቁንም እየመረመርን ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር አለኝታነታችንን ማሳየት ይገባናል::

*የሰላም አምላክ ሰላሙን ከእኛ አይለይብን!*

# “በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ”

(ኢዩ.፪÷፲፪)



ዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ

ቸርነት፣ ደግነት፣ ምሕረትና ይቅር ባይነት የባሕርይ ገንዘቦቹ የሆኑለት አምላካችን እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠራቸው የሰው ልጆችን ከመንገዱ በመውጣት በጠላት ወጥመድ ተይዘው እንዳይቀሩ “ወደ እኔ ተመለሱ” እያለ ዘወትር ይጣራል፡፡ ይህ ጥሪ የንስሓ ጥሪ ነው፡፡ ንስሓ የቃሉ ትርጉም መጸጸት መቆጨት፣ በሠሩት ክፉ ተግባር ማዘን ማለት ነው፡፡ (ደስታ ተክለ ወልድ ገጽ ፷፱፻፷፰) በሌላ በኩል ደግሞ ንስሓ በሙሉ ልብ መመለስንና መለወጥን ያመለክታል፡፡ የሰው ልጅ ድካም የሚስማማውን ሥጋ እንደ መልበሱ ይደክማል፤ ይዝላልም፡፡ ከእውነት መንገድ፣ ከጽድቅ፣ ከሕይወት፣ ወጥቶ ይስታል፡፡ ይሁን እንጂ የሚያስብ አእምሮና የሚያመዛዝን ኅሊና ያለው ፍጡር እንደመሆኑ የሠራውን ስሕተት አስተውሎ መጸጸቱ የማይቀር ነው፡፡ ጸጸቱ የሐሳብ ለውጥ መኖሩን ያመለክታላል፡፡ ነገር ግን የሐሳብ ለውጥ ብቻ መፍትሔ አይሆንምና በተግባር መለወጥ አለበት፡፡ በሐሳብም በተግባርም መለወጥ ማለት ደግሞ አጠቃላይ የሕይወት ለውጥ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ንስሓ የሚባለውም ይህ ነው፡፡ ማለትም በመጀምሪያ ያለንበትን ሁኔታ ቆም ብለን ማሰብ፤ ያለንበት ሁኔታ ከትክክለኛው የሕይወት መስመር የወጣ እንደሆነ መጸጸትና መቆጨት፤ ቀጥሎም የበደልነውና የተጣላነው ሰው ካለ ይቅርታ መጠየቅና መታረቅ፣ ከሁሉ በላይ ሕጉን በመተላለፍ ያሳዘንነው አምላካችን ይቅር እንዲለን ደጅ መጥናት ንስሓ ይባላል፡፡ ከንስሓ በኋላም ወደ ትትክለኛው መንገድ በመመለስ አዲስ ሕይወት መጀመር ይጠበቅብናል፡፡

ጠቅለል አድርገን ስንመለከት ንስሓ እኖር እከብር ባይ ኅሊና የሚያሳስበንን ሥጋዊ ፍላጎት ተከትለን፣ ስላጠፋነው ጥፋት ስለ በደልነውም በደል ምሕረትና ይቅርታ የምንጠይቅበት ለኃጢአትና ለጥፋት የጋበዘንን ሥጋችንን የምንገሥጽበትና የምንቀጣበት፣ የእግዚአብሔርንም ቸርነት ደጅ የምንጠናበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህም ማለት አስቀድመን በተከተልነው ክፉ ሐሳብና በፈጸምነው የጥፋት ተግባር የምንቆጭበት፣ የምንጸጸትበት፣ራሳችንን የምንወቅስበት ወደኋላም ተመልሰን የቀደመ ስሕተታችንን ላለመድገም ቃል የምንገባበት ሥርዓት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ “ልጆቼ ወደ እኔ ተመለሱ” እያለ ዘወትር የሚጠራንን የአምላካችንን ድምፅ መስማት ይጠበቅብናል፡፡ ነቢዩ ኢዮኤልም ይህንኑ ሲናገር ነው “አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ” ያለው፡፡ (ኢዩ.፪÷፲፪) እዚህ ላይ ዋይታና፣ ልቅሶ፣ የሚሉ ቃላት ንስሓን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ንስሓ አውቀን በድፍረት ሳናውቅ በስሕተት በሠራነው ጥፋት ተቆጭተን ወዮልኝ ባላደርገው ምን ነበር እያልን ራሳችንን የምንወቅስበት ሥርዓት ነውና፡፡

ስለዚህ ንስሓን ስናስብ ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን መዘንጋት የለብንም እነሱም፡- መናዘዝ፣ የሚሰጠንን ቀኖና መፈጸምና፣ ለኃጢአታችን ሥርየት የተሠዋልንን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን መቀበል የሚሉት ሲሆኑ እነዚህንም ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

## ፩. ኃጢአትን መናዘዝ፡-

የራስን ጥፋት አውቆ ለእግዚአብሔርም ለሰውም መናገር መናዘዝ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አስተምህሮ መናዘዝ ስንል ሰው በሐሳብ፣ በንግግር እና በተግባር በፈጸመው ኃጢአት ተጸጽቶ “እባክህ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቀኝ” ብሎ ጥፋቱን ለካህን ዘርዝሮ የሚናገርበት ሥርዓት ነው፡፡ አንድን ተነሳሒ እና ካህንን የንስሓ ልጅና አባት የሚያሰኘው ዋናው ጉዳይም ይህ ነው፡፡ የንስሓ ልጅም የንስሓ አባት የመያዙ መሠረታዊ ጉዳይ ይኸው ነው፡፡

መናዘዝ የሚለውን ቃል ስናነሣ በሉቃስ ወንጌል የተጻፈውን የጠፋው ልጅ ታሪክ መመልከት ይጠቅመናል፡፡ ታሪኩ እንደሚነግረን፡- አንድ አባት ሁለት ልጆች ነበሩት፡፡ ከሁለቱ አንዱ /ታናሹ/ ድርሻውን ተካፍሎ ለመውጣት ፈለገ፡፡ አባቱም ከሀብቱ ለልጁ ሊደርሰው ይገባል ያለውን ድርሻውን ከፍሎ ሰጠው፡፡ ልጁም ድርሻውን ተቀብሎ ወደ ሩቅ ሀገር በመሄድ ሀብቱን አባክኖ ጨረሰ፡፡ ኋላም በሚኖርበት ሀገር ጽኑ ራብ በሆነ ጊዜ ለአንድ ገበሬ እሪያ ለማሰማራት ተቀጠረ፡፡ ከመራቡም የተነሣ እሪያዎች ከሚበሉት አሰር ሊመገብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠው ግን አልነበረም፡፡ ያን ጊዜም “ወደ ልቡ ተመልሶ እንዲህ አለ፡- እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ፡፡ ተነሥቼም ወደ አባቴ

እሄዳለሁና:: አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ" አለ:: እንዳለውም አደረገ:: አባቱንም "አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም" አለው:: አባቱ ግን ገና ሩቅ ሳለ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው:: ጎረቤቶቹንም ጠርቶ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም:: ደስም ይበለን ብሎ ታላቅ ድግስ ደገሰ ይለናል (ሉቃ.፲፭፥፲፩-፴፪)::

ይህን ምሳሌዊ ትምህርት በቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት ሊቃውንት በብዙ መንገድ ያመሠጥሩታል:: እኛ ግን አንዱን ብቻ ብንመለከት የሁለት ልጆች አባት የተባለው የሁሉ ፈጣሪና አባት እግዚአብሔር ነው:: ሁለቱ ልጆች ደግሞ ቅዱሳን መላእክትና አዳም /የሰው ልጆች/ ፣ የጠፋው ልጅ ማለትም ታናሹ የተባለው አዳም ፣ ወደ ልቡ መመለሱ ደግሞ ንስሓ ለመግባት መወሰኑን፣ ጥፋተኛ ነኝና ልጅህ ልሆን አይገባኝም አገልጋይህ አድርገኝ ማለቱም ጥፋተኛነቱን አምኖ፣ ተጸጽቶ መናዘዙን ያስረዳልናል::

የሰው ልጅ የለበሰው ሥጋ ለኃጢአት የሚስማማ ከመሆኑ የተነሣ ዕለት ዕለት አውቆ በድፍረት ሳያውቅ በስሕተት እንዲሁም በቸልተኝነት ሕገ እግዚአብሔርን ይተላለፋል:: በዚህም ምክንያት ከቤተ እግዚአብሔርና ከመንፈሳዊ አገልግሎት ይርቃል:: ይህም የኅሊና ዕረፍት፣ የአእምሮ ሰላም፣ የልብ ደስታ እንዲሁም የሰማያዊ ርስት ተስፋንም ያሳጣዋል:: ያን ጊዜም ያዝናል፤ ይከፋል፤ ወደ ልቡም ተመልሶ መፍትሔ ይፈልጋል:: መፍትሔው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ሽማግሌ መፈለግ ነው:: ይህ ሽማግሌም ካህን ነው:: ካህን ደግሞ እንደ ሽማግሌነቱ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቀኝ ብሎ ሲመጣ አስታርቅህ ዘንድ ጥፋትህ ምንድን ነው ብሎ ይጠይቃል:: እርቅ ፈላጊውም ጥፋቱን(ኃጢአቱን) ዘርዝሮ ይናገራል:: እንግዲህ መናዘዝማለት ይህ ነው::

ይህ ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ ሥርዓት በኦሪትም በወንጌልም ተጽፏል:: ለምሳሌ በኦሪት «ወንድ ወይም ሴት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይተላለፍ ዘንድ ሰው የሚሠራውን ኃጢአት ቢሠራ በዚያም ሰው ላይ በደል ቢሆንበት በሠራው ኃጢአቱ ላይ ይናዘዝ» ተብሎ ተጽፏል:: (ዘፀ.፭፥፯) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ እንደሚገባን ሲናገር ለምጻሞቹ ኢየሱስ ሆይ ማረን እያሉ ወደርሱ ሲመጡ «ወደ ካህን ሂዱና ራሳችሁን አስመርምሩ» በማለት ወደ ካህናት ልኳቸዋል:: ሄደውም ራሳቸውን ለካህን ሲያሳዩ (ኃጢአታቸውን ሲናዘዙ) ከበደላቸው ነጽተዋል:: (ሉቃ.፲፯፥፲፪-፲፭) ራስህን ለካህን አሳይ ማለቱም ለምጽ በኃጢአት ምክንያት የሚመጣ በሽታ ስለነበረ ነው:: (ዘሌ.፲፫፥፵፭-፵፮) ለኃጢአት በሽታ መድኃኒቱ ንስሓ መሆኑ የታወቀ ነው::

የንስሓ ልጆች ለካህናት የተሰጣቸውን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን አምነው ኃጢአታቸውንና በደላቸውን ሳይደብቁና ሳይሳቀቁ ለካህን መናዘዝ አንዱ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል:: ይህን ከማድረጋቸው በፊት ግን ልክ እንደ ጠፋው ልጅ ወደ ልባቸው መመለስና ቆም ብለው ማሰብ የኃጢአተኝነትን ስሜት መራራነት መረዳት ዳግመኛም ወደ ኃጢአት ላለመመለስ መወሰን ኃጢአት በመሥራታቸው የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ማሳዘናቸውን እያሰቡ የንስሐ ኀዘን ማዘን በመጨረሻም «በምድር ያሰራችሁት በሰማይም የታሰረ በምድር የፈታችሁት በሰማይም የተፈታ ይሆናል» (ማቴ.፲፰፥፲፰):: እንዲሁም «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል» (ዮሐ.፳፥፳፫):: ተብሎ ለካህናት የተሰጣቸውን ሰማያዊ ሥልጣን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል:: በመጨረሻም ሁሉን የሚያየውን ልብና ኵላሊትን የሚመረምረውን እግዚአብሔርን በማሰብ እንደነሱ ሰው የሆነውን ካህኑን በመፍራት /በማፈር/ የሠሩትን ኃጢአት አንድም ሳያስቀሩ ዘርዝሮ መናዘዝ የተነሳሕያን መሠረታዊ ግዴታቸው ነው::

## ፪. ቀኖናን ተቀብሎ መፈጸም፡-

ቀኖና ካኖን /canon/ ከሚለው የጽርዕ /የግሪክ/ ቃል የተወሰደ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም መቃ፣ መስፈሪያ፣ መለኪያ፣ መለካት መቁጠር ማለት ነው:: (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ ፯፻፱) ከንስሓ ጋር በተያያዘ ያለውም ትርጉም "አንድ ተነሳሒ በካህኑ ፊት ኃጢአቱን ከተናዘዘ በኋላ ካህኑ ለኃጢአት ማስተሥረያ የሚሰጠው የመንፈሳዊ ቅጣት ቁጥር መጠንና ዓይነት" ማለት ነው:: ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ሁሉ ካህኑ ኃጢአተኛውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ሽማግሌ እንደ መሆኑ መጠን እርቁ እንዲፈጸም ጥፋተኛው ግለሰብ የሚጠበቅበትን መንፈሳዊ ግዴታ ለይቶ ማሳወቁ የማይቀር ነው:: ምክንያቱም እርቅ ሲደረግ የበደለው አካል ይቅርታ ለማግኘት የተበደለው አካል ደግሞ ይቅርታ ለማድረግ በየግላቸው ሊወጡ የሚገባቸው ድርሻ አለና::

በዚህም መሠረት የተነሳሒ ድርሻ በፍጹም ልብ ከመመለስ፣ በተጨማሪ የበደለውን መካስ የቀማውን መመለስ እንዲሁም በጾም በጸሎት፣ በስግደት፣ በፅንባና በዋይታ ወደ እግዚአብሔር ማልቀስ ነው፡፡ ይቅርታ ማድረግ ግን ምሕረትና ቸርነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነው የእግዚአብሔር ነው፡፡

እንግዲህ ካህኑ ለኃጢአተኛው ሰው እግዚአብሔር ይቅር ይልህ ዘንድ መንፈሳዊ ተግባራትን ሥራ ብሎ የሚያዝዘው ትእዛዝ ቀኖና ይባላል፡፡ ይኸውም በብሉይ ኪዳን የኃጢአት፣ የበደል፣ የደኅንነት ወዘተ መሥዋዕት ተብለው የፍየል የበግ የርግብ... መሥዋዕት በማቅረብ ይፈጸም የነበረ ሲሆን በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ጹም፣ ጸልይ፣ ስገድ፣ መጽውት... ወዘተ በመሳሰሉት እንደካህኑ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ቀኖና በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አስተምህሮ መሠረት ሰው ከስሕተቱ የሚታረምበት መንፈሳዊ ተግሣጽ ሲሆን ይህ ግን ምድራውያን ነገሥታት ለወንጀለኞች እንደሚሰጡት ቅጣት የሚታይ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ይቅር የሚለው ኃጢአተኛነቱን አምኖ በማዘኑ፣ በመቆጨቱና ከጥፋቱ በመመለሱ እንጂ ስለበደሉ በሚከፍለው ካሳ ብዛት አይደለምና፡፡ ለዚህም ነው ቀደም ብለን ባየነው የጠፋው ልጅ ታሪክ ላይ ልጁ ለመናዘዝ ወደ አባቱ እየመጣ ሳለ "አባቱ ግን ገና ሩቅ ሳለ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው" የሚለው፡፡ (ሉቃ.፲፭፥፳) ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ ላይ "የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና፡፡" ባለው መሠረት ነው፡፡ (፩ኛ ጴጥ.፬፥፫) አባቶቻችንም ይህንን መሠረታዊ እውነት ሳይዘነጉ ኃጢአተኛው በኃጢአት ባሳለፈበት ዘመን ፈንታ ቀሪ ዘመኑን በጽድቅ ጎዳና እንዲመላለስ ያዝዛሉ፡፡

ሐዋርያው "የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና፡፡" ሲል በቃ ቁጭ በሉ ማለቱ አይደለም፡፡ በዚያ ፈንታ ፈቃደ እግዚአብሔርን አድርጉ ለማለት እንጂ፡፡ አባቶች ካህናትም በዚሁ መሠረት ለኃጢአተኛ ሰው በቀማህበት ፈንታ መጽውት፣ ያለ ልክ በመብላትና በመጠጣት በስካር በኃጢአት ባሳለፍክበት ዘመን ፈንታ ጹም ጸልይ ስገድ በማለት ለኃጢአተኛው ቀኖና ይሰጡታል፡፡ ይህም ተገቢ ነው፡፡

እንዲያውም አባቶቻችን ለባለጸጋ/ ጾምን፤ ለድሃ /ምንም ለሌለው ችግረኛ/ ምጽዋትን በማዘዝ ኃጢአተኞች ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመፈጸም በሰውነታቸው ላይ ጨክነው መወሰንን እንዲለማመዱ ያዛሉ፡፡ ምክንያቱም ለባለጸጋ ምግብ በቤት ውስጥ ሞልቶ ተርፎ እያለ መጾም፣ ለድሃ ደግሞ ቆጥቦ ያስቀመጠውን ወይም ለምኖ ያገኘውን ገንዘብ መመጽወት ከባድ ነውና፡፡ ይሁንና ድሃ ጦሙን አድሮም ቢሆን ይመጸውታል ባለጸጋም ለተወሰነ ቀን ነውና እንደምንም ራቡን ታግሦ ይጾማል፡፡ ከዚህም የተነሣ ሰውነታቸው ኃጢአትን ከመጸየፍ በተጨማሪ ለጽድቅ መታዘዝንም ይለማመዳል፡፡

ስለዚህ ተነሳሒያን የተሰጣቸው ቀኖና በዛ ብለው ሳያንጎራጉሩ አነሰም ብለው ሳይጠራጠሩ በካህኑ ቀኖና ላይ የእግዚአብሔር ቸርነት እና የተነሳሒው ትሩፋት ተጨምሮ ከታላቅ በደልና ኃጢአት እንደሚያነፃቸው አምነው ቀኖናቸውን መቀበልና መፈጸም ይገባቸዋል፡፡

## ፫. ሥጋውንና ደሙን መቀበል፡-

በክርስትና አስተምህሮ የአገልግሎቶች ሁሉ መደምደሚያው ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ነው፡፡ የካህናትና የመምህራንም መሾም ዋና ግቡ ምእመናንን አስተምረው ለሥጋውና ለደሙ ማብቃት ነው፡፡ ምክንያቱም የመንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ ግቡ ሰማያዊ ርስት መውረስ ነውና፡፡ ያለክርስቶስ ሥጋና ደም ደግሞ ሰማያዊ ርስት ማለትም የዘለዓለም ሕይወት የለም፡፡ ምክንያቱም "..እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡" (ዮሐ.፮፥፶) ተብሎ ተጽፏል፡፡

በየጠፋው ልጅ ታሪክ አስቀድመን እንደተመለከትነው ልጁ ወደ አባቱ ቤት ሲመለስ አባቱ ፊሪዳ አርዶ ድግስ ደግሶ ተቀብሎታል፡፡ የጠፋው ልጅ አዳም ነው፡፡ የጠፋውን አዳምን ፍለጋ የመጣው ደግሞ ክርስቶስ ነው፡፡ "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" (ሉቃ.፲፱፥፲)እንዲል፡፡ ለአዳም ምግብ ሊሆን የታረደው ፍሪዳም ራሱ ክርስቶስ ነው፡፡ በቀራንዮ ኮረብታ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ መሥዋዕት ሆኖአልና፡፡ ዓርብ መሥዋዕት ከመሆኑ በፊት ሐሙስ ማታ ላይም "እንጀራን አንሥቶ ባርኮ ቈርሶ እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው፣ በማለት እንዲሁም ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡" በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም የክርስቶስ ሥጋና ደም

ለእኛ የሕይወት ምግብና መጠጥ ሆኖ መቅረቡን የሚናገር ነው (ማቴ.፳፮፥፳፯)።

ስለዚህ እኛም የዘለዓለም ሕይወት ለማግኘትና ሰማያዊ ርስትን ለመውረስ የክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል የግድ ነው። "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።" የሚለውም ይህንኑ የሚያስገነዝበን ነው (ዮሐ.፮፥፶፮-፶፯)።

ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም ለመቀበል አስቀድሞ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ የሚገባ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ "ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት" (፩ኛቆሮ.፲፩፥፳፯) በማለት ይመክረናል። አያይዞም ሥጋውና ደሙ ዕዳ እንዳይሆንብን ማድረግ ያለብንን ጥንቃቄም ሲናገር "ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤" ብሏል (፩ኛቆሮ.፲፩፥፳፰)።

ራሱን ይፈትን ማለቱም "እኔ ምንድን ነኝ ኃጢአተኛ ወይስ ንጹሕ?" ብሎ ራሱን በመጠየቅ መቼም ንጹሕ የለምና በደሉን ለካህን ተናዝዞ ካህኑ የሚሰጠውን ቀኖና ተቀብሎ ከፈጸመ በኋላ ሥጋውንና ደሙን ይቀበል ማለቱ ነው። ለዚህ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምጻሞቹ ማረን ሲሉት በመጀመሪያ ሂዱና ራሳችሁን ለካህን አስመርምሩ ያላቸው። ቤተ ክርስቲያናችንም ይህንን ቃል መሠረት በማድረግ ሥጋውንና ደሙን ተቀብለው ክርስቶስን ለመዋሐድ የሚመጡትን ሁሉ ሂዱና ራሳችሁን ለካህን አስመርምሩ ትላቸዋለች። ራሳቸውን ፈትነው ኃጢአተኛነታቸውን አምነው ለካህን ከተናዘዙ በኋላ ቀኖናቸውን ፈጽመው ለሚመጡት ሥጋውንና ደሙን ትሰጣቸዋለች። ይህን ሳያደርጉ ለሚመጡት ግን ካህኑ "የቀማውን ሳይመልስ የበደለውን ሳይክስ ኃጢአቱንም ለካህን ሳይናዘዝ የመጣ ካለ እኔ ከደሙ ንጹሕ ነኝ" በማለት እያስጠነቀቀ ሥጋውንና ደሙን ይሰጣል። ቅዱስ ጳውሎስም "ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና።" በማለት አስጠንቅቋል (፩ኛቆሮ.፲፩፥፳፱)።

በኦሪቱ በነበረው የመሥዋዕት ሕግም እስራኤላውያን የፋሲካውን በግ ሲመገቡ ጫማቸውን ተጫምተው፣ ወገባቸውን ታጥቀው፣ ኩፌታቸውን ደፍተው በትራቸውን ይዘው እየተቻኮሉ እንዲመገቡ ታዘው ነበር (ዘፀ.፲፪፥፲፩)። "ይህም ዛሬ ላለነው ክርስቲያኖች ምሳሌ ሆኖን የአማናዊውን በግ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን ስንቀበል በጎ ምግባር ሠርተን፣ ወንጌሉን ተጫምተን፣ የንጽሕናን ዝናር ታጥቀን አክሊለ ሦክን ነገረ መስቀሉን እየዘከርን (መስቀሉን ተመርኩዘን) ሞት እንዳለብን በማሰብ እንዳይቀድመን ፈጥነን ንስሓ በመግባት ሥጋውንና ደሙን መመገብ የሚገባን መሆኑን ያስገነዝበናል።

ቀደም ብለን ባየነው የጠፋው ልጅ ታሪክም አባት ልጁ ከጠፋበት ሲመለስ ፊሪዳውን ከማረዱ በፊት "ባሪያዎቹን ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ" በማለት ልጁ ታጥቦ ንጹሕ የሆነውን ለብሶና ተጫምቶ እንዲዘጋጅ ነበር ያደረገው። እንደሚታወቀው ያንን ልጅ ወደ ልቡ እንዲመለስና የአባቱን ቤት እንዲያስብ ያደረገው ረኃብ ነበር። "እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ አለ" እንዲል። ከአባቱ ቤት ካለው ማዕድ ለመቀበል ግን አስቀድሞ ያንን ማዕድ አቋርጦ በመውጣት የበደለውን አባቱን ይቅርታ መጠየቅ ነበረበት።

ስለሆነም አባቱን ማረኝ አለው። አባቱም ይቅር አለው። ከዚያ በኋላ ከፊሪዳው ተመገበ። እኛም ገና በአርባና በሰማንያ ቀናችን ጀምረን ስንመገብ የኖርነውን ሥጋውንና ደሙን አቋርጠን ወደ ተለያየ የኃጢአት ሕይወት ብንገባም እንኳ ወደ ልባችን ተመልሰን ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል ስንመጣ አስቀድመን ስለ ጥፋታችን ይቅርታ መጠየቅ እንደሚገባን ያስገነዝበናል። ይህም ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል ንስሐ ገብተን መዘጋጀት የሚገባ መሆኑን አንድም የንስሓ ጉዞ መጨረሻው በክርስቶስ ሥጋና ደም መደምደም /መቋጨት/ የሚገባ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል።

በአጠቃላይ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ከተለየ በንስሓ መመለስ ይኖርበታል። እግዚአብሔር አምላካችንም በነቢዩ ላይ አድሮ አምላካዊ ጥሪውን ያስተላለፈውና "ወደ እኔ ተመለሱ" እያለ የሚጠራን ለንስሓ ነው። ስለሆነም ሁላችንም በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን ቅዱስ ሥጋውን በልተን ክቡር ደሙን ጠጥተን ከቅዱሳን ማኅበር እንዲጨምረን የራሳችንን ድርሻ መወጣት አለብን። በንስሓ ተመልሰን በቤቱ እንድንኖር እግዚአብሔር በቸርነቱ ቅዱሳን በአማላጅነታቸው አይለዩን አሜን።

# ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው?

*(ቅዱስ ያሬድ ድጓ ዘስምዖን አረጋዊ)*

*በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን*

ድካም በብዙ መንገድ ይገለጻል። በሥጋ መድከምና መሸከም የሚገባውን መሸከም አለመቻል፣ መሥራት በሚገባው መጠን መሥራት አለመቻል፣ መሮጥ በሚገባው መጠን መሮጥ አለመቻል ወዘተ ሁሉ ድካም ይባላል። ሌላው ደግሞ በመንፈስ መድከም ሲሆን ይህም የሚጠበቅበትን ያህል አለመጾም፣ አለመጸለይ፣ አለመስገድ፣ ብሎም በእምነት ጸንቶ አለመኖር ወዘተ የመንፈስ ድክመት ይባላል። አረጋዊው ስምዖን አስቀድሞ በመንፈስ ደክሞ የኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና መወለድ ማመን ተቸግሮ ነበር። በኋላ ግን በዕድሜ ረጅም ዓመታትን በዚህ ዓለም ውጣ ውረድ ከመኖሩ የተነሣ ሽምግሎ ደክሞ ነበር። በዚህ ዐውድ ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው የሚለው በሥጋ መድከሙን አይደለም። ምክንያቱም ምንም ቢደክም የአርባ ቀን ሕፃን መሸከም አይቸገርምና። እንዲህ ከሆነ  የቃሉ ተናጋሪ ኢትዮጳያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ምን ለማለት ነው ይህን የተናገረ የሚለውን ሙሉ ቃሉን እንጥቀስና በዝርዝር እንመለከታለን።

“ለዓለም ዘያዐርፎ  በእንቲአነ ሥጋ ሰብእ ተአጺፎ በከመ አቅደመ እምትካት ተጽሕፎ ስምዖን ካህን ነበረ እንዘ ይሴፎ ሰአለ ከመ ያዕርፎ በሕፃኑ ተወክፎ አረጋዊ ድኩም እፎ ለነበልባል ሐቀፎ።  ዓለምን የሚያሳርፈው ስለእኛ የሰውን ሥጋ ለብሶ (ተጎናጽፎ) ከጥንት ጀምሮ በመጻፍ መናገርን እዳስቀደመ ካህን ስምዖን ተስፋ እያደረገ ተቀመጠ። እንዲያሳርፈውም ለመነ። በዕቅፉም ታቀፈው። ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው።” (ድጓ ዘስምዖን አረጋዊ) በዚህ ምንባብ የሚከተሉትን ነጥቦች መመልከት ይቻላል።

## ሀ. ዓለምን የሚያሳርፈው

ይህን ዓለም በልዩ ጥበቡ ፈጥሮ የሚጠብቀው፣ የሚመግበው፣ ከድካሙ የሚያሳርፈው አምላክ እግዚአብሔር ነው። ይህ ዓለም ከድካሙ የሚያሳርፈው፣ ከውድቀቱ የሚያነሣው፣ ከሕማሙ የሚፈውሰውና ከመከራው ሁሉ የሚያወጣው አጥቶ ለ፶፻፭፻ ዘመን ያህል በመከራ ውስጥ ኑሯል። ይሁን እንጂ ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ይህን ዓለም ከድካሙ አሳረፈው። መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ ነኝና፤ ልቤም ትሑት ነውና፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገኛላችሁ። ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና” (ማቴ.፲፩፥፳፰-፴) በማለት እንደተናገረ ለዓለሙ ሁሉ ያልተቻለውን ሸክም ከላዩ ላይ አንሥቶ ከድካሙ ያሳረፈው ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልደ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ በሥጋም ሆነ በነፍስ የደከሙትን ከድካማቸው ያስርፋቸው ዘንድ ይቻለዋል። በሥጋ ለደከሙት ኃይል ሥጋዊ፣ በመንፈስ ለደከሙት ደግሞ ኃይል መንፈሳዊ በመስጠት ከድካማቸው ያሳርፋቸው ዘንድ ይቻለዋል። በባሕርዩ ድካመ የሌለበት አምላክ “እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በስድስተኛው ቀን ፈጸመ፤ እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ” (ዘፍ.፪፥፪) ተብሎ ተነገረለት። ይህ የሆነው የእኛን ዕረፍተ ሥጋ ሲባርክ ነው። እርሱ ሥራ በፈጸመ ጊዜ ዐረፈ እንደተባለ ሁሉ እኛንም በሊቀ ነቢያት ሙሴ አማካኝነት ሰው ብቻ ሳይሆን እንስሳት ሁሉ እንዲያርፉ አዝዞናል።

ይህን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ “የሰንበትን ቀን ትቀድሳት ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራህን ሥራ፤ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛዋ ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ናት፤ አንተ ወንድ ልጅህም፣ ሴት ልጅህም፣ ሎሌህም፣ ገረድህም፣ አህያህም፣ ከብትህም፣ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርስዋ ምንም ሥራ አትሥሩ፤ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣ በውስጣቸው ያለውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፏልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል፤ ቀድሶታልም።” (ዘፀ.፳፥፰-፲፩) ተብሎ ተጽፎ እናገኘዋለን።

አስቀድሞ ለሰው ልጅ እንደሚያሻው አውቆ ዕረፍትን በዚህ መልኩ እንዳዘጋጀለት ሁሉ አማናዊውን ዕረፍት ሊያድለን በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የእኛን ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም መጣ። ስለዚህ "ለዓለም ዘየዓርፎ፤ ዓለምን የሚያሳርፈው" ተብሎ ተነገረለት።

## ለ. የሰውን ሥጋ ለበሰ

እግዚአብሔር አምላካችን ዓለምን ያድንበት ዘንድ የመረጠው እና የወደደው የድኅነት መንገድ የሰውን ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም በመምጣት ወይም በሥጋ መገለጥ ነበር። ይህ የማዳን ሥራ የተገለጠበት መንገድም ምሥጢረ ሥጋዌ ተብሏል። ይህም ጥበቡ ሊቃውንቱን እጅግ አስደንቋቸው እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል ብለዋል። የተራቆቱትን የሚያለብሰው አምላክ የሰውን ሥጋ ለበሰ፤ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ የሰውን ልጅ ብቻ ሳይሆን " ኪነ ጥበቡ መንክር ወዕፁብ ለዘሀሎ መልዕልተ አርያም አርአየ ሥልጣኖ ላዕለ ሞት ዘከለሎ ለሰማይ በዋክብት ብሩሃን። ወለምድርኒ አሠርገዋ በጽጌያት ንጹሓን አርአየ ሥልጣኖ ላዕለ ሞት፤ በላይ በአርያም ያለው አምላክ ጥበቡ እጅግ ይደንቃል፤ ሥልጣኑን በሞት ላይ አሳየ፤ ሰማይ በብሩሃን ከዋክብት የሸፈነ፣ ምድርንም በንጹሓን አበቦች ያስጌጠ አምላክ ጥበቡ እጅግ ድንቅ ነው" (ድጓ ዘዮሐንስ) በማለት የተናገረለት አምላክ የእኛን ሥጋ ለበሰ።

"በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ያም ቃል እግዚአብሔር ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ።"

የእኛን ሥጋ ለብሷልና በረደው፤ በመሆኑም በልደቱ ጊዜ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም የበለስ ቅጠል አለበሰችው፤ እንስሳት እስትንፋሳቸውን ገበሩለት፤ አዳምን የጸጋ ልብስ ያለበሰ እርሱ ተራቆተና የሚለብሰው አጣ፤ ረቂቅና ሰማያዊ ልብስ የሆነውን ብርሃን አልብሶ ብርሃን አኅናጽፎ በመንፈሳዊው ልደት የሚወልደን አምላክ የእኛን ግዙፍ ሥጋ ለበሰ። ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በውዳሴው "የመመኪያችን ዘውድ፣ የድኅነታችን መጀመሪያ፣ የንጽሕናች መሠረት እኛን ለማዳን ሰው የሆነ የግዚአብሔርን ቃል በወለደችልን በድንግል ማርያም ሆነልን" (ውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ) በማለት እንደተናገረ እኛን ያድን ዘንድ የእኛ ሥጋ ለበሰ።

ወንጌላዊው ዮሐንስም "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ያም ቃል እግዚአብሔር ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ።" (ዮሐ. ፩፥፩-፫) በማለት ቀዳማዊነቱን፣ ሁሉ በእርሱ ሆነ ብሎ ዓለማትን ሁሉ የፈጠረ አምላክ መሆኑን ከነገረን በኋላ ይህ ዓለምን የፈጠረው አምላክ እኛን ለማዳን ሲል የእኛን ሥጋ መልበሱን ደግሞ "ያም ቃል ሥጋ ሆነ፤ በእኛም አደረ" (ዮሐ. ፩፥፲፬) በማለት አስረዳን። ስለዚህ ሊቁ ዓለምን የሚያሳርፈው ስለኛ የሰውን ሥጋ የለበሰው በማለት ይህ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የሰውን ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም የተገለጠው አምላክ ዓለማትን ሁሉ የፈጠረ መሆኑን አስረዳን።

## ሐ. አስቀድሞ እንደተጻፈ

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን በአበው ምሳሌ በነቢያት ትንቢት አስቀድሞ የተነገረ ነው። ነገሩን አስቀድሞ በኦሪት ያጻፈው በነቢያትም ያናገረው መሆኑን በተመለከተ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ "አቅዲሙ ነገረ በኦሪት አቅዲሙ ነገረ በኦሪት ከመ ይመጽእ ወልድ በስብሐት ዘይዜንዋ ለጽዮን ቃለ ትፍሥሕት። ወካዕበ ይቤ በአፈ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ብርሃን ዘመጽአ ውስተ ዓለም፤ ዘያበርህ ላዕለ ጻድቃን መርዓዊሃ ለቤተ  ክርስቲያን ይርዳዕ ዘተኀጕለ ያስተጋብእ ዝርዋነ መጽአ ውስተ ዓለም፤ ወልድ በክብር በምስጋና እንደሚመጣ አስቀድሞ በኦሪት ተናገረ፤ ዳግመኛም በዳዊት አፍ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ  የተባረከ ነው አለ፤ በጻድቃን ላይ የሚያበራው ወደዚህ ዓለም የመጣው ብርሃን ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ሙሽራ የጠፉትን ይመልስ ዘንድ፣

የተበተኑትንም ይሰበስብ ዘንድ ወደዚህ ዓለም መጣ::" (ድጓ ዘአስተምህሮ) በማለት አስቀድሞ በኦሪት የተጻፈ በነቢያትም የተነገረ መሆኑን ይመሰክራል::

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከማረጉ አስቀድሞ ለሐዋርያት በአስተማራቸው መጽሐፈ ኪዳን (ትምርተ ኅቡአት) "ዘበነቢያት አቅደመ ተዐውቆ ወበ ሐዋርያት ተሰብከ ወእመላእክት ተአኰተ ወእምኀበ ኵሉ ተሰብሐ፤ በነቢያት መታወቅን አስቀደመ፤ በመላእክት ተመሰገነ፤ በሁሉ ዘንድም ተመሰገነ" ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን:: ይወርዳል ይወለዳል፤ የእኛን መከራ ተቀብሎ ያድነናል:: እየተባለ በነቢያቱ እንደተነገረ ከሰማየ ሰማያት ወረደ፤ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ተወለደ፤ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ ይህን ዓለም አዳነ:: ይህ ሁሉ አስቀድሞ የተነገረ፣ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፈ ስለሆነ ሊቁም አስቀድሞ እንደተጻፈ አለን::

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ለዕብራውያን ምእመናን በላከው መልእክቱ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ::" (ዕብ.፩፥፩) በማለት እንዳስረዳው ይህ ሁሉ አስቀድሞ በብዙ ምሳሌና በብዙ ትንቢት የተነገረ ነው:: በመሆኑም ይህ ዓለምን የሚያሳርፈውን፤ ስለ እኛ የሰውን ሥጋ የለበሰውን፤ ይህንም አስቀድሞ በኦሪትና በነቢያት ያናገረውን አምላክ አረጋዊው ስምዖን በዐይኖቹ ያይ ዘንድ በተስፋ ሲጠብቅ ኖረ::

## መ. ስምዖን በተስፋ ተቀመጠ

ተስፋ በሃይማኖት የመኖራችን አንዱ መገለጫው ነው:: እግዚአብሔር ያደርግልኛል ብሎ አምኖ የሚደረግልንን ነገር በተስፋ መጠበቅ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖራችን በእግዚአብሔርም ለማመናችን መገለጫው ነው:: ስምዖን የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲተረጉም "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠዋለች::" (ኢሳ. ፯፥፲፬) የሚለውን ንባብ ሲያነብ ከበደው:: ድንግል እንዴት በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ልትወልድ ትችላለች በማለት ተቸገረና ድንግል የሚለውን ሴት እያለ መጻፍ ጀመረ:: ያን ጊዜም የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ መጥቶ ይህን እስክታይ አትሞትም ብሎት ነበርና እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ ቆይቷል:: ይህን ቅዱስ ሉቃስ "በኢየሩሳሌምም ስሙ ስምዖን የሚባል አንድ ሰው ነበር፤ እርሱም ጻድቅና ደግ ሰው ነበር፤ እርሱም የእስራኤልን ደስታቸውን ያይ ዘንድ ተስፋ ያደርግ ነበር፤ መንፈስ ቅዱስም ያደረበት ነበር:: የእግዚአብሔርንም መሢሕ ሳያይ እንደማይሞት መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነበር:: (ሉቃ.፪፥፳፭-፳፮) በማለት ጽፎት እናገኛለን::

ከአዳም ጀምሮ የሰው ልጅ በሙሉ የእግዚአብሔርን መምጣት በተስፋ ይጠባበቅ ነበር:: የሰው ልጅ ድኅነትን አገኛለሁ ከሲኦል እወጣለሁ፣ እከብራለሁ፣ የተወሰደብኝ ሁሉ ይመለስልኛል ወዘተ. ብሎ ተስፋ ያደረገ ሲሆን መላእክትም የሰው ልጅ ድኅነት እጅግ ደስ ስለሚያሰኛቸው የእርሱን መምጣት ይጠባበቁ ነበር:: ሊያዩትም ይመኙ ነበር:: በጸሎተ ኪዳን "ዘያፈትዎሙ ለመላእክት ከመ የሐውጽዎ፤ ይኅበኙት ዘንድ የሚያስመኛቸው" ተብሎ እንደተጻፈ:: ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም "ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ" (፩ጴጥ. ፩፥፲፪) ብሎ እንደጻፈልን መላእክቱ ሳይቀሩ ይመኙት ነበር:: ከእነዚህ ከሰው ልጆችና ከመላእክት በተለየ ሁኔታ ዕረፍተ ሥጋም ሳያገኝ የመሢሑን መምጣት በተስፋ ይጠባበቅ የነበረው ስምዖን አረጋዊ መሆኑን ሊቁ "ስምዖን ካህን ነበረ እንዘ ይሴፎ፤ ስምዖን ካህን ተስፋ እያደረገ ነበረ" በማለት ይስረዳናል::

## ሠ. ስምዖን ካህን ታቀፈው

የመሢሑን መምጣት በተስፋ ይጠባበቅ የነበረው አረጋዊ ጊዜው በደረሰ ጊዜ መንፈስ አነሣሥቶት ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ:: በዚያም የኦሪቱን ሕግ ሊፈጽም በአርባ ቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ የወሰዱትን ሕፃኑን አገኘው፤ ታቀፈውም:: ይህም በቅዱስ ወንጌል "መንፈስም ወደ ቤተ መቅደስ ወሰደው፤ ዘመዶቹም በሕግ የተጻፈውን ያደርጉለት ዘንድ ሕፃኑን ጌታችን ኢየሱስን ወደ ቤተ መቅደስ ባገቡት ጊዜ እርሱ ደግሞ ተቀብሎ በክንዱ ታቀፈው፤ እግዚአብሔርንም አመሰገነው::" (ሉቃ.፪፥፳፪-፳፰) ተብሎ ተጽፎ እናገኘዋለን::

ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና በጆሮአችን የሰማነውን፣ በዐይኖቻችንም ያየነውን፣ የተመለከትነውንም፣ እጆቻችንም የዳሰሱትን እንነግራችኋለን" (፩ዮሐ.፩፥፩) ብሎ እንደጻፈው ቅድመ ዓለም የነበረው ዓለምን የፈጠረው፣ ዓለምን

ያዳነው አምላክ፣ በባሕርይው የማይታየው አምላክ የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ፣ በሐዋርያት እጅ የሚዳሰስ፣ በሐዋርያት ዐይን የሚታይ፣ በሐዋርያት ጆሮ የሚሰማ ሆነ። ይህን አምላክ ስምዖን አረጋዊ ታቀፈው። ቃል አይታይም የእኛን ሥጋ ሲዋሐድና በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የማይታየው ታየ፤ የማይዳሰሰው ተዳሰሰ፤ ዘመን የማይቆጠርለት አምላክ ዘመን ተቆጠረለት።

እግዚአብሔር በባሕርዩ አይታይም። ወንጌላዊው ዮሐንስ "በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ገለጠልን እንጂ እግዚአብሔርንስ ከቶ ያየው የለም" (ዮሐ. ፩፥፲፰) በማለት እንደነገረን በእኛ አእምሮ አይመረመርም፣ በዐይነ ሥጋ አይታይም፣ ይሁን እንጂ "ወኮነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ፤ ከኃጢአት ብቻ በቀር እንደ እኛ ሰው ሆነ" (ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ) ተብሎ እንደተነገረ የእኛን ሥጋ ተዋሕዷልና በስምዖን ዕቅፍ ተይዞ ታየ።

## ረ. ያሳርፈው ዘንድ ለመነ

ሰው ዕድሜ ቢጨመርለት ይፈልጋል። በተለይም የሰማያዊውን ዓለም ሕይወት ያልተረዱትና በዚህ ዓለም ያለውን ድሎት የሚያስቀድሙ አካላት ዕድሜያቸው ቢጨመርላቸው ይፈልጋሉ። አረጋዊ ስምዖን ግን "አሰናብተኝ" በማለት ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም መሄድን መረጠ። በቅዱስ ወንጌል "እንዲህም አለ አቤቱ እንዳዘዝህ ዛሬ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ። ዐይኖቼ ትድግናህን አይተዋልና። በወገንህ ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ለአሕዛብ ብርሃንን ለወገንህ ለእስራኤልም ክብርን ትገልጥ ዘንድ" (ሉቃ.፪፥፳፱-፴፩) ተብሎ እንደጻፈ አረጋዊው ስምዖን ዕረፍቱን መረጠ።

ሰማያዊውና ዘለዓለማዊው ሕይወት ሲገባቸው ከዚህ ዓለም ሕይወት ይልቅ የወዲያኛውን ዓለም ይመርጣሉ። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "እኔ ፈጽሜ ግዳጄን ጨርሻለሁ፤ የማርፍበት ዕድሜዬም ደርሷል። መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴንም ጠብቄያለሁ። እንግዲህስ የጽድቅ አክሊል ይቆየኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም" (፪ጢሞ.፬፥፯-፰) በማለት እንደተናገረ ከዚህ ዓለም ኑሮው ይልቅ የወዲያኛውን ዓለም ሕይወት መርጧል። ይህም ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ኑሮ ይልቅ የወዲያኛውን ዓለም እጅግ አብዝተው የሚወዱት መሆናቸውን ያስረዳናል።

ሥጋ ለለበሰ ሁሉ ይህ ሞት የሚቀር አይደለም። ይሁን እንጂ እንደማይቀር እያወቅን ቢሆንም ሞታችንን አንፈልገውም። በሥጋዊ ሐሳብ ስንመላለስ የሚታየውን ብቻ እናስቀድምና በዚህ መኖራችንን አብዝተን እንመኛለን። አረጋዊው ስምዖን ግን "የናርኩት ይበቃኛል ከዚህ በኋላ ብትወድስ ባሪያህን ታሰናብተዋለህ" እያለ ዕረፍቱን ሲለምን እንመለከታለን። አረጋዊው ስምዖን ዕረፍቱን መመኘቱን ብቻ ሳይሆን እንደ ሕፃን ሕገ ኦሪትን ሊፈጽም በእናቱ ዕቅፍ ወደቤተ መቅደስ የመጣው አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን፣ ዕረፍተ ሥጋ ዕረፍተ ነፍስ የሚሰጥ እርሱ መሆኑን በሚገባ ተረድቷል። መረዳቱንም "እነሆ ይህ ሕፃን ከእስራኤል መካከል ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ይሆን ዘንድ የተሰየመ ነው" (ሉቃ.፪፥፴፬) በማለት በተናገረው ቃል መረዳት ይቻላል። ስለዚህ ለሚያምኑበት ሁሉ ዕረፍተ ሥጋ ዕረፍተ ነፍስን የሚያድል አምላክ መሆኑን ስለተረዳና ስላመነ እንዲያሳርፈው ለመነው።

**"እነሆ ይህ ሕፃን ከእስራኤል መካከል ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ይሆን ዘንድ የተሰየመ ነው"**

## ሰ. ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው?

ሊቁን እጅግ ያስደነቀው ይህ ነገር ነው። አረጋዊው ስምዖን በመጀመሪያ ሊሆን ያለውን ለማመን ተቸገረ፤ እርሱ የታቀፈው ነበልባል ደግሞ በደካማው ሽማግሌ ዕቅፍ ታየ። አረጋዊወ ስምዖን ለማመን የተቸገረበትንም ድንቅ ምሥጢር ፈጸመ፤ አረጋዊው ስምዖን ምን አልባትም ለሦስት ለአራት መቶ ዘመናት በመኖሩ ብሉየ መዋዕል የተባለ ሽማግሌ ቢሆንም አስቀድሞ ማመን የተቸገረበትን ረቂቅ ምሥጢር የፈጸመው አምላክ ደግሞ ቅድመ ዓለም በንግሥናው የነበረ ንጉሥ ነው። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው" (መዝ.፸፫፥፲፪) በማለት እንዳስረዳን ከዘመናት በፊት የነበረ፤ ዓለምን የፈጠረ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" (ዘፍ.፩፥፩) እንዲል። ዛሬም ያለ ወደፊትም የሚኖር ዘለዓለማዊ አምላክ ነው። ነቢዩ ዳዊት "አንተ ግን አንተ ነህ ዓመትህም ከቶ አያልቅም" (መዝ.፻፩፥፳፯) በማለት እንደተናገረው በዘመናት የማይወሰን አምላክ ነው። እንዲህ ያለውን አምላክ መታቀፍ እጅግ ያስደንቃልና በአድናቆት ተናገረ።

**ሊቁ ግን በእምነት መነጽርነት ተገልጾለት እንደሌሎች በመጠራጠር ሳይሆን በማመንና በማድነቅ እየተመለከተ በውስጡ የተፈጠረውን አድናቆት ይናገራል። ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ አንድ ሽማግሌ ታቀፈው፤ በእርግጥም የሚደንቅ ነው።**

እሳት በባሕርዩ የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ አይደለም። ይሁንም እንጂ ከብረት ጋር ሲዋሐድ የጋለውን ብረት ባለሙያዎች በመቆንጠጫ ይይዙታል። በቅዱስ ወንጌል "እግዚአብሔርንስ ከቶ ማንም ያየው የለም" (ዮሐ.፩፥፲፰) የተባለው አምላክ የእኛን ሥጋ ለብሶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ግን በአንዲት ብላቴና ማሕፀን የሚወሰን፣ ባለሙያው "ና ሕፃኑን ግረዝ" ተብሎ የሚመጣበት፣ የኦሪትን ሕግና ሥርዓት ሊፈጽም ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄድ፣ እንዲሁ አረጋዊው ስምዖንም የሚታቀፈው ሆነ። ቅዱስ ያሬድ ይህ ድንቅ ሥራ ስላስደነቀው "ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው?" በማለት በአድናቆት ተናገረ።

ለሙሴ በደብረ ሲና ሲገለጥለት ነበልባሉ ከሐመልማሉ ሐመልማሉ ከነበልባሉ ተዋሕዶ ነበር። እንደሊቃውንቱ አገላለጽ ነበልባሉ የመለኮት፣ ሐመልማሉ ደግሞ መለኮተ የተዋሐደው ሥጋ ምሳሌ ነው። ሊቁ አባ ሕርያቆስም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት ቅዳሴው "እሳት በላዒ ለአማፅያን ለእለ ይክሕዱ ስሞ፣ እሳት ማሕየዊ ለርቱዐነ ልብ ለእለ ይገብሩ ፈቃዶ፤ ለአመፀኞች የሚባላ እሳት ነው፤ እንደፈቃዱ ለሚኃዙትና ልባቸው ቅን ለሆኑት የሚያድን እሳት ነው" (ቅዳሴ ማርያም) በማለት እንደገለጸው አምላክ እሳት ነው። ግን አንድ ደካማ ሽማግሌ ታቀፈው። ሊቁ ይህ ስላስደነቀው "ደካማው ሽማግሌ ነበልባሉን እንዴት ታቀፈው?" በማለት በአድናቆት ተናገረ።

የክርስቶስ ሰው መሆንና ወደዚህ ዓለም መምጣት ለሚያምኑት የሚደንቅ፣ ለማያምኑት ደግሞ እየረቀቀባቸው የሚሰናከሉበት ነው። ሊቁ ግን በእምነት መነጽርነት ተገልጾለት እንደሌሎች በመጠራጠር ሳይሆን በማመንና በማድነቅ እየተመለከተ በውስጡ የተፈጠረውን አድናቆት ይናገራል። ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ አንድ ሽማግሌ ታቀፈው፤ በእርግጥም የሚደንቅ ነው።

በአጠቃላይ ሊቁ ዓለምን የሚያሳርፈው፣ እኛን ለማዳን የእኛን ሥጋ የለበሰው፣ በአንድ አረጋዊ ዕቅፍ የታየው፣ አረጋዊውም አምላክነቱን ተረድቶ እንዲያሳርፈው የለመነው አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑ ያስረዳናል። እኛም እንደ አረጋዊው ስምዖን ዕረፍተ ሥጋ ዕረፍተ ነፍስን የሚያድል አምላክ መሆኑን በማመን እንደንማጸነው፤ እንደ ቅዱስ ያሬድም ምሥጢሩን ተረድተን የተረዳነውንም ለሌላው እንድናስረዳ፤ ይህንንም ድንቅ ምሥጢር በማመን ከፍጹም እምነት ከሚገኘው በረከት እንድንሳተፍ እግዚአብሔር ይፍቀድልን።

# የአድዋ ድል ቤተ ክርስቲያን በገነባችው የሥነ ልቡና ልዕልና የተገኘ ነው።



*ዲ/ን ኅሊና በለጠ*

‹‹ሃያ ሺህ ያህል ወታደሮች ያሉበት የኤሮፓ ጦር በአፍሪካ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ተሸነፈ። በኔ እምነት መሠረት በዘመናችን ታሪክ ውስጥ እንደ አድዋው ያለ ጦርነት የለም።... በአፍሪካ በኩል ታላቅ የተወላጆች ኃይል መነሣቱ ታወቀ። የአፍሪካ ተወላጆች ታሪክ ተለወጠ። ጥቁሩ ዓለም በኤሮፓውያን ላይ ሲያምጽና ሲያሸንፍ የመጀመሪያው መሆኑ ነው። አበሾች አደገኛ ሕዝቦች መሆናቸው ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ ተጽፎላቸዋል። የኛ ዓለም ገና ቶርና ኦዲዮን በሚባሉ አማልክት ሲያመልክ በነበረበት ጊዜ አበሾች የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበሉ ናቸው። አሁን የኹሉንም ፍላጎት አድዋ ዘጋው...››። (ጳውሎስ ኞኞ፣ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፣ ገጽ ፪፻፱)።

ይህንን የተናገረው ቤርክሊይ የተባለ ጸሐፊ ነው። (Berkeley, George; The Campaign of Adowa and the Rise of Menilik)። ከአድዋ ጦርነት በኋላ ይህና እንዲህ ዓይነቱ የአድናቆት ምስክርነት ከዓለም ዙሪያ ለኢትዮጵያውያን መበርከቱን የተለያዩ የታሪክ መዛግብት ይመሰክራሉ። የአድዋ ድል የዓለም ፖለቲካዊ አካሔድ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ነበረው። እንዲያውም የዚያን ዘመኑን የቅኝ ግዛት ዘመን ከአድዋ በፊትና ከአድዋ በኋላ ብሎ መክፈልና ማጥናት ይቻላል። በዓለም ላይ ከታዩ እጅግ አስገራሚና ወሳኝ ክስተቶች እንደ አንዱም መመደብ የሚችል ነው። ይህ የሆነው ደግሞ በጊዜው አሉ የተባሉትን ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን የታጠቀችና ከጊዜው ኃያላን አንዷ የሆነች አንዲት አውሮፓዊት ሥልጡን ሀገር፣ እዚህ ግባ የሚባል ሥልጣኔ በሌላትና እንደ አውሮፓውያኑ የምታመርተው ቀርቶ የምትገዛውና በእርዳታ የምታገኘው የጦር መሣሪያ እንኳን በቁጥር ውሱንና እጅግ ኋላ ቀር በሆነ፣ ዘመናዊ የጦርነት ስልትን እንደ ሌሎቹ ያልተራቀቀችበት፣ ጦርና ጋሻን በያዙ ዜጎቿ የምትዋጋ እንጂ የወታደሮቿ ቊጥር ጥቂት በሆነባት፣ በአንዲት አፍሪካዊት ሀገር መሸነፏ ነበር።

ጦርነቱ በሁለት አውሮፓውያን ወይም በሁለት አፍሪካውያን ሀገራት መካከል የተደረገ ቢሆን ኖሮ፡ ጥቂትም ቢሆን የኃይል መመጣጠን ስለሚኖር ይህን ያክል አያስደንቅም ነበር። ነገር ግን በጉልበተኞች ጽንፍ ባለች በአንዲት ሀገርና በምስኪኖች ጽንፍ ባለች በሌላ ሀገር ምክንያት የተደረገ በመሆኑና ውጤቱም ሥጋ ለባሽ ከሚጠብቀው አመክንዮአዊ ውጤት እጅግ የተለየ መሆኑ አስገራሚ ያደርገዋል። ከጦርነቱ መጀመር አስቀድሞ ጳውሎስ ኞኞና አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ እንደ ገለጹት ‹‹ሁሉም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እንደምታሸንፋት›› ያስቡ የነበረው ይህን አለመመጣጠን በሰውኛ መነጽር በማየት ነበር። ታዲያ ድሉ እንዴት ተገኘ?

የድሉ ዋና መሠረት የሥነ ልቡናና አስተሳሰብ ሚዛን ነበር። የኢጣሊያ ወታደሮች በዘመናዊ መሣሪያዎቻቸውና በውጊያ አቅማቸው ክፉኛ ተማምነውና መተማመናቸውም ወደ ትዕቢት ከፍ ብሎ ነበር። ‹‹...በቅርብ ቀን ምኒልክን በቀፎ ውስጥ አሥሬ ሮማ ውስጥ አመጣዋለሁ...›› ይል የነበረው የኢጣሊያ የጦር መሪ፡ የጄኔራል ባራቲዬሪ ንግግርም ይህንን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነበር። ሕዝቡም ገና ጦርነቱ ሳይጀመር ‹‹ድል አድራጊው›› እያሉ እርሱን መጥራታቸው የዚህ ሌላው ማሳያ ነበር። (ጳውሎስ ኞኞ፣ ፪፻፫)።

በኢትዮጵያውያን በኩል ምንም እንኳን የኢጣሊያ ዐቅም እጅግ እንደሚልቅ ቢረዱትም፡ ከንጉሡ አዋጅ ጀምሮ ካላቸው የጦር ቁስ ይልቅ በእግዚአብሔር ላይ መተማመናቸው ጎልቶ ይታይ ነበር፦

‹‹እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ። እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ። እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደ ፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም።

‹‹አሁንም ሀገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቶአል። እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ፣ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ

አልሰጠውም። ያገሬ ሰው፤ ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም፤ አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበትም የሌለህ ለልጅህ ለሚሽትህ ለሃይማኖትህ ስትል በኀዘን እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ፤ አልተውህም፤ ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረኢሉ ከተህ ላግኝህ።›› (ጳውሎስ ኞኞ፣ ፻፶፮-፻፶፱)።

በዚህ አዋጅ ላይ ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ የሚያኖረው እግዚአብሔር እንደ ሆነ፣ ርትዕንና ፍትሕን እስከ ያዙ ድረስ በእግዚአብሔር እርዳታ አለመጠራጠር፣ ጠላትን በጠላትነት የመፈረጁ ነገር የመጣው ሀገር የሚያጠፋና ሃይማኖት የሚለውጥ በመሆኑ እንደ ሆነ፣ በእግዚአብሔር ረዳትነት እንደሚዋጉት፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በውጊያና በጉልበት ብቻ ሳይሆን ለሃይማኖት ሲባል በማዘንም ማገዝ እንደሚቻል ማመን እንደሚገባ ተገልጾአል። ጦርነትን በውጊያ ብቻ ሳይሆን ‹‹የሚያዝኑ ብፁዐን ናቸው›› እንደ ተባለ በማዘንና ወደ እግዚአብሔር በማልቀስ ድል መንሣት ይቻላል ብሎ ማሰብ ምን ዓይነት መንፈሳዊ የሥነ ልቡና ልዕልና ነው? (ማቴ. ፳:፴)። ኢጣሊያኖች የጎደላቸው ይህ ዓይነቱ ‹‹መሣሪያ›› ነበር።

የኢጣሊያ መልእክተኞች ሁሉ ለጦርነት መቋመጣቸውንና በጉልበታቸው ክፉኛ መመካታቸውን ያዩት እቴጌ ጣይቱም ‹‹የእስራኤል አምላክ ሆይ፣ ይህን ግፍ ተመልከት። በመድፋቸውና በጠብ መንጃቸው ተመክተው የፈቀዳቸውን ተናገሩ፤ ኃይል የእግዚአብሔር መሆኑን አላወቁም። እኛም በክርስቶስ ኃይል አንፈራቸውም›› ማለታቸው ያነሣነውን ጉዳይ በግልጽ የሚያሳይ ነው።

የአድዋ ጦርነት እጅግ የተለያየ የኑሮና የፍልስፍና ሐሳብ (Paradigm) ባላቸው ሁለት ተቃራኒ ሀገራት መካከል የተደረገ ጦርነት ነው። አንደኛዋ ሀገር ቅኝ ገዢና ወራሪ፣ ብዙ ሀገራትን አስቀድማም የወረረች፣ አሉ ከተባሉ ሥልጡን ሀገራት አንዷ፣ ባለኝ የጦር መሣሪያና የሠለጠነ የወታደር ኃይል አሸንፋለሁ ብላ የምታስብና የምትወጋትን ሀገር እጅግ የናቀች፣ ጥቁር የነጭ ባሪያ መሆንና በነጭ ሥር መተዳደር አለበት ብላ የምታምን፣ የሌላ ሀገርን ሀብትና ንብረት ለመዝረፍ የመጣች፣ የወታደሮቿ የመጨረሻ ግብ ቅኝ ገዝተው ጀግና ተብለው መሞገስና የተሻለ ሀብትንና ዝናን እንደ ሀገርም እንደ ግልም ማካበት የሆነባት… ወዘተ ነበረች። ሁለተኛዋ ደግሞ በተቃራኒው ቅኝ ገዝታም ተገዝታም የማታውቅ፣ የቅኝ ግዛት አስተሳሰብንም ‹አግባብ አይደለም› ብላ የምትጠየፍ፣ ከሥልጣኔ አንጻር እጅግ ኋላ ቀር የምትባል፣ ከጉልበት ይልቅ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ዜጎች የሞሉባትና የቱንም ሀገር ስለ ድህነቱ የማትንቅ፡ ስለ ብልጽግናውም ክባ የማትፈራ፣ የሰው ልጅ ሁሉ በፈጣሪ አምሳል የተፈጠረና እኩል እንጂ ማንም የማንም ባሪያ እንዳልሆነ የምታምን፣ የሌላን የማትነካ የራሷንም የማታስነካ፣ የዜጎቿ (የወታደሮቿ) የመጨረሻ ግብ ሀገርንና ሃይማኖትን ማዳንና ለዚህም ሲባል በመሠዋት ሰማያዊ ክብርን ማግኘት … ወዘተ ነበር።

በዚህ የእሳቤ መሠረት የተነሣ ኢትዮጵያውያን ወኔያቸው ልዩ ነበር። ይህ ወኔ ‹‹የቆምኩትና የምዋጋው ለእውነት ነው፤ ምድራውያን ብቻ ሳይሆኑ እግዚአብሔርና በሰማይ ያሉ አገልጋዮቹ ሁሉ አብረውኝ አሉ፤ ብሞት እንኳን ሞቴ የከበረ ነው›› የሚል ግዙፍ አስተሳሰብ የፈጠረው ፍርሃትን የሚያርቅ ወኔ ነው። በዘመነ ሰማዕታት ክርስቲያኖች ወደሚሞቱበት ቦታ ሲወሰዱ እንደ ሌሎች ከመፍራትና ከመለማመጥ ይልቅ በፈገግታና ወደ ሰርጉ እንደሚሔድ ሙሽራ በደስታ እንደ ነበረው ሁሉ፡ ኢትዮጵያውያንም ይህ ዓይነቱ አሳብ በልባቸው የተሰነቀ ነበር። ስለዚህ ምንም መሣሪያን ያልያዙት፣ እንኳን መሣሪያን ሊይዙ ይቅርና ለእግራቸው ጫማ ያላደረጉትም ቢሆኑ ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጸጉሩ የታጠቀ የኢጣልያ ወታደር ፊት ሲቆሙ በጥብዐትና በጀግንነት ነበር።

በአንጻሩ ደግሞ የኢጣልያ ተዋጊዎች የኃይል ሚዛኑ በጥቂቱም ቢሆን ወደ ኢትዮጵያውያን ባደላበት ጊዜ ሁሉ ፍርሃት የሚወራቸው ዓይነት ነበሩ። የአምባላጌን በመሰሉት ውጊያዎች ላይ የኢትዮጵያውያኑን ድል ካዩ በኋላ አስጨናቂ የፍርሃት ዝግጅትን ያደርጉ የነበረው ለዚሁ ነበር። የመቀሌው ምሽግ እዚህ ላይ ሁነኛ ማስረጃ ይሆነናል፤

ጳውሎስ ኞኞ (፻፸፪-፻፸፫) እንደ ተረከው በመቀሌው ምሽግ የኢጣሊያ ወታደሮች በቅድሚያ ፫ ሜትር ስፋት ያለው ግንብ ገነቡ። ይህ አልበቃ ብሏቸው በ፴ ሜትር ውስጥ በጣም የሾሉ ከፍታቸው ፴ ሳ.ሜ. የሆኑና አንዱ ካንዱ በ፳ ሳ.ሜ. የሚርቁ እንጨቶችን በብዛት ቸከሉ። ኢትዮጵያውያኑ ግር ብለው ሲመጡ እግረኞቹም ፈረሰኞቹም በነዚህ እንጨቶች

ላይ እየወደቁ ተሰክተውባቸው እንዲሞቱ ነበር። ይህም አልበቃቸውም፤ ከዚያ ቀጥሎ እሾኻማ ሽቦ እያድበለበሉ አስቀመጡ። ይህም ‹‹እንኳን ሰው ወፍ አያሾልክም›› የተባለለት ነበር። አሁንም ፍርሃቱ ስላልለቀቃቸው ጠርሙስ ሰብረው ነሰነሱ። ይህም በባዶ እግራቸው የሚመጡ የኢትዮጵያውያንን እግር ሸረካክቶ ለማስቀረት ነበር። ለመሞት አስቀድመው የተዘጋጁት አባቶቻችን ግን ታንክና ተዋጊ ቆራርጦ ባይኖራቸውም፡ ይህን ሁሉ ያልፉ ዘንድ በሃይማኖት ጥብዐት የተቃኘው ወኔያቸው በቂ ነበር። በባዶ እግራቸው በጠርሙስ ላይ ለመራመድ፣ ስስ ልብስ በሸፈነው ገላቸውም የተጠቀለለ ሽቦን ለመሻገር አላመነቱም። ግዙፉን ምሽግ እግዚአብሔርን ይዘው ሰበሩት።

ይህ የኢትዮጵያውያኑ ወኔ ያስገረመው የኢጣሊያው የጦር መሪ የነበረው ጄኔራል ባራቲዬሪ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

‹‹እኛ የሠለጠነው ዓለም ሥልጡን ወታደሮች ምንም አያውቁም ከሚባሉት ኢትዮጵያውያን የምንማረው ትምህርት አለ። አበሾች ለባሩድና ጥይት ይሳሳሉ። የሚገድሉ ካልሆነ በስተቀር አይተኩሱም። ለዚያውም ቢሆን ፲ እና ፲፭ እርምጃ ያህል ቀርበው ባንድ ጥይት ደራርበው መግደል ይፈልጋሉ። ያለዚያ ተደበላልቀው በጎራዴ መምታት ይመርጣሉ እንጂ ጥይት ማበላሸት አይወዱም። ይህም በማስጮህ ብቻ ጥይት ለሚያባክነው ለሠለጠነው አገር ወታደር ጥሩ ትምህርት ነው። ለምሳሌ ደጀን የነበረው የመድፈኛው አዛዥ ካፒቴን ፍራንዚኒ መድፎቹን ይዞ ከጦር ሜዳ እንዲገባ ታዘዘ። ፴ ኪ.ሜ. ያህል ተጉዞ ከጦሩ ሜዳ ገባ። ቦታውን አመቻችቶ አንድ የመድፍ ጥይት ገና እንዳስተኮሰ ተገደለ። ይህም ሊሆን የቻለው ያቺን የመድፍ ጥይት ድምጽ የሰሙ ኢትዮጵያውያን በንዴት ተሞልተው በብዛት ሆነው ስለ ወረሩት ነው። የተመካንባቸው ደጀን የነበሩት መድፎቻችንም ካንድ ጥይት ተኩስ በኋላ ተማረኩ…››።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ታሪከ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ በሚል መጽሐፋቸው እንደ ገለጹትም ‹‹…ሠራዊቱ ቀለብ ሊያመጣ የሔደው፣ አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ሊስም የሔደው ኹለት እጁ ነው እንጂ አንድ እጁ ለጦር አልደረሰም። የተኩሱን መድመቅ በሰማ ጊዜ ሠራዊቱ ተሰልፎ ተነሣ። አጤ ምኒልክም ከበቅሎ ወጥተው ወደሱ መንገድ ጀመሩ። ሰልፉ ግን አልተገናኘም። በየፊቱ ክምር እንዳየ ዝንጅሮ ወደ ጦሩ ወደ መድፉ ይሮጥ ነበር።… መድፉ ይመታኛል፣ ነፍጡም ይጥለኛል እሞታለሁ ብሎ ልቡ አልፈራበትም። …የቈሰለውም ሰው ‹አልጋው ይቁም እንጂ ኋላ ስትመለስ ታነሣኛለህ፣ በመሀይም ቃሌ ገዝቼሃለሁ› ይለው ነበር። ጥይትም ያለቀበት እንደ ሆነ የቈሰለውን ሰው ከወገቡ ዝናሩን እየፈታ እያባረረ ወደ ፊት ይተኩስ ነበር። ሰውም ከመንገድ ርዝመት ከተኩሱ ብዛት የተነሣ ደክሞት የተቀመጠ እንደ ሆነ ‹የምኒልክ ወርታ፣ የጮማው የጠጁ ይህ ነውን?› እየተባባለ እንደ ገና እየተነሣ ይዋጋ ነበር››።

በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ልዩነትን ጠንቅቀው ያውቁ የነበሩት ኢትዮጵያውያኑ ከጦርነቱ በፊት ጦርነቱ እንዳይካሔድ ያደረጉት ጥረትና ከጦርነቱ በኋላም ያሳዩት ጠባይ ከፍርሐትም ከተዐብዮም የራቀና ክርስቲያናዊነትን የተሞላ ነበር። የዐፄ ዮሐንስ ልጅ የሆኑት ራስ መንገሻ ዮሐንስ ከአዲ አምባይ የጦር ሰፈር ለጣልያኑ ንጉሥ አስቀድመው ‹‹ለታላቁና ለተከበሩ ንጉሥ ኡምቤርቶ፤ በአሁኑ ጊዜ ሰይጣን በመካከላችን በመግባቱ ክርስቲያን የሆንን ሕዝቦች እርስ በርሳችን እንድንፋጅ ሆነ፤ ባለፈው ጊዜ የደረሰው ሁሉ የሰይጣን ሥራ ነው። ሰላምን ስለምንፈልግ እውነተኛና ትክክለኛ የሆነ ሰው ይላኩ።›› በማለት መልእክትን መላካቸው ለዚህ ማሳያ ነው።

ጦርነቱ በድል ከተጠናቀቀ በኋላም ታዲያ ይህ ትሕትና በትዕቢትና በትምክህት ሳይቀየር ንጉሡ ‹‹በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ። እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የእነዚያን ሁሉ ክርስቲያኖች ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየሁ ድል አረግሁአቸው ብዬ ደስ አይለኝም…›› ማለታቸው ይህንን የመንፈሳዊ ልዕልና ያሳያል። (ጳውሎስ ኞኞ፣ ፻፶፱)።

‹‹እኔ ሴት ነኝ። ጦርነት አልወድም። ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከመቀበል ጦርነት እመርጣለሁ…›› (ጳውሎስ ኞኞ፣ ፻፵፰) ብለው የተናገሩት የእቴጌ ጣይቱ ታዋቂ ንግግርም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ‹‹ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ›› የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ሲተረጉም ‹‹እግዚአብሔር ከሌለበት ሰላም እግዚአብሔር ያለበት ጦርነት ይሻላል›› ብሎ ከተናገረው ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው። (ሮሜ.፲፪፥፲፰)። በእውነትም ሀገርና ሃይማኖትን ከሚያሳጣ ‹ሰላም›ስ ጦርነት ይሻላል።

በርግጥ በአድዋ ድል ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽዖ በብዙ መልኩ የሚነገር ነው።

በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸውንና ሕዝቡን የሚመሩ አባቶችን ሁሉ አዝምታለች፤ ማዝመቷም በጸሎት እንዲያበረቱ ነው። ይህም ለዘማቹ ሁሉ እጅግ የሚያበረታታ ተግባር ነበር። ከዘመቱት መካከል ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ፣ እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ፣ የደብረ ሊባኖስ ፀባቴ፣ ከእንጦጦ ማርያም የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ፀሐይ ኪዳነ ወልድ፣ ንቡረ ዕድ ተክለ ጊዮርጊስ፣ መምሬ ገብረ ሥላሴ፣ መምህር ተክለ ማርያም፣ አፈ ንቡረ ዕድ ገብረ ማርያም፣ መምህር አርአያ፣ መምህር ገብረ መድኅን፣ ቀኝ ጌታ ቢሆን…ወዘተ ካህናት፣ ሊቃውንት (ከቀራንዮ መድኃኔዓለም፣ ከሆለታ ኪዳነ ምሕረት….) ይገኙበታል። ሕዝቡ እግዚአብሔር አብሮት እንዳለ እንዲያስብና በዘመቻ መንገዱ ሁሉ የሥነ ልቡናው ብርታት እንዳይሸረሸርም የንዋያተ ቅድሳት አብሮ መዝመት አስፈላጊ ነበር። ከታቦታት-- የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ እንጦጦ መንበረ ፀሐይ ቅድስት ማርያም፣ ከሸዋ የግንባርዎ ማርያም፣ የበር ግቢ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የአክሱም ማርያምና መድኃኔዓለም…ወዘተ የዘመቱ ሲሆን መስቀሎች፣ ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት፣ ቃጭል፣ ጥላዎች፣ ድባቦች፣ ሥዕላት - በተለይም የግንባርዎ ማርያም ‹አምለሱ› ሥዕለ ማርያም …ወዘተ ዘምተዋል። (በአድዋ ጦርነትና ድል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ፣ ገጽ ፷፮-፷፰)።

**‹‹የዓድዋን ድል ተከትሎ በመላው ዓለም ተበትነው ያሉ ዝርዋን አፍሪካውያን የዓድዋን፣ የምኒልክንና የነጻይቱን አገር ኢትዮጵያን ስም በልዩ ሁኔታ ማንሣት ጀመሩ፤ ጥቁር ሕዝቦች እንደ ታላቂቷ ጽዮናዊት ኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ጉዞ ማድረግ ጀመሩ።››**

በርግጥ ታቦትና ንዋያተ ቅዱሳትን ይዞ መዝመት ብቻ ለድል አያበቃም፤ እግዚአብሔርን በማያስቆጣ መንገድ መጓዝና ከእውነትና ከፍትሕ ጎን መሰለፍ እንጂ። ቤተ ክርስቲያንም ንዋያተ ቅድሳትንና የሃይማኖት አባቶችን ከማዝመትም በላይ የምእመናንን ሥነ ልቡና የገነባችበት መንገድ ለጦርነቱ እጅግ አስፈላጊ ነበር። ምናልባትም ያ ባይኖር ድሉም አይኖርም ነበር። ብዙ ጸሐፊዎችም ድሉን ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚያያይዙት ለዚሁ ነው።

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ የተባሉ ሊቅ ‹‹ለኢትዮጵያ ታሪኳ-ነው መልኳ›› በተሰኘው መጽሐፋቸው የአድዋውን ድል መሠረት እንደሚከተለው ገልጠዋል።

‹‹… ምኒልክን ለአድዋው ድል ያበቃቸው

አንዱም ፣ ኦርቶዶክሳዊ እምነታቸውና የልብ ጸሎታቸው ነው።›› (ገጽ፣፹፩)

ዳንኤል ሮፕስ የተባለ ታዋቂ የፈረንሳይ ጋዜጠኛ ‹‹የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ታውቋታላችሁን?›› በሚል ርእስ ባዘጋጀው መጣጥፍ ላይ የሚከተለውን አስፍሯል።

“ወራሪዎች ምድርዋን የያዙባት መሆኑን ታሪክ ያወሳል፤

ነገር ግን ሃይማኖት የእንቅስቃሴ መሣሪያዋ ሆኖ በመገኘቱ በነፃነት ተመልሳ ተገኝታለች››

የአድዋን ድል በቀጥታ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር ያያያዙት ሌሎችም ኢትዮጵያን በአፍሪካ እንደምትገኝ ኢየሩሳሌም አድርገው መቊጠር ጀምረው ነበር። ፕሮፌሰር ሬይሞንድ ጆናስ ‹‹ THE BATTLE OF ADWA:-African victory in the age of Empire›› በተሰኘው ታሪካዊ መጽሐፋቸው ‹‹የዓድዋን ድል ተከትሎ በመላው ዓለም ተበትነው ያሉ ዝርዋን አፍሪካውያን የዓድዋን፣ የምኒልክንና የነጻይቱን አገር ኢትዮጵያን ስም በልዩ ሁኔታ ማንሣት ጀመሩ፤ ጥቁር ሕዝቦች እንደ ታላቂቷ ጽዮናዊት ኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ጉዞ ማድረግ ጀመሩ።›› ሲሉ መግለጻቸው ለዚህ ምስክር ነው።

አንድ ጣልያናዊ ተዋጊም ‹‹በነጭ ፈረስ ተቀምጦ ወደ ቀኝና ወደ ግራ እየተመላለሰ ወደ ጦርነቱ ግቡ ኢጣሊያኖችን ማርኩ እያለ ትእዛዝ ሲሰጥና ሲዋጋን የዋለ ማነው?›› ብሎ መጠየቁ እየተገለጸ የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ አጋዥነት መገለጹም እዚህ ላይ መነሣት የሚገባው ነው። (በአድዋ

ጦርነትና ድል...፣ ፶፫)፡፡ ይህንንም በአንድ ባለ ቅኔ፡-

‹‹ኃይል ውእቱ ዘጊዮርጊስ፣

አኮኑ ኵዕናት

በላዔ ሮማዊት ነፍስ፣

ዘጌዴዎን ምኒልክ

ዘአውረደ በዐውደ ሮምያ

ጠለ ደም እምርእስ፡፡ (በአድዋ ጦርነትና ድል...፣ ፶፪)፡፡ (የሮማዊትን ነፍስ (ሰውነት) የበላ (ድል ያደረገ) የጊዮርጊስ ኃይል እንጂ ጦር አይደለም፣የጌዴዎን ምሳሌ ምኒልክ በሮምያ አደባባይ ከራስ ላይ እስካወረደ ጠብታ ደም፡፡) ተብሎ የተነገረ ነው፡፡

የአድዋ ድል ብሔራዊና ዓለም ዐቀፋዊ ትሩፋቱ ባሻገር ሃይማኖታዊ ትሩፋቱም መነገር የሚገባው ነው፡፡ ‹ኢትዮጵያውያንን እንደ እስራኤል ዘነፍስ መቍጠርና ሀገሪቱንም ጸጋ እግዚአብሔርን የታደለችና ሀገረ እግዚአብሔር እንደ ሆነች አድርጎ ማየት፣ ሀገረ እግዚአብሔር ከሆነች ዘንድም መደፈር የለባትም በሚል እሳቤ ድንበሯን መጠበቅና በዚህም ሂደት መሠዋት የዜግነት ክብር ብቻ ሳይሆን ጽድቅም ነው ብሎ ማመን› ለኢትዮጵያውያን አዲስ እሳቤ ባይሆንም በአድዋ ድል ግን ይበልጥ ጠንክሯል፤ ከዓለም ሕዝብ መካከልም ይህንን ያመኑ እጅግ ብዙ ነበሩ፡፡ ከነጮች ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የጥቁሮች የሃይማኖት እንቅስቃሴ በተለይ በአሜሪካና በደቡብ አፍሪካ ‹ኢትዮጵያኒዝም› በሚል ስያሜ እንዲጀመር መሆኑ ለዚህ ምስክር ነው፡፡

ለማጠቃለል ያህል የአድዋ ድል ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በገነባችው የመንፈሳዊ ሥነ ልቡና ብርታትና ለሀገርና ለሃይማኖት እስከ ሞት የመጋደል ወኔ የተገኘ መሆኑ ከድሉ እኩል መነገር ያለበት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን የኢጣሊያን ወረራ በሀገረ እግዚአብሔር ላይ እንደ ተደረገ ሰይጣናዊ ጥቃት ነበር የቈጠሩት፡፡ ለዚህም ነው ድሉን እንኳን ሰይጣን ድል ከተነሣበት ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር በማመሳሰል

‹‹ሞያ ለሞት

ሠዐሮ ለጣዖት

ገብረ ትንሣኤ በሰንበት›› እያሉ ዳግመኛም

‹‹ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ

ተሐፂባ በደመ ሰማዕታት››

ብለው እየዘመሩ ያከበሩት፡፡ (በአድዋ ጦረነትና ድል...፣ ፳)፡፡

የአድዋ ጦርነት ሊጀመር ሰዓታት በቀሩበት ጊዜ እንደ ተዋጊ ሳይጨነቁ፣ ሁሉን ትቶ በተጠንቀቅ ከመቆምና የነደፉትን የውጊያ ስልት ከማሰላሰል ይልቅ ‹እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ይበልጣል› በሚል ታላቅ የሥነ ልቡና ዐቅም ዐፄ ምኒልክ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፣ ራስ መኮንን፣ ራስ መንገሻ፣ ፊታውራሪ ገበየሁ ገቦ ...ወዘተ በአድዋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እያስቀደሱ ነበር፡፡ በርግጥ ከዚህም በኋላም ንጉሡ በእርጋታቸው ጸንተው ዕለቱ ጊዮርጊስ በመሆኑ አሁንም ወደማይጕዓጕዓ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ልባዊ ጸሎትን አቅርበው ነበር፡፡ በጦርነት መጀመሪያ የመጨረሻው ሰዓት ለዚያውም ዐቅሙ እጅግ የሚገዝፍ ጠላት ከፊት ተደግኖ እንዲህ ዓይነት መረጋጋትን ያሳዩ ሌሎች ተዋጊዎች መኖራቸው እጅጉን አስገራሚ ነው፡፡ ይህ በርግጥም መንፈሳዊ ጥብዐት እንጂ ምን ይባላል?

በአድዋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፡ ተሰብስበው ሲያስቀድሱ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ቀዳሽ ነበሩ፡፡ እርሳቸውም ከቅዳሴ በኋላ ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ፡-

‹‹ልጆቼ ሆይ... ዛሬ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚፈጸምበት ቀን ነው፡፡ ኺዱ ለሃይማኖታችሁ፣ ለሀገራችሁ ሙቱ፤ እግዚአብሔር ይፍታህ››፡፡ (ጳውሎስ ኞኞ፣ ፪፻፫)፡፡

በእውነት የእግዚአብሔር ፍርድ በዕለቱ ተፈጸመ፤ ለሀገርና ለሃይማኖት የተሠዉትን ሁሉ ነፍሳቸውን ይማርልን፡፡



# ዐቃብያነ እምነት/ቀዋምያን ለቤተ ክርስቲያን

ዐቢይ ጉዳይ

*ሕግና ዕቅበተ እምነት አገልግሎት ማስተባበሪያ*

ባለፈው ጽሑፋችን ዕቅበተ እምነትን በተመለከተ በጥቅሉ መጻፋችን ይታወሳል። ይህ ጽሑፍም ካለፈው የቀጠለ ሲኾን በተለይ ዐቃብያነ እምነት ወይም ቀዋምያን ለቤተ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩ አባቶችን ሕይወትና ጽሑፋቸውን የሚዳስስ ነው።

ኹለተኛው ክፍለ ዘመን በርካታ ፈተናዎችን በቤተ ክርስቲያን ላይ የጋረጠ ክፍለ ዘመን እንደ ነበር ተመልክተናል። የሮም መንግሥት በግዛቶቹ ሁሉ ክርስትናን ሕጋዊነት የሌለው አዲስ እንቅስቃሴ አድርጎ በመቍጠሩ ክርስቲያኖች እንደ ወንጀለኛና የመንግሥት ተቃዋሚ ተደርገው እንዲታዩ መንገድ ከፍቶ ነበር። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አዲስ አቀራረብ ያላቸው የዕቅበተ እምነት ጽሑፎች መውጣት ጀመሩ። በዚህ ሂደት የአቴንሱ ዮስጢኖስ የመጀመሪያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

## ፩. ሰማዕቱ ዮስጢኖስ /Justin Martyr (፻-፻፷፭ዓ.እ/AD.)

በኹለተኛው ክፍለ ዘመን ከተነሡ ዐቃብያነ እምነት አንዱ የሆነውና በጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ጽሑፎች ጥናት ስሙ በሰፊው የሚነሣው ዮስጢኖስ ነው። (Johannes Quasten, Patrology Vol. I,፻፺፮.) ጥንት የሰማርያ ክፍል በነበረችው፣ ናብሉስ (Neapolis/Nablus) ከኢአማንያን ወላጆች የተወለደ፣ እስከ ሠላሳ ዕድሜው ድረስ የተለያዩ የፍልስፍናና ሌሎችንም የዕውቀት ዘርፎችን ሲያጠና ቆይቶ በ፻፴ ዓ.እ/AD. ክርስትናን የተቀበለ፣ በመጭረሻም ታላቅ የክርስትና ጠበቃ መኾን የቻለ አባት ነው። (Cross, The Oxford Dictionary of the Christian Church, 1974, 770.)

In this time also Justin, a genuine lover of the true philosophy, was still busy studying Greek learning. He too indicate this date, when in his Defense to Antonius he writes: ... (Eusebius, The History of the Church, 4:8.) ታዋቂው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ዮስጢኖስን በዚህ መልኩ ያነሣዋል። በዚህም የግሪክ ፍልስፍና ትምህርቱንና የፍልስፍና ወዳጅነቱን፣ ብሎም ከዕቅበተ እምነት ጽሑፎቹ መካከል የኾነውን ለአንቶኒዮስ ፒዮስ የጻፈውን አቤቱታ ጨምሮ ይዘክረዋል።

ዮስጢኖስ ፍልስፍናን በጥልቀት የተማረና ከታዋቂ ፈላስፎች ተርታ መጠራት ችሎ የነበረ፣ ክርስትናን ከተቀበለ በኋላም ለክርስትና ጠበቃ የሆነ አባት ነው። እውነትን ፈልጎ ከማግኘት ጠንካራ ፍላጎቱ የተነሣ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን የተማረ ሲኾን፤ ጥልቅ ተመራማሪም ነበር።

አንድ ቀን ነገሮችን በጥልቀት በሚያሰላስልበት የተመሰጠ ጊዜው በባሕር ዳርቻ ሲመላለስ ሕይወቱን የለወጡትን አንድ አረጋዊ አገኘ። አረጋዊው በዕድሜ የገፋ ኾነው ምክንያታዊና ታሪካዊ ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ የነበራቸው ዕውቀት አስገርሞት ነበር። ነቢያት፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን የተናገሯቸው ትንቢቶች በምን ዓይነት ሁኔታ እንደ ተፈጸሙ፣ የሐዲስ ኪዳንና የክርስትናን ነገር አፍታተው ሲነግሩት ከግሪክ ፍልስፍና የቀደመ ዕውቀት እንዳለ ተረዳ። በክርስትና ውስጥ ያለው እውነት በፍልስፍና ውስጥ ካለው ዕውቀት እጅግ የላቀ እንደኾነም ገለጹለት። ንግግራቸውን ጨርሰው በተለዩት ጊዜ ዮስጢኖስ ራሱ በሰጣቸው ምስክርነቶች ውስጥ የሚከተሉትን ሐሳቦች አስፍሮ ነበር።

አፍላጦናዊ ለኾነው የፍልስፍና ዘይቤ የተለየ ዝንባሌ ነበረኝ። ሌሎቹንም በሚገባ ተምሬያቸዋለሁ ብዬ አስብ ነበር። ይኹን እንጂ አረጋዊውን ሰው ካገኘኋቸው በኋላ ነገሮች ተቀየሩ። አፍላጦናዊም ኾነ የትኛውም ፍልስፍና የሰው ልጅን የሕይወት ጥያቄዎች በተሟላ መልኩ እንደማይመልሱ ነገሩኝ። በማነሣቸው ነጥቦች ሁሉ የክርስትናን ምላሽ እያቀረቡ መፈናፈኛ አሳጡኝ። ከዚያች ቀን በኋላ አይቻቸው ባላውቅም እያንዳንዱ ቃላቸው በነፍሴ ውስጥ የጫረው እሳት ሲቀጣጠል ይኖራል። ለነቢያት የተለየ ፍቅር አደረብኝ፣ የክርስቶስን ሐዋርያት ቃል በነገር ሁሉ መከተል ጀመርኩ። ፈላስፋ ስለኾንኩ እያንዳንዱ ሰው

በእኔ መንገድ እንዲያልፍ እመኛለሁ። ነገር ግን ከአዳኙ እውነትና ትምህርት እንዲያፈነግጡ ሳይኾን እምነታቸውን እንዲያጠነክሩ ነው። እኔ የገባኝ ነገር ቢኖር ከፍልስፍና ሁሉ የላቀ እውነት በክርስትና ውስጥ አለ።" (Dialogue ፰.)

ከዚህ ልዩ አጋጣሚ በተጨማሪ ክርስትናን እጅግ በላቀ አትኩሮት እንዲመለከት ያደረጉትን የቀደሙ ሁኔታዎችንም ያነሣ ነበር። እነዚህም ክርስቲያኖችንና ትምህርታቸውን እንዴት ባለ ንቀት ይመለከት እንደ ነበረና ኋላ ግን፤ "በሰማዕትነት ለመሞት የነበራቸውን ቁርጠኝነት፣ ፍቅራቸውንና መተባበራቸውን ስታዘብ መገረም ጀመርኩ። እንደዚህ ዓይነቱ ብቃት በቀላሉ የሚገኝ እንዳልኾነም መገንዘብ ጀመርኩ" እያለ ተናግሯል። "I myself found satisfaction in Plato's teaching, and used to hear the Christians abused, but when I found them fearless in the face of death and all tat men think terrible, it dawned on me that they could not possibly be living in wickedness and self-indulgence. ..." ( Defence ፩፥፰፱; Eusebius, The History of the Church, ፲፱፻፹፭፣፻፲፩.)

## ለአረማውያን የተጻፈ (Against Pagans)

በዚህ አጠራር የሚታወቁት የዮስጢኖስ ጽሕፎች ኹለት ዓይነት መልክ ያላቸው ናቸው፡ አጠቃላይ አሕዛብን የሚነቅፍበትና በቀጥታ ለአንቶኒዮስ (፻፴፯፻፷፩ ዓ.እ/ AD.) የተጻፉ። ቀደም ሲል በአውሳብዮስ የተነሣው የዮስጢኖስ ጽሑፍ በቀጥታ የተጻፉ ለሚባሉት አብነት ይኾናል። ጽሑፉን የጻፈው ወደ ሮም ሄዶ ትምህርት ቤት ከከፈተ በኋላ ነበር። (Hammel, Handbook of Patrology, ፲፱፹፰, ፴፰.) በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያው ክፍል እንደ ተመለከተነው፤ ገዢው አንቶንዮስ ሕዝቡ እንዲያመልከው አዝዞ ነበር። ብዙዎች በፍርሃት ትእዛዙን ተግባራዊ አድርገውም ነበር። ይህን በተመለከተ የጻፈውን አውሳብዮስ ሲጠቅስ፤ "I think it is not out of place at this point to mention Antonius who d died so recently. Everyone was frightened into worshiping him as a god, though everyone knew who he was and where he came from." [በዚህ አጋጣሚ፤ በቅርቡ ስለሞተው አንቶንዮስ ብናገር ያለቦታው የገባ አይመስለኝም። ምንም እንኳ ሁሉም ሰው ማን እንደ ነበረና ከየት እንደ መጣ ቢያውቀውም እርሱ ግን እንደ ጣዖት ሊመለክ ፈልጎ ሰውን ሁሉ ሲያስፈራራ፣ ከዚህም የተነሣ ብዙዎች ሲፈሩ ነበር] በሚል አስቀምጦታል።

ይህ ነገር፤ መነሻውን ፍርሃትና የተለያየ ሰብአዊ ምክንያት አድርጎ እየተለመደ መጥቶ የነበረውን የገዥዎች መመለክ በሰፊው የሚመለከት ነበር። ምክንያቱ ምንም ቢኾን በቀላሉ ሊያልፈው አልፈለገም። ነገሮች ከምን ተነሥተው ወደ የት እንደሚያድጉ መገመት/ማስላት ለአንድ የቤተ ክርስቲያን ሰው ቀዳሚው ተግባሩ መኾን አለበት። ስለዚህም ሁሉም የሚያውቁት ሰው እንደኾነ ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸው ተከታዮቹ ገዥዎች ፊት (ማርቆስ አውሮሊዮስ) ያለ ፍርሃት አስተማረ።

የመጀመሪያውና ክርስትናን በሚጠብቅበት ጽሑፉ፤(- First Apology) ቤተ ክርስትያን የምትወነጀልባቸውን የሐሰት ውንጀላዎች እያነሣ ምላሽ ይሰጣል፣ የከሳሾችንም ሐሳብ ከንቱነት ያጋልጣል። ከመግቢያው ጀምሮ ለሮሙ ቄሣር "ከቅድመ ጥላቻ ወጥተህ የክርስቲያኖችን ጉዳይ በምክንያታዊነት ተመልከት" እያለ ይመክራል ይገሥፃል። እየተበደሉ ለሚከሰሱ ክርስቲያኖች ጥብቅና ቆሞ ይከራከራል። (Johannes Quasten, Patrology: Vol. I, ፻፺፱.)

**እነዚህም ክርስቲያኖችንና ትምህርታቸውን እንዴት ባለ ንቀት ይመለከት እንደ ነበረና ኋላ ግን፤ በሰማዕትነት ለመሞት የነበራቸውን ቁርጠኝነት፣ ፍቅራቸውንና መተባበራቸውን ስታዘብ መገረም ጀመርኩ።**

በኹለተኛው የዕቅበተ እምነት ጽሑፉ፤ ክርስቲያን በመኾናቸው ብቻ እና ክርስቲያን ነን፣ በክርስቶስ አምላክነት እናምናለን በማለታቸው በሠይፍ እንዲቀሉ የተደረጉ ሰዎችን እያነሣ መንግሥቱን ይሞግታል፡፡ ክርስቲያን መኾን የተለየ ወንጀል አለመኾኑን ይልቁንም ለፍትሐዊነት ለፍቅርና ሰላም መሠረት መኾኑን እያስረዳ ይከራከራል፡፡

ምሥጢረ ጥምቀትና ቊርባን በመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ውስጥ ለማይኖርና የምሥጢራቱ ተካፋይ ላልኾነ ሰው ምን ያህል የጸነኑ ጉዳዮች እንደኾኑ የታወቀ ነው፡፡ ይኹን እንጂ፤ በዘመኑ ከነበሩ ተቃዋሚዎች መካከል ሳይገባቸው የሚተቹ ብዙዎች ነበሩ፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ተገቢ የኾነውን ምላሽ በመስጠት በዋጋ የማይተመን አገልግሎት አበርክቷል፡፡

**ቤተ ክርስቲያን፤ ከሃይማኖታዊ ትምህርታቸው በተጨማሪ ቊሳውያን የሚመኩባቸውን የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች አጥንተው፣ የተደላደለ ዕውቀትና ጥበብ ይዘው የሚገኙ በርካታ ልጆች አሏት፡፡ ልዩነቱ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የማንንም የሐሳብ ድንበር ያለ ሥርዓት ጥሰው አይገቡም፡፡**

በዚህ አጋጣሚ በእኛም ሀገር በእኛው ዘመን ተመሳሳይ ነገሮች እየገጥሙ እንደኾነ ልብ ይሏል፡፡ አንዳንዶች በሕይወቱ ውስጥ ሳይኾኑ አልያም ሳይማሩና ሳይገባቸው ስለ ምሥጢራት በፖለቲካዊ ዐውድ አደባባይ ወጥተው ይናገራሉ፡፡ ዓላማቸው ወገንተኝነትን መሠረት ያደረገ ማጥላላትና በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ እንዲበረታ ብሎም ግጭትን የመቀስቀስ ቢኾንም በእነዚህ መረዳቶች ብቻ የማይታለፍ ሁሉን አቀፍ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ምላሹ በእምነት የምሥጢራትን ፋይዳ ለሚረዱት ወገኖች ብቻ ሳይኾን ከሳሾቹ ጭምር የቆሙበትን የሙያ መስክ እንዳላከበሩና እንዳልተረዱ የሚያጋልጥ መኾን ይገባዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን፤ ከሃይማኖታዊ ትምህርታቸው በተጨማሪ ቊሳውያን የሚመኩባቸውን የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች አጥንተው፣ የተደላደለ ዕውቀትና ጥበብ ይዘው የሚገኙ በርካታ ልጆች አሏት፡፡ ልዩነቱ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የማንንም የሐሳብ ድንበር ያለ ሥርዓት ጥሰው አይገቡም፡፡ ይህን ሥርዓት የሚያስከብር አገራዊ ሕግ የሚያስፈልግ ቢኾንም፤ በወረቀት የሰፈረው እንኳን ተግባራዊ ሲኾን አይታይም፡፡ ማለትም አንዱ ሲነቀፍ፣ ቤተ ክርስቲያንም ያልተገባ ስም ሲሰጣት፣ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ኾኖ ሲገኝ የተደመጡ የቤተ ክርስቲያን ድምፆች ከመጀመሪያው ጠብ አጫሪ በላይ ተጠያቂ ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ በዚህም በወቅታዊው የአገራችን ሁኔታ ውስጥ ያለውን አድሏዊነት በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ምቹ ያልኾኑ ሁኔታዎች የዕቅበተ እምነት አገልግሎትን ምክንያት ኾነው የሚያስቀሩ አለመኾናቸው በትኩረት ሊታይ ይገባዋል፡፡ ይልቁንም በቤተ ክርስቲያን ላይ የተቃጡ ጥፋቶች በበረከቱ ቊጥር አገልግሎቱም ሊሰፋ ይገባዋል፡፡ ከዮስጢኖስ የምንማራቸው ቁምነገሮች እነዚህ ናቸው፡፡

* ተዋሥኦ ምስለ ትሪፎን/ከአይሁዳዊው ትሪፎን ጋር የተደረገ ውይይት/Dialogue with the Jew Trypho

ክርስትና ለአይሁድ የሚሰጣቸው ምላሾች የተመዘገቡበት ጥንታዊ ጽሑፍ ይህ የዮስጢኖስ የዕቅበተ እምነት ጽሑፍ ነው፡፡ ከዮስጢኖስ ጋር የነበረው ተወያይ የአይሁድ መምህር እንደ ነበር ይነገራል፡፡ (Eusebius, The History of the Church, ፬፥፲፰.)

*ይቀጥላል!*

# የጮቢ መካነ ሕይወት በዓታ ለማርያም የአንድነት ገዳም

## እናስተዋውቃችሁ

*በዲ/ን ደረጀ ጋረደው*

## ፮. በገዳሙ የተከናወኑ ገቢረ ተአምራት

- ✞ በገዳሙ ለረጅም ጊዜ ያስቆጠረ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጠበል የሚገኝበት ሲሆን፤ በተጨማሪ ከቅርብ ዓመታት በፊት የበዓታ ለማርያም ጠበል ፈልቋል። አሁን ሁለቱም ጠበሎች በአንድ ላይ የሚፈሱ ሲሆን፤ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ ብዙ ድውያን ተፈውሰዋል እየተፈወሱም ይገኛሉ
- ✞ ጠበሉ ፈዋሽ እንደመሆኑ መጠን አላግባብ ለሚጠቀሙበት ሰዎችም ደም በመሆን ተአምራቱን ገልጿል።
- ✞ በጥንት ጊዜ ጫካው የሚጠበቀው በዳልጋ አንበሳ እንደ ነበር አባቶች ያስረዳሉ።

## ፯. በገዳሙ ተሠርተው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የልማት ውጤቶች

፯.፩.የእናቶች እና አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናት ማደሪያ

አንድ እናት ፫ እጓለ መውታ (የሙት ልጅ) ሕፃናትን በመንከባከብ እንዲያሳድጉ በማሰብ ፲፮ ክፍሎች ያሉት ባለ አንድ ፎቅ (G+1) ዘመናዊ ሕንጻ ተገንብቶ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ሲሆን የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ የገላ መታጠቢያ እና መጸዳጃ ቤቶችም የተሟሉለት ነው። እጓለ ማውታ (የሙት ልጅ) ሕፃናት ገብተው አገልግሎቱ መሰጠት ባይጀምርም ሕንጻው መናንያን እናቶችን በጊዜያዊ በዓትነት እያገለገለ ይገኛል።

### ፯.፪. ዘመናዊ የእህል ማከማቻ ጎተራ

የገዳሙ ዋና የገቢ ምንጭ እርሻ ነው። ከእርሻው የሚሰበሰበውን ምርት በጥንቃቄ ለማስቀመጥ ባለ አንድ ፎቅ (G+1) ዘመናዊ ሕንጻ ጎተራ ተገንብቷል። ጎተራው ፰ ክፍሎች ሲኖሩት እህሉ በላይኛው ፎቅ ይጨመራል። ለአገልግሎት ሲፈለግ በታችኛው ወለል በእያንዳንዱ የእህል ዘር ማስቀመጫ ቀዳዳ ክዳን በመክፈት በቀላሉ መውሰድ ይቻላል። ገዳሙ የተለያዩ የእህል አይነቶችን ማለትም ስንዴ፣ ጤፍ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ገብስ፣ ሽንብራ፣ እና በቆሎ የሚያመርት ሲሆን ፲፬ ጥማድ የእርሻ በሬዎችም አሉት። በተጨማሪም ሰብሉን ከአውድማ ወደ ጎተራ የሚያመላልስ ፩ ትራክተር አለው።

፯.፫. የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ እና ቤተ መጻሕፍት

የገዳሙ ዋና ችግር የመጠጥ ውኃ ነው። ችግሩ ከፍተኛ በመሆኑ ውኃ ይቆነናል። ችግሩን ለማቅለል የተወሰደው እርምጃ ከጠበሉ ጎን የሚመነጭ ውኃ በማጠራቀም አገልግሎት ላይ እንዲውል ይደረጋል። ይህንንም የሚያግዝ ፴፻ (ሦስት መቶ ሺህ) ሊትር የሚይዝ የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ በግንብ መሬት ላይ ተገንብቶ ሥራ ጀምሯል። ከውኃ ማጠራቀሚያው ላይ የተገነባው የላይኛው ቤት ፶ ሰዎችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ ዘመናዊ ቤተ መጻሕፍት እና ለገድል ማንበቢያ እንዲሆን ታስቦ የተሠራ ነው። ቤተ መጻሕፍቱም መናንያን፣ የአብነት ተማሪዎች ጠበልተኞች እና የዕረፍት ጊዜያቸውን በገዳም የሚያሳልፉ ምእመናን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች የሚገለገሉበት ይሆናል።

### ፯.፬. ለሕሙማን አገልግሎት የሚሰጥ ጠበል

ቀደም ሲል ከተለያዩ ቦታ የሚመነጩ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጠበል የነበረ ሲሆን ኃይል ከማጣቱ የተነሣ ሕሙማን በሚገባ መጠበል አይችሉም ነበር። ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ጠበሉን ከዋናው ምንጭ በማቆር እና በማጠራቀም በኃይል እንዲወርድ ተድርጓል። አሁን ምእመናን ሳይሳቀቁ በኃይል የሚወርድ ጠበል ይጠበላሉ። ሕሙማን ከተጠበሉ በኋላ በፍሳሽ መልክ የሚወርደው ማይ አይባክንም። በውኃ ማስተላለፊያ ቧንቧ ተጠልፎ ለግንባታ አገልግሎት ይውላል። በገዳሙ ውስጥ የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉት ሕንጻዎች በሙሉ በዚሁ ከጠበል በሚወርደው ውኃ በመጠቀም ነው።

### ፳.፭.ዘመናዊ የወተት ላም ፕሮጀክት

ዘመናዊ የወተት ላም እርባታ በገዳሙ በጥቂቱ የተጀመረ ሙከራ ያለ ሲሆን ይህን ተሞክሮ ለማስፋት ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል። በዚህም ፴ የፈረንጅ ላሞችን የሚይዝ ዐሥራ ዐራት በሃያ ካሬ ዘመናዊ ቤት ተገንብቶ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆኗል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የወተት ማቀነባበሪያም ለመገንባት በረጅም ጊዜ ዕቅድ ተይዟል። ከእነሱ በሚወጣው እበት የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂም የሚሠራ ይሆናል። ለዚህ ዕቅድ መሳካት ዋነኛው በቂ የውኃ አቅርቦት ሲኖር ነው። ይህንንም  ችግር ለመፍታት ገዳሙ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

### ፳.፮.የተግባር ቤት

ገዳሙ ሲመሠረት አብሮ የተገነባው ተግባር ቤት ብዙ ዓመታት አገልግሎት በመስጠቱ አርጅቶ ወደ መፈራረስ ተቃርቧል። አስቀድሞ ሲሠራም አካባቢውን ያገናዘበ ባለመሆኑ በጪስና በሙቀት በመታፈኑ ለተግባር ቤት አገልጋዮች ፈተና ነው። የአካባቢውን የአየር ንብረት ያገናዘበ፣ ብዙ አገልጋዮች ማስተናገድ የሚችል፣ መናንያን የአብነት ተማሪዎችንና ወደ ገዳሙ የሚመጡ ምእመናን የሚያገለግል አዲስ ተግባር ቤት መሥራት አስፈልጓል። ይኅንንም ታሳቢ ያደረገ ተገንብቶ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆኗል።

## ፳. ግንባታቸው ያልተጠናቀቁ ሕንጻዎች

ገዳሙ ብዙ የልማት ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ይኽም ከላይ ያየናቸው የተለያዩ ግንባታዎች ዋናዎቹ ሲሆኑ ወደፊት የሚጠናቀቁ ግንባታዎች የሚከተሉት ናቸው።

### ፳.፩. የእናቶች በዓት

ገዳሙ የአንድነት ገዳም ቢሆንም የእናቶች እና የአባቶች በዓት መለያየት እንደሚገባ የገዳሙ መተዳደሪያ ደንብ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ፲፰ ክፍላትን የያዘ ሙሉ መገልገያ የሚሟላለት ሕንጻ በመገንባት ላይ ይገኛል።

### ፳.፪. የስብከተ ወንጌል አደራሽ

ለገዳሙ ከሚያስፈልጉት መሠረተ ልማቶች መካከል የስብከተ ወንጌል አዳራሽ አንዱ ነው። የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ይሰጣል። ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች መማሪያ ለመንፈሳዊ ጉባኤያት፣ ለእንግዶች መቀበያ እና ማረፊያ ያገለግላል። ገዳሙም ችግሩን ለመፍታት በማሰብ በአንድ ጊዜ ፲፻ (አንድ ሺህ) ምእመናንን ማስተናገድ የሚችል አዳራሽ እያስገነባ ይገኛል።

### ፳.፫. ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን

አሁን ያለው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ገዳሙ ሲመሠረት የተገነባ ሲሆን ከዕድሜ መጨመር እና የአካባቢው ማኅበረሰብ እየበዛ መሄድ በተፈለገው መጠን ምእመናኑን ማስተናገድ አልተቻለም። የገዳሙ አስተዳደር አዲስ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መገንባት አስፈላጊ መሆኑን ካመነበት በኋላ ፲፱ ሚሊየን የሚገመት አዲስ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መገንባት ተጀምሯል።

## ፱. የገዳሙ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች

ገዳሙ ከመናንያኑ ጀምሮ በርካታ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ያሉት ሲሆን ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፡-

- ✞ የይዞታ ማረጋገጫ ያለው ፹፩.፸፱ (ሰማንያ አንድ ነጥብ ሰባ ዘጠኝ) ሄክታር የእርሻ መሬት
- ✞ በናፍታ የሚሠራ ሁለት የእህል ወፍጮ
- ✞ ሰዎችን፣ እቃንና ምርትን ከቦታ ቦታ የሚያመላልስ ትራክተር
- ✞ የብሎኬት ማምረቻ ማሽን
- ✞ የሲሚንቶ ማቡኪያ ሚክሰር
- ✞ አርማታ ማዋሐጃ ቫይብሬተር
- ✞ ከሙአለ ሕጻናት እስከ ፬ኛ ክፍል አገልግሎት እየሰጠ ያለ ት/ቤት
- ✞ ፳፰ የእርሻ በሬዎች
- ✞ ፶፪ የሐበሻ እና የፈረንጅ ላሞች
- ✞ ፯ አህዮች
- ✞ ተገንብተው የተጠናቀቁ እና በመገንባት ላይ ያሉ ሕንጻዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## ፲. ገዳሙ ለአከባቢው ማኅበረሰብ እየሰጠ ያለው አገልግሎት

በማንኛውም ደዌ ተይዘው ወደ ገዳሙ ለሚመጡ ምእመናን የጠበል አገልግሎት የሚደረግባቸው ሲሆን ጠበልተኞች የማረፊያ ቦታ ይመቻችላቸዋል በቆይታቸውም መቁነንት ከመናንያን ጋር ይጣሰቸዋል።

ለአከባቢው ማኅበረሰብ በተለይ በገዳሙ ዙሪያ ለሚኖሩ ምእመናን ማንኛውም ችግር ሲገጥማቸው ገዳሙ ይደርስላቸዋል። ለአብነት ያህልም ዘር ሲያጥራቸው ዘር ይሰጣል፣ ከገዳሙ የእርሻ መሬት በየዓመቱ በቂ ምርት የሚሰበሰብ በመሆኑ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ባሻገር ለተለያዩ ገዳማትም የቀለብ እገዛ ይደረጋል። በገበያ ቀን ከገዳሙ እስከ ዋናው መንገድ ፲ ኪ.ሜ. በእቃ ማጓጓዣ ትራክተር የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል፣ በበጋ ወቅት የውኃ እጥረት ሲኖር የመጠጥ ውሃ ያከፋፍላል፣ የወፍጮ አገልግሎት በቅናሽ ዋጋ፣ አቅም ለሌላቸው ደግሞ በነጻ ይፈጫል፣ በኬላ ከተማ ከሙአለ ሕፃናት እስከ ፬ኛ ክፍል በከፈተው ት/ቤት በአከባቢው ካሉ የግል ት/ቤቶች በተሻለና ዝቅተኛ ክፍያ ማለትም በአንድ ተማሪ ፲፱ ብር በማስከፈል ያግዛል፤ እጓለ ማውታ (የሙት ልጅ የሆኑ) ሕጻናትን ያሳድጋል።

አካባቢው የገጠር ቀበሌ በመሆኑና ጥርጊያ መንገድ ባለመኖሩ አርሶ አደሩ ምርቱን ወደ ገበያ ለመውሰድ፣ ሰው ሲታመምበት ወደ ሕክምና ለማድረስ ከፍተኛ ችግር ነበር። ገዳሙም ይህን በመረዳት በራሱ ወጪ ፲ ኪ.ሜ. መንገድ በማስጠረግ እና ከዋናው መንገድ ጋር በማገናኘት የተጠቀሱ ችግሮችን መፍታት ችሏል።

## ፲፩. ወደፊት ሊሠሩ የታሰቡ ግንባታዎች

- ✞ እያንዳንዱ ፳፬ ክፍሎች ያሉት ባለ አንድ ፎቅ (G+1) የተለያዩ ፫ ሕንጻዎች የካህናት ቤት
- ✞ ዕቃ ቤት
- ✞ ምርፋቅ (የመመገቢያ አዳራቀሽ)
- ✞ የወንድ ተግባር ቤት
- ✞ የእደ ጥበባት ማእከል (የእንጨት ሥራ፣ የብረታ ብረት ሥራ፣ የሽመና ሥራ)
- ✞ የአብነት ትምህርት ቤት ግንባታ
- ✞ የከርሠ ምድር ውኃ ቁፋሮ
- ✞ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## ፲፪.ገዳሙ ላይ ያለው ተግዳሮት

ገዳማዊ ሕይወት በራሱ ከፈተና ያልተለየ ሕይወት ቢሆንም ከላይ ካየናቸው ሰፋፊ የልማት ሥራዎች አንጻር የገዳሙ ዋና ፈተና የመናንያን ፍልሰት ነው። ወደ ገዳሙ ለሚመጡ መናንያን ልዩ አቀባበል ቢደረግላቸውም በገዳሙ ውስጥ ከሚከናወኑ በርካታ ተግባራት እና የጉልበት ሥራዎችን በመስላቸት አብዛኛዎቹ መናንያን ለመቆየት ፈቃደኛ አይደሉም።

## ፲፫. መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ

ለመናንያን ፍልሰት መፍትሔ ሊሆን የሚችለው በዋናነት አጽንኦ በዓት ሲሆን ይህም የሚሆነው አግዚአብሔር ሲፈቅድ እና ሲያጸና መሆኑ በእርግጥ ይታወቃል። ይሁን እንጂ እንደ ሰው ሰውኛ መናንያን በበዓታቸው እንዲጸኑ የተለያዩ ሥልጠናዎች መሥጠትም አንድ መፍትሔ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ የምንኵስና ሕይወት ያሉት ፈተናዎች እና የሚየሰጠው ጸጋ፣ አጽንኦ በዓት እና ሌሎች ተዛማች ሥልጠናዎች ለመናንያን ቢሰጣቸው ያሉትን ችግሮች ሙሉ በሙሉ መፍታት ባይቻልም የመናንያንን ፍልሰት በትንሹ መቅረፍ ይቻላል። በተጨማሪም አዲስ ለሚመጡ መናንያን ከነባሩ ጋር መጓዝ ለማይችል አንድ ጊዜ ቀኖና ከመጫን ደረጃ በደረጃ እንደ ቆይታው መጠን እንዲለማመደው ቢደረግ እንዲሁም ተተኪ መናንያን ለማፍራት ሁሉም ገዳማት እና መናንን ዐቅደው መሥራት እንዳለባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት።

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት በዱግዳ ቦራ ወረዳ የሚገኘውን የመካነ ሕይወት ጮቢ በዓታ ለማርያም አንድነት ገዳምን ከሚገኝበት ቦታ በመነሣት መቼ እንደተመሠረተ፣ ከተመሠረተበት ጀምሮ ያከናወናቸውን ተግባራትና የገዳሙን ታሪክ በአሁኑ ሰዓት ገዳሙ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ ከረጅሙ በዐጭሩ አቅርበናል። እግዚአብሔር አምላክ ከገዳሙ በረከት ያድለን አሜን

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

ክፍል አንድ

የጥያቄዎቻችሁ መልስ

በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን



መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ

*ውድ አንባብያን በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዐምዳችን የትዳርንና ትዳር የሚፈርሱባቸውን ምክንያቶች በተመለከተ የሚነሡ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን ምላሽ ይሰጡን ዘንድ* ***በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በምሥራቀ ፀሐይ ቀበና መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል አገልጋይ የሆኑትን መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰን ጋብዘናል። መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቴሌቪዥን መርሐ ግብር አዘጋጅም ናቸው።*** *ፈቃደኛ ሆነው ከቦታችን ተገኝተውልን ቆይታችንን እንዲህ አዘጋጅተነዋል፤ መልካም ንባብ።*

***ሐመር፡-*** መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰን ትዳርንና በትዳር መካከል የሚነሡ ችግሮችን መሠረት ያደረጉና በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚነሡ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን ለምናነሣቸው ሐሳቦች ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለ ሆኑልን አስቀድመን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

***፩. ሐመር፡-*** ትዳር ማለት ምን ማለት ነው?

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** ትዳር፡- ብዙ አጥኚዎች፣ በጋብቻ ዙሪያ የጻፉና የሰበኩ መምህራንም በተለያየ መልኩ ገልጸውታል። እኔ በአለኝ መረዳት ሁለት ተጋቢዎች አንድ ወንድና አንዲት ሴት በጋብቻ አንድ የሚሆኑበት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። በሌላ አገላለጽ ደግሞ ሀብት ንብረት ማፍራት፣ ልጆች ወልዶ፣ በአንድነት ቤተሰብ መሥርቶ መኖር ትዳር ይባላል። አንዳንድ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ትዳር ሀብት ንብረት ተብሎ ተገልጾ እናገኛለን። ተጋቢዎች ሀብት ንብረት አፍርተው የሚኖሩበትን ሕይወት ያስረዳል። ለምሳሌ "ከዐሥራ ሁለት ዓመትም ጀምሮ ደም የሚፈስሳት ሴት ነበረች፤ ትዳሯንም ሁሉ ለባለ መድኃኒቶች ሰጥታ ማንም ሊፈውሳት አልተቻለውም ነበር" (ሉቃ.፰፥፵፫) ተብሎ ተጽፎ እንደምናነበው ትዳር ሀብት ንብረት ተብሎ ተገልጾአል። በአጠቃላይ ትዳር አንድ ወንድና አንዲስ ሴት በጋብቻ ተጣምረውና ጎጆ ቀልሰው የሚኖሩበት የአንድነት ኑሮ ማለት ነው።

***፪. ሐመር፡-*** ትዳር በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እይታ እንዴት ይገለጻል?

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** ትዳር (ጋብቻ) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ቅዱስና ክቡር ነው ተብሎ ይገለጻል። አስቀድሞ መሥራቹ ልዑል እግዚአብሔር ነው። ፈጻሚዎቹ ደግሞ የሰው ልጆች ናቸው። እግዚአብሔር የባረከው፣ የቀደሰውና ሕግ አድርጎ የሰጠው ሁሉ መልካም ነው። አንድ ወንድና አንዲት ሴት በፍቅር ላይ ተመሥርተው የሚመሠርቱት ጋብቻም

ቅዱስ ነው፡፡ ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ ጋብቻን ባርኮ የሰጠ እግዚአብሔር ነው፡፡ የሰው ልጅ ዕድሜው ሲደርስ በቅዱስ ጋብቻ ወይም በምንኵስና እንዲኖር ይመከራል፡፡ ሱባኤ ገብቶ፣ ልቡን መርምሮ፣ ካህናትን አማክሮ አንዱን ሕይወት ይወስናል፡፡ ስለዚህ በየትኛውም ሕይወት ማለትም በጋብቻም ሆነ በምንኵና ሕይወት መኖር የተቀደሰና የተባረከ ነው፡፡

አስቀድሞ የተመሠረተው በእግዚአብሔር ስለሆነ ዛሬም ራሱን መርምሮ ከካህን ጋር ተመካክሮ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቆ በትዳር እንዲወሰን መጽሐፍ ቅዱስ ይመክራል ያስተምራል፡፡ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በማስተማር ዘመኑ የመጀመሪያውን ተአምር በቃና ዘገሊላ ተገኝቶ በሰርግ ቤት ማድረጉ ጋብቻ የተባረከ መሆኑን ያሳየናል፡፡ እንዲሁም አስቀድሞ "ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚረዳውን ጓደኛ እንፍጠርለት እንጂ" (ዘፍ.፪፥፲፰) በማለት የተናገረውን አምላካዊ ቃል ሕግ አድርጎ እንደሰጠን ሁሉ በማስተማር ዘመኑም ‹‹ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል፤ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ፡፡ እንኪያስ ሁለት አይደሉም፤ አንድ አካል ናቸው እንጂ፤ እግዚአብሔርም አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ" (ማቴ.፲፱፥፭-፮) ብሎ ማስተማሩ ትዳር ቅዱስ መሆኑ ይገልጻል፡፡

እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ትዳር ክብረ ንጽሕናቸውን ጠብቀው እስከ ጋብቻቸው በድንግልና ለኖሩ በተክሊል፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ድንግልናቸውን ሳልጠበቁ ንስሓ ገብተው፣ በቁርባን በመንፈሳዊ ሥርዓት ሲፈጸም ቅዱስ፣ ክቡር ነው፡፡ ልዩ ልዩ ምክንያቶች የተባሉትም በሞት፣ በዝሙትና በመሳሰሉት እንደ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ ትእዛዝ ድጋሜ ጋብቻ ለሚፈጽሙት በመዓስብ ሥርዓት ይፈጸማል፡፡ ማሳረጊያው ግን ቅዱስ ቍርባን ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በንስሓና በመንፈሳዊ ሥርዐት የሚፈጸም ጋብቻ ክቡር ነው፤ ቅዱስ ነው፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለበት ነው፤ እያለች ትመሰክራለች፡፡

ጋብቻ ቅዱስ የሚሆነው በመንፈሳዊ ሥርዐት ሲፈጸም ብቻ ነው፡፡ ሰው ሁሉ የሥላሴ ፍጡር ነው፡፡ ሰው ሁሉ ግን ቅዱስ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ይህም ቅድስና የተለየ ተጋድሎ ስለሚጠይቅ ነው፡፡ ተራሮች ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጥረታት ናቸው፡፡ ግን ተራሮች ሁሉ መሥዋዕት አይሠዋባቸውም፡፡ ቦታዎችን ሁሉ ቅዱሳት መካናት፣ አድባራትና ገዳማት አንላቸውም፡፡ ታቦተ ሕጉ ያለበትን፣ ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበትን ቅዱሳን ከሰብአ ዓለም ተለይተው ዕድሜ ልካቸውን የጸለዩበትን፣ ሱባኤ የገቡበትን፣ ቃል ኪዳን የተቀበሉበትን፣ ወዘተ ቅዱሳት መካናት፣ አድባራትና ገዳማት እያልን እንጠራቸዋለን፡፡ ከተራራ መርጦ በገዳመ ቆሮንቶስ ጾምና ጸሎት እንደያዘ፣ በደብረ ሲና ጽላተ ኦሪትን እንደሰጠ፣ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን እንደገለጠ ሁሉ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን፣ በንስሓ ሕይወት፣ በመንፈሳዊ ሥርዐት በቅዱስ ቍርባን የተፈጸመ ጋብቻ ቅዱስ ነው፤ ክቡርም ነው፡፡

**ጥ. *ሐመር፡-*** እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ባልና ሚስት እንዴት ይገለጻሉ? በምንስ ይመሰላሉ?

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** ባልና ሚስ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንዴት ይገለጻሉ በምንስ ይመሰላሉ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በኦሪቱ ነቢያት የእስራኤልንና የእግዚአብሔርን ግንኙነት እንደባልና ሚስት መስለው አስተምረውበታል፡፡ እስራኤል ከሕገ እግዚአብሔር ፈቀቅ ባሉ ጊዜ ጋለሞታ ተብለው ተሰድበዋል፡፡ በድንቅ አጠራሩ ጠርቶ፣ በቸርነቱ ረድቶ ከብዙ መከራ የታደጋቸው ሲበድሉ ግን እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ ላይ አድሮ የተናገረውን እንመልከት፡፡

ከዳተኛይቱ እስራኤል ያደረገችውን አየህን ወደረዘመው ተራራ ሁሉ ወደለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች ሄደች፤ በዚያም አመነዘረች፡፡ ይህንም ሁሉ ካደረገች በኋላ ወደእኔ ተመለሽ አልኋት፤ ነገር ግን አልተመለሰችም፤ አታላይ እህቷ ይሁዳም አየች ከዳተኛይቱ እስራኤል እንዳመነዘረች አየሁ፡፡ የፍችዋንም ደብዳቤ በእጅዋ ሰጥቼ ሰደድኋት ጎስቋላ እህቷ ይሁዳ ግን በዚያ አልፈራችም፤ እርሷም ደግሞ ሄዳ አመነዘረች ዝሙቷም ከንቱ ሆነ፤ እርሷም ከድንጋይና ከግንድ ጋር አመነዘረች በዚህም ሁሉ ከዳተኛይቱ ይሁዳ በሐሰት እንጅ በእውነት ወደእኔ አልተመለሰችም፡፡ (ኤር. ፫፥፮-፲)

ጋለሞታ ማለት ባል ፈትታ የምትኖር ሴት ማለት ነው፡፡ እስራኤል ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወጥተው በአምልኮተ ጣዖት ወይም ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጭ ሆነው መኖር በጀመሩ ጊዜ ባሏን የፈታች ሴት ተብለዋል፡፡ ባልና ሚስት

አይለያዩም፤ የሰው ልጅም ከአምልኮተ እግዚአብሔር ሊወጣ አይገባውም። አለዚያ ግን ጋለሞታ ወይም ባል አልባ ወይም ሚስት አልባ ይባላል። ስለዚህ እስራኤል ከአምልኮተ እግዚአብሔር በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር አምላካችን በነቢዩ በኤርምያስ ላይ አድሮ "ጋለሞታ" በማለት ገሥጻቸው።

ነቢዩ እግዚአብሔር በእስራኤል ስለመገለጡ፣ በእስራኤል ድንቅ ምሥጢር ስለማድረጉ እነርሱን እየመገበ በእነርሱ እየተመሰገነ መኖሩን እግዚአብሔር እንደ ባል እስራኤል እንደሚስት ሆነው ቅርርባቸውን የሚያሳይ ነው። ይህም ትዳር መንፈሳዊና ሰማያዊ ምሥጢር ያለው መሆኑን ነው የሚያሳየው።

በሐዲስ ኪዳን ደግሞ የበለጠ ይልቅም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባልና ሚስትን ይልቁንም በፍቅር የሚዋሐዱ አንድ ወንድና አንድ ሴትን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መስሎ አስተምሯል። ይህንም በኤፌሶን መልእክቱ ‹‹ዐቢይ ውእቱ ዝ ነገር፤ ወአንሰ እብሎ ላዕለ ክርስቶስ ወላዕለ ቤተ ክርስቲያኑ፤ ይም ምሥጢር ታላቅ ነው፤ እኔም ይህንኑ ስለክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያኑ እናገራለሁ›› (ኤፌ.፭፥፴፪) በማለት የምሥጢሩን ታላቅነትና ባልና ሚስት ሊኖሩበት የሚገባውንም ልዩ የአኗኗር ምሥጢር በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መስሎ አስተማረ። ከላይም እንዲሁ "ወንዶችም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ራሱንም ስለ እርስዋ ቤዛ አድርጎ እንደሰጠላት ሚስቶቻቸውን ይውደዱ" ይላል። (ኤፌ.፭፥፳፭) ይህ ማለት ሴትም ለባሏ ትገዛ ባልም ሚስቱን ይውደዳት በማለት ነው።

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደዳት እስከሞት ድረስ ነው። ባልም ሚስቱን እስከሞት ድረስ ሊወዳት ይገባል። ሚስትም ለባሏ ትገዛ ሲል ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ በፍቅር እንዳምትገዛ ሁሉ ሚስት ለባሏ በፍቅር ትገዛ ሲል አስተምሯል። ቤተ ክርስቲያን ስንል ማኅበረ ምእመናንን ማለታችን ነው። ማኅበረ ምእመናን የሚጸሙት፣ የሚጸልዩት፣ ንስሓ የሚገቡት ተገደው አይደለም። ካህናቱ አስገድደዋቸው ገዝተዋቸው አይደለም። በራሳቸው ፈቃድ ነው። ደስ ብሏቸው የሚያደርጉት ነው። አጽዋማቱ መጡ፣ ብለው ሊጾሙ የሚዘጋጁት፣ በዓላቱ መጡ ብለው ገንዘባቸውን አውጥተው ሊያከብሩ የሚዘጋጁት፣ ዐሥራት በኩራታቸውን የሚያወጡት እግዚአብሔርን ወደው ነው። ስለዚህ ሴት ለባሏ የምትገዛ በፍቅር ነው። ባልም ከመውደድ አልፎ ይሙትላት ተብሏል። እንግዲህ ክርስቶስ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ ባልም ራሱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ የሚወዱትና ሁለቱም በጽኑ ፍቅር የሚኖሩበት ስለሆነ ባልና ሚስት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ተመስለዋል።

በሌላ አንቀጽ እንደ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው የሚኖሩ ናቸው። ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው ሰው የሚለውንና በሰብእና የሚገልጸው ነገር እንደሚያስገኙት ሁሉ ባልና ሚስትም በአንድነት ተዋሕደውና ተስማምተው የመኖር ድንቅ ምሥጢር እንዳለው በልዩ ልዩ የሊቃውንት መጽሐፍ እንረዳለን። ክብር ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አንድ አካል ናቸው በማለት ድንቅ ቃል ተናገረ። አንድ አካል ናቸው ሲልም ለምሳሌ፦ ማንም አካሉን እንደሚወድ ሁሉ ከአካሌ ላይ ይቆረጥ፣ ከእግሬ ላይ ይቆረጥ እንደማይል ሁሉ በሌላ አገላለጽም ቅዱስ ጳውሎስ "ሚስቱንም የሚወድ ራሱን ወደደ" (ኤፌ.፭፥፳፰) እንዳለ ሁሉ ባል የሚስት አካል ነው ሚስትም የባል አካል ናት። ማንም ሰው ለዐይኑ እንደሚሳሳ እንዲሁ አንዷት ሴት ለእጇ፣ ለእግሯ፣ ለሰውነቷ ሌላው ቀርቶ ለጌጣጌጧ እንደምትሳሳ ሁሉ ባሏንም እንደሰውነቷ እንደ አካሏ እንድታይ ጌታችን መድኃኒታችን አንድ አካል ናቸው ያለውን መሠረት አድርገው ሐዋርያትና ሊቃውንት ተንትነውታል።

**ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደዳት እስከሞት ድረስ ነው። ባልም ሚስቱን እስከሞት ድረስ ሊወዳት ይገባል። ሚስትም ለባሏ ትገዛ ሲል ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ በፍቅር እንዳምትገዛ ሁሉ ሚስት ለባሏ በፍቅር ትገዛ ሲል አስተምሯል። ቤተ ክርስቲያን ስንል ማኅበረ ምእመናንን ማለታችን ነው።**

ለምሳሌ፡- ቅዱስ ጳውሎስ በ (፩ቆሮ.፯፥፬) ላይ "ሚስት በራስዋ አካል ሥልጣን የላትም፤ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ባል በራሱ አካል ሥልጣን የለውም፤ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ" ሲል በእርሱ አካል ላይ ሚስት ሥልጣን አላት። በሚስት አካል ላይ ባል ሥልጣን አለው። ይህም አንድ አካል ናቸው የሚለውን ይበልጥ እንድንረዳው የሚያስገነዝበን ነው። ራስ ወዳድነት የሚጠፋበት፣ መዋደድ፣ መተሳሰብ፣ ባል ለእኔ ሳይሆን ለእርሷ የሚልበት፣ ሚስትም ከራሷ ይልቅ ለባሏ የምታስብበት፣ የባል ችግር ለሚስት፣ የሚስትም ችግር ለባል፣ የባል ደስታ ለሚስት፣ የሚስትም ደስታ ለባል፣ የሚሆንበት ነው። በአንድ የሰውነት ክፍል መታመም የትኛውም የሰውነት ክፍል ምቾት አይስማማውም። ለምሳሌ፡- እግር ቢታመም መላውን ሰውነቱን እንደ ሕመም ይሰማዋል። ይህ ሁሉ የማይነጣጠል ጽኑ አንድነት ያለበት በእስራኤልና በእግዚአብሔር በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን፣ በነፍስና በሥጋ የተመሰለ መሆኑን ያስረዳናል።

***፬. ሐመር፡-*** በዚህ ዘመን የትዳር መፍረስ እየተስፋፋ እንደሆነ ይስተዋላል። ለትዳር መፍረስ ምክንያቶች ናቸው ብለው ከሚያስቧቸው መካከል የተወሰኑትን ቢገልጹልን?

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** ለትዳር መፍረስ ምክንያት የሚሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። አንዳንዶች እንደ እግዚብሔር ፈቃድ በሽምግልና ከመፍረስ ሲድኑ አንዳንዶቹ ደግሞ በየፍርድ ቤቱ ሰማንያችን ይቀደድልን ብለው ሲሄዱና ትዳራቸውንም ሲያፈርሱ ይስሠተዋላል። ለዚህ ሁሉ ችግሮችና የችግሮቹን ምንጮች ስናነሣ እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምሮ ከመጀሪያው ለመነሣት፡-

***፩. በጠላት ዲያብሎስ ፈተና፡-*** ጠላታችን ዲያብሎስ በዙሪያችን ሆኖ የእኛን መሰናከልና መውደቅ ይጠባበቃል። በመሆኑም በሥጋ ወደሙ፣ በንስሓ ሕይወት፣ በአጠቃላይ በጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት ከብረው የኖሩትን ባልና ሚስቶች ሳይቀር መርዙን እየረጨ ሊፈትናቸው ይችላል። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ "እንግዲህ ዐዋቂዎች ሁኑ ትጉም፤ ጠላታችሁ ጋኔን የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና" (፩ጴጥ.፭፥፰) በማለት እንደገለጸው ዲያብሎስ እኛን ለመጣል ስለማያርፍ በዚህ ምክንያት ሊፈርስ ይችላል።

***፪. በራስ ደካማ ጐን፡-*** ይህ ሲባል በባል ወይም በሚስት በኩል ባለ ድክመት፣ ራስን ለይቅርታ ባለማዘጋጀት በማይረባ ምኞት በመጠለፍ ፈተናቸው እየጠነከረ ሲሄድ ይስተዋላል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ "የሚፈተን ሰው ቢኖር እግዚአብሔር ይፈትነኛል አይበል፤ እግዚአብሔር ለክፉ ነገር አይፈትንምና፤ እርሱ ማንንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ምኞት ከፀነሰች ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ከተፈጸመች ሞትን ትወልዳለች" (ያዕ.፩፥፲፫-፲፭) በማለት እንደተናገረው ክፉ ምኞታችን ለራሳችን የሕይወት መሰናክል ይሆናል።

እንዲሁ ይህው ሐዋርያ ‹‹በእናንተ ዘንድ ጥልና መጋደል ከወዴት ይመጣሉ? በሰውነታችሁ ውስጥ የሚሠራውን ዝሙት ከመውደድ የተነሣ ከዚህ አይደለምን? ትመኛላችሁ እንጂ አታገኙም፤ ትቀናናላችሁ፤ ትገዳደላላችሁ፤ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፤ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ፣ ትዋጉማላችሁ፤ ነገር ግን አትለምኑምና የምትፈልጉትን አታገኙም፤ ትለምናላችሁ ለፍትወታችሁ ትከፍሉ ዘንድ ለክፉ ትለምናላችሁና አታገኙም" (ያዕ.፬፥፩-፫) በማለት እንደተናገረ ከራሳችን ክፉ ምኞት፣ ጸሎት አለማድረግ፣ ብናደርግም እንኳን ለመልካም ነገር ሳይሆን ለክፉው ነገር ስለምንለምን መልካሙን አታገኙም ተባልን። ስለዚህ ራሳችን ያለመገንዘብ፣ ራሳችን ለትዳራችን በአግባቡ ካለመጸለይ፣ ወዘተ ከመሳሰሉት ሁሉ ለትዳር መፈታት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ይኖራሉ። ሌሎቹንም ብዙ ጊዜ ለትዳር መፍረስ ምክንያት የሚሆኑትን የተወሰኑትን ለመጥቀስ ልሞክር፡-

***፫. ሳይተዋወቁ መጋባት፡-*** ቀድሞ በሁለቱም በኩል ያለውን ጠንካራና ደካማ ጐን ሳይጠናኑ በችኮላና በአንዳንድ ጊዜያዊ ስሜቶች ወስና የሚገቡበት ትዳር በኋላ ለሚፈጠረው የሐሳብ መለያየት "ሳላውቀው ነው፤ ሳላውቃት ነው" መባባል ላይ ስለሚደርሱ የፍች ምክንያት ሲሆን ይታያል። በእርግጥ ሰው ተጠንቶ አያልቅም። ይሁን እንጂ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ግን መሠረታዊ የሆነ ግንዛቤ በሁለቱም በኩል ሊኖር ይገባል። ይህ ሳይሆን ይቀርና መጋባታቸው ከመስማቱ መፋታታቸው የሚሰማ ባልና ሚስቶች እየተበራከቱ መጥተዋል።

***፬. ስለ ሦስተኛ ወገን ሳያስቡ መጋባት፡-*** ይህ ማለት ስለ ልጅ፣ ስለ እናትና አባት፣ ስለ ቤተ ሰብ፣ ስለማኅበራዊ ኑሮ ወዘተ ሳያስቡ መጋባት የሚያስከትለው ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ ከተጋቡ በኋላ ልጅ እንውለድ አንውለድ ተባብለው የሚጋጩ አሉ፡፡ በሥራ ጠባይ፣ በሀብት እጥረት፣ በትምህርት ወዘተ ሰበብ ሲሉ ለመውለድ አንዱ ሲፈልግ ሌላኛው ሳይፈልግ ግጭት ይፈጠራል፡፡ ይህ ደግሞ ገና መጀመሪያ ሲጋቡ "ሰነፈች፣ ደከመች፣ መከነች፣ ጠቆረች፣ ከሳች፣ ወዘተ" ብዬ ላልፈታት የሚለውን ቃል ኪዳን ልብ አለማለትን ያስረዳል፡፡ ከጋብቻ በኋላ ገንዘቡ ሲቀንስ፣ ውበቱ ሲቀንስ፣ ታዋቂነቱ ሲቀንስ ወዘተ የጠባይ መለዋወጥ የፍቅር መቀነስ ይከሠታል፡፡ "ራስን መተው፣ ራስን መካድ" የሚለውን ይዘነጉትና በሐሳብ ለመለያየታቸው መሠረታዊ ጉዳይ ባልሆነው ሁሉ ሲጋጩ ይስተዋላሉ፡፡ ይህ ሁሉ ትርጉም ሲያጣ ፍቺ ይከሠታል፡፡

***፭. ሀብትን መሠረት አድርጐ መጋባት፡-*** በዚህ ዓለም ሲኖሩ ሀብት ንብረት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ቀዳሚ ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡ ሀብትን መሠረት አድርጐ መጋባት ሀብቱ እየጐደለ ሲሄድ ቤት ላይ በሚጐድሉ ነገሮች መለያየት፣ መጨቃጨቅ ይጀምራሉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ሀብት ቢኖርም ሀብት ለጊዜው እንጂ ዘላቂ ፍቅርን አይሰጥም፡፡ ሲያውቁበት እንጂ ሳያውቁበት መንግሥተ ሰማያትንም ለመውረስ ፈተና ይሆናል፡፡ መድኀኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ "ገንዘብ ላለው ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነው?" (ማር.፲፥፳፫) በማለት ያስተማረው ወደ ሰማያዊውና ወደ ዘለዓለማዊው ዓለም ለመግባትም መሰናክል የሞሆንበት አጋጣሚ ስላለ ነው፡፡ ደግሞም በገንዘቡ እናገኘዋለን ብለው የጠበቁት ነገር አልገኝላቸው ሲል ትዳራቸውን ይፈታሉ፡፡

***፮. አለመተማመን፡-*** በመካከላቸው አለመተማመን፣ ካለ ትዳራቸው ሊፈርስ ይችላል፡፡ በሆነ ባልሆነው መጨቃጨቅ ከእገሌ ጋር አየሁህ፤ ከእገሌ ጋር አየሁሽ ወዘተ መባባል የጭቅጭቃቸው መጠን እየሰፋ ይሄዳል፡፡ በባልም ሆነ በሚስት በኩል በድብቅ የሚፈጸም ነገር ካለ በጎም ቢሆን መቆም አለበት፡፡ በበጎው ላይ መደባበቅ ካለ በመጥፎውም ላይ ሊኖር ይችላል በማለት እርስ በእርሳቸው እንዲጠራጠሩ ይገፋፋቸዋል፡፡ አለመተማመን ለወንዶች ወይም ለሴቶች ብቻ ተለይቶ የሚሰጥ አይደለም፡፡ ጥርጣሬ የሚፈጥሩ ነገሮችን ማስወገድ አለመቻል ነው፡፡

***፯. ግልጽ አለመሆን፡-*** በአንዳንዶቹ ዘንድ የሚበሉ፣ የሚጠጡትን፣ የሚለብሱትን ብቻ መናገራቸው ግልነት ሊመስላቸው ይችላል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን የውስጥ ስሜታቸውን በተክክል አይናበቡም፡፡ በይሉኝታ ተደብቆ፣ በራስ ማንነት ሳይሆን ሚስት ከሆነች ባሏን ባልም ከሆነ ሚስትን ደስ ያሰኙ እየመሰላቸው በትክክለኛ ማንነታቸው መገለጥ አለመቻል ሊገለጡ የሚገባቸውን ጉዳዮች አለመግለጥ፤ ግልጽ የገንዘብ ዝውውር አለመኖር፣ በድብቅ ቤተሰብን መርዳት ወዘተ ለግጭት መንሥኤ ሊሆን ይችላል፡፡

***፰. በሩካቤ ሥጋ አለመጣጣም ነው፡-*** ከጋብቻ በፊት ጤንነታቸውን፣ የውስጥ ስሜታቸውን በሚገባ ማጤን ይኖርባቸዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ከጋብቻ በፊት ባለ የቆይታ ጊዜ ከአላስፈላጊ መነካካት፣ ከመዳራት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ በስነ ልቡና ችግር፣ በፊት በነበራቸው የብቸኝነት እሳቤ በፍርሃት ወዘተ… ባለመነጋገር (ባለመወያየት ወዘተ በሚፈጠር አለመጣጣም ጋብቻ ሲፈርስ ይታያል)

***፱. የሌሎች አሉታዊ ጣልቃ ገብነት፡-*** ይህ በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በሥራ ባልደረባ ወዘተ አማካኝነት ትዳራቸውን ከሚያጸና ይልቅ የሚያፈርስ ሐሳብ ሊያመጣ ይችላልና የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ካለ ትዳር ሊፈርስ ይችላል፡፡ የአንዳንዶቹ ጣልቃ ገብነት በውስጣቸው የሐሳብ መለያየትን ከመፍጠር አልፎ ፍታት ወይም ፍቺው ብለው እስከ መወሰን ድረስ የሚደርስ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ባለትዳሮቹ በብሉይ ኪዳን "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ሚስቱንም ይከተላል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" (ዘፍ.፪፥፳፬) እንደተባለ በሐዲስ ኪዳንም ‹‹ስለዚህ ወንድ አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናል፤ ሁለቱም አንድ አካል ናቸው›› (ኤፌ.፭፥፴፩) ተብሏል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ይህን በአግባቡ በመረዳት ለትዳራቸው ዋስትና ማበጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ባል የሚስቱን ሐሳብ ሚስት የባሏን ሐሳብ አክብራ ለትዳራቸው እንቅፋት የሚሆነውን የሦስተኛ ወገን ሐሳብ በመተው ዘላቂ የሆነውን ኑሯቸውን መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ግን ከእናትና ከአባቴ አትበልጥብኝም /ጭብኝም በመባባል ትዳራቸው ሲፈርስ ይስተዋላል፡፡

# ከወንድሞቻችሁ ጋር በፍቅር ኑሩ

(ዕብ.፲፫፥፩)

በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

የሰው ልጅ ፍላጎቱ ገደብ የሌለው፣ አንዱ ሲሟላለት ሌላ የሚያስብ፣ በወቅቱ ያሰበው ሲከናወንለት ደግሞ ሌላ የሚፈልግ ነው። ይህ የሚሆነው ደግሞ አሳቢ አእምሮ ተሰጥቶት ስለተፈጠረ እንደሆነ ይታወቃል። ምን አልባትም እንደ አደገበት ሁኔታ፣ እንደተማረው የትምህርት ዓይነት፣ እንደኑሮ ዘይቤው የሚያስበው ነገር ሊለያይ ይችላል እንጂ የማያስብ ሰው ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ይሁንም እንጂ ስላሰበ ያሰበው ሁሉ አይሟላለትም፣ የጀመረውን ሁሉ አይፈጽምም፤ የተመኘውን ሁሉ አያገኝም። ምክንያቱም ፍላጎቱ ገደብ የለሽ ሆኖ የተፈጠረው የሰው ልጅ ፍላጎቱን ለማከናወን ያለው ዐቅም ውሱን ስለ ሆነ ነው። ይህም ሆኖ ለመኖር መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች መሟላት አለባቸው። ከእነዚህ መካከል ፍቅር፣ የእርስ በእርስ መተሳሰብ፣ የተቸገሩትን መርዳት ተጠቃሾች ናቸው። ስለዚህ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ከወንድሞቻችሁ ጋር በፍቅር ኑሩ" በማለት የተናገረው ለሰው ልጅ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል ስለሆነ ነው።

በመሠረቱ ወንድምነት በብዙ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ከሥነ ፍጥረት አንጻር ከተመለከትነው ምንም እንኳን ብዙዎቻችን በዚህ መልኩ ባንረዳውም ሁሉም የአዳምና የሔዋን ልጅ ስለሆነ ሁላችንም ወንድማማቾች ነን። ከምናመልከው አምላክና ከምንከተለው ክርስትና አንጻር ስንመለከተው ደግሞ በክርስቶስ ስም ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በአርባና በሰማንያ ቀን ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ሲቀበል የቤተ ክርስተያን አባል የክርስቶስ አካል ሲሆን ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ተወልዶ ሁሉም የሥላሴ ልጅ ይሆናል። ስለዚህ በዚም በኩል ሁላችንም ወንድማማቾች ነን። ይህን በአግባቡ መረዳት ባንችልም እንኳ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ኑሮ የሚያስፈልገውና ብቻውን ምሉእ እንዳልሆነ ሊገነዘበው ይገባል።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ምእመናን በላከው መልእክት የጠቀሰውን እንደ መነሻ በማድረግ ከላይ የተዘረዘሩትን አስፈላጊነት እንመለከታለን። "ከወንድሞቻችሁ ጋር በፍቅር ኑሩ። እንግዳ መቀበልንም አትርሱ፤ በዚህ ምክንያት መላእክትን በእንግድነት ለመቀበል የታደሉ አሉና። ከእነርሱ ጋር አብራችሁ እንደታሰራችሁ ሆናችሁ እስረኞችን ዐስቡ፤ መከራ የጸናባቸውንም በሥጋችሁ ከእነሱ ጋር እንዳላችሁ ሁናችሁ ዐስቡ። (ዕብ. ፲፫፥፩-፫) እንዲል። በዚህ ምንባብ ፍቅር፣ እንግዳን መቀበል፣ የታሰሩትንና የተቸገሩትን ማሰብ እንደሚገባ እንረዳለን። እያንዳንዳቸውን ዘርዘር አድርገን ለመመልከት ያህል፦

## ሀ. በፍቅር መኖር

ይህ ዘመን ክፋት እንደ ጽድቅ የተቆጠረበት ዘመን ነው በሚያስብል መልኩ ፍቅር ጥፍቷል። በቅዱስ ወንጌልም "ከመዓፃ ብዛት የተነሣ ፍቅር ከብዙዎች ዘንድ ትጠፋለች" (ማቴ.፳፬፥፲፪) ተብሎ እንደተነገረ ሰዎች ብትፋቀሩ ትኰነናላችሁ የተባሉ ያህል ፍቅርን ወደ ኋላ ጥለውታል። ይሁን እንጂ ሰዎች በዚህ ዓለም እስከ ኖሩ ድረስ እርስ በእርሳቸው ተፈቃቅረው እንዲኖሩ "ከወንድሞቻችሁ ጋር በፍቅር ኑሩ።" በማለት አስፈላጊነቱን ያስረዳናል።

ደግሞ ማንም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነኝ የሚል ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆኑ የሚረጋገጠው ባልንጀራውን መውደድ ሲችል እንደሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ "እኛም እርስ በእርሳችን እንዋደድ፤ እግዚአብሔርንም እንውደደው፤ እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና። እግዚአብሔርን እወደዋለሁ የሚል ወንድሙን ግን የሚጠላ ሐሰተኛ ነው፤ የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ግን የማያየውን እግዚአብሔርን እንደምን ሊወደው ይችላል? እግዚአብሔርን እንወድደው ዘንድ ወንድማችንንም እንወድ ዘንድ ከእርሱ የተቀበልነው ትእዛዝ ይህ ነው። እግዚአብሔርን የሚወድ ሁሉ ወንድሙን ይወዳል።" (፩ዮሐ.፬፥፲፱-፳፩) በማለት ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ያስረዳናል።

ፍቅር ለሰው ልጅ መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነና ከሁሉም እንደሚበልጥ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም "የሰውን ሁሉ

ቋንቋ ባውቅ የመላእክትንም ሁሉ ቋንቋ ባውቅ ፍቅር ከሌለኝ እንደሚጮህ ነሐስ ወይም እንደሚመታ ከበሮ መሆኔ ነው" (፩ቆሮ. ፲፫፥፩) በማለት ካስረዳን በኋላ ሐሳቡን ሲደመድምም "አሁንም እነዚህ ሦስቱ እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ጸንተው ይኖራሉ፤ ከሁሉም ግን ፍቅር ይበልጣል" (፩ቆሮ. ፲፫፥፲፫) በማለት የሚያስፈልጉንና ገንዘብ ልናደርጋቸው የሚገቡን ቢኖሩም ከሚያስፈልጉን በርካታ ነገሮች ሁሉ ፍቅር የሚበልጥ መሆኑን ያስረዳናል።

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በአግባቡ ተረድቶ ለሕይወት የሚሆን ሥራ ከመሥራት ይልቅ የጥያቄ ብዛትን ብቻ የማቸጎድጎድ ልማድ የነበራቸውና በትምክሕት የተሞሉት ጸሐፍት ፈሪሳውያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የትኛው ሕግ እንደሚበልጥ በጠየቁት ጊዜ ፍቅር ከሁሉም እንደሚበልጥ አስረድቷቸዋል። ይህን በተመለከተ በቅዱስ ወንጌል "ፈሪሳውያንም ሰዱቃውያንን ምላሽ እንዳሳጣቸው በሰሙ ጊዜ በአንድነት ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ከመካከላቸውም አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው ጠየቀው። መምህር ሆይ ከኦሪት ማንኛይቱ ትእዛዝ ትበልጣለች አለው። ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለው። አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይልህ ውደደው ታላቂቱና የመጀመሪያይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። የምትመስላት ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትለው ናት። ኦሪትና ነቢያት ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸንተዋል።" (ማቴ.፳፪፥፴፬-፵) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን።

ኦሪትም ነቢያትም በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸንተዋል ማለት የኦሪት ትእዛዝም የነቢያት ትንቢትም ፍቅር የባሕርዩ በሆነው ራሱም ፍቅር ነው በተባለው በእግዚአብሔር የተፈጸመና ጸንቶ የሚኖር መሆኑን ራሱ ባለቤቱ አስረድቶናል። የጌታውን የእግዚአብሔርን ቃል በአግባቡ የተረዳው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም "ከወንድሞቻችሁ ጋር በፍቀር ኑሩ" በማለት ለምድራዊውም ሆነ ለሰማያዊው ሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ሀብት ገንዘብ እንድናደርገው ያስረዳናል።

## ለ. እንግዳ መቀበል

ሰው በብዙ ምክንያት በሚፈልገውም ሆነ በማይፈልገው ምክንያት ከቤቱ ይወጣል። የሚቀበለው ይፈልጋል፤ የሚያስተናግደው ይሻል። በዚህ ጊዜ "የእግዚአብሔር እንግዳ" ብሎ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ እንዲያሳድሩት ሰዎችን ይለምናል። በዚህ ጊዜ ራሱን እግዚአብሔርን በአካል እንደተቀበሉት ቆጥረው በደስታ የሚያስተናግዱ አሉ። በአንጻሩ ደግሞ ቤቱን ለመሥራት የራሳቸው ብቻ አስተዋጽኦ እንጂ ቤቱ የእግዚአብሔር ስጦታ እንዳልሆነ በመቍጠርና የእግዚአብሔርንም ቸርነት ባለመረዳት ማንም እንዳይመጣብኝ የሚሉም አሉ። ሐዋርያው እንግዳ መቀበልን ዕለት ዕለት የሚያዘወትሩን እየመሰገነ የማይቀበሉትን ደግሞ በረከት እንዳይቀርባቸው እያሳሰበ ያስተምረናል።

እንግዳ መቀበል እንደሚገባ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። እግዚአብሔር አምላክ ለሊቀ ነቢያት ሙሴ የፋሲካን ሕግ በአስረዳበት ትእዛዝ "የእግዚአብሔርን ፋሲካ ያደርግ ዘንድ ወደ እናንተ የመጣ መጻተኛ ቢኖር ወንዱን ሁሉ ትገርዛለህ፤ ያን ጊዜ ፋሲካ ያደርግ ዘንድ ይገባል፤ እንደ ሀገር ልጅም ይሆንላችኋል፤ ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ" (ዘፀ.፲፪፥፵፰) በማለት ስለ ፋሲካ ክብር መገረዝ ለለበት ቢባልም ሊቀበሉት እንደሚገባ ግን ያስረዳናል። ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር አምላካችን "በሀገራችሁ ውስጥ እንግዳ ከእናንተ ጋር ቢቀመጥ ግፍ አታድርጉበት። እናንተ በግብፅ ምድር እንግዶች ነበራችሁና፤ ወደ እናንተ የመጣ እንግዳ እንደ ሀገር ልጅ ይሁንላችሁ፤ እርሱን እንደ ራሳችሁ ውደዱት፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና" (ዘሌ.፲፱፥፴፫-፴፬) ሲል ለሕዝቡ ያስተላለፈውን አምላካዊ ትእዛዝ እናገኛለን።

ይህ ሁሉ የሚያስረዳን ከጥንት ጀምሮ እንግዳ መቀበል አምላካዊ ትእዛዝ መሆኑን ነው። እንግዳ ይቀበሉ የነበሩ ሰዎች መላእክትን እንዲሁ እግዚአብሔርን በአንድነት በሦስትነቱ ለመቀበልና ከቤታቸው ለማስተናገድ በቅተዋል።

እንግዳ የመቀበል መልካም ልማድ የነበረው ሎጥ መላእክቱን ከቤቱ አስተናግዷል። በቅዱስ መጽሐፍ "ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ደረሱ፤ ሎጥም በሰዶም ከተማ በር ተቀምጦ ነበር። ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ፤ ፊቱንም ወደ ምድር ደፍቶ ሰገደላቸው፤ አላቸውም ጌቶች ሆይ ወደ ባሪያችሁ ቤት ገብታችሁ እደሩ፤ እግራችሁንም ታጠቡ፤ ነገም ማልዳችሁ መንገዳችሁን ትሄዳላችሁ። እነርሱም በዐደባባዩ እናድራለን እንጂ አይሆም አሉት። እርሱም ግድ አላቸው፤ ወደ እርሱም አቀኑ፤ ወደ ቤቱም

ገቡ፤ ቂጣንም አስጋገረላቸው፤ እነርሱም በሉ።" (ዘፍ.፲፱፥፩-፫) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም "እንግዳ መቀበልንም አትርሱ፤ በዚህ ምክንያት መላእክትን በእንግድነት ለመቀበል የታደሉ አሉና።" (ዕብ.፲፫፥፩) በማለት የነገረን እንደ ሎጥ ያሉትን እንግዳ ወዳዶች ሊያመሰግን ለእኛም ያላቸውን አርአያነት ሊያሳየን ነው።

ሌላውና የእንግዳ መቀበል ልማድ የነበረው ታላቁ አባት አብርሃም ነው። አብርሃም እንግዳ ካልመጣ ምግብ መመገብ የማይችል ታላቅ አባት ነበር። ይሁን እንጂ ጠላት ዲያብስ ቀንቶበት እግዳ ቢከለክለው አጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ ከቤቱ ተገኙለት። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ "በቀትርም ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ ዛፍ ሥር ተገለጠለት ። ዐይኑንም ባነሣ ጊዜ እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፤ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ፤ ወደ ምድርም ሰገደ፤ እንዲህም አለ አቤቱ በፊትህ ባለሟልነትን አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈው፤ ውኃ እናምጣላችሁ፤ እግራችሁንም እንጠባችሁ። ከዛፉም ሥር ዕረፉ እንጀራም እናምጣላችሁና ብሉ፤ ከዚያም በባሪያችሁ ዘንድ ካረፋችሁ በኋላ ወደ ዐሰባችሁበት ትሄዳላችሁ። እነርሱም እንዳልህ እንዲሁ አድርግ አሉት።" (ዘፍ.፲፰፥፩-፰) በማለት የአብርሃምን መልካም ሥራ ከመልካም ሥራውም የተነሣ እግዚአብሔርን በአንድነት በሦስትነቱ ማየት እንደቻለ፣ ማየት ብቻም ሳይሆን ከቤቱ ለማስተናገድ እንደታደለ ያስረዳናል።

በሐዲስ ኪዳን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እንግዳ ቢቀበሉ በዳግም ምጽአቱ "እናንተ የአባቴ ቡሩካን" ብሎ እንደሚቀበላቸው አስረድቶናል። (ማቴ.፳፭፥፴፫) ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ካህን ሊሆን የሚወድ ሰው ቢኖር መሆን አለበት ብሎ ከዘረዘራቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ "እንግዳ ተቀባይ መሆን አለበት" የሚል ነው። (፩ጢሞ.፫፥፪) ፤ (ቲቶ ፩፥፰) ለዕብራውያን ምእመናንም እንግዳ መቀበልን አትርሱ ያላቸው ሰዎች በሕይወታቸው ሊፈጽሟቸው ከሚገቡት ተግባራት መካከል ስለሆነና በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ በረከትን የሚያሰጥ ስለሆነ ነው።

ዛሬም በአንድም በሌላም ከቦታቸው ተፈናቅለው፣ በማያውቁት ሀገር እየተንከራተቱ ያሉትን፣ ሀገር እያላቸው ሀገር እንደሌላቸው በግፈኞች እየተሳደዱ በመከራ የሚሠቃዩትን እንግዶች መቀበል እንዳለብን ከዚህ መልእክት ልንማር ይገባናል።

## ሐ. እስረኞችን ማሰብ

ሰዎች አጥፍተውም ሆነ ሳያጠፉ ይታሰራሉ። ወደ ዘመነ ሰማዕታት መለስ ብለን የቅዱሳኑን ሕይወት ስንመለከት በዐላውያን ነገሥታት በዐላውያን መኳንንት ሃይማኖታቸውን እንዲክዱ፣ ለጣዖት እንዲሰግዱ ይገደዱ ነበር። ሃይማኖታችንን አንክድም ለጣዖትም አንሰግድም ሲሉ ይታሰሩ ከዚህም አልፎ ይገደሉ ነበር። ዛሬም በግልጥ የቆመ ጣዖት ባይኖርና ስገዱ ባይባሉም በሃይማኖታቸው ምክንያት በእስር ቤት የገቡት በርካቶች ናቸው። በዚህ ጊዜ ልንጠይቃቸውና ልናረጋጋቸው ይገባል።

መሪዎች በሚያስተዳድሩት ሕዝብ ላይ ግፍ ሲፈጽሙ፣ የአስተዳደር ብልሹነት ሲሰፍን መምህራኑ፣ በኃላፊነት ላይ ያሉም ሆኑ የሌሉ አካላት "ድሃ ተበደለ ፍርድ ጎደለ" በማለታቸው ይታሰራሉ፤ ብሎም ይገደላሉ። መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ "ዋርሳ አትውረስ" ብሎ ሄሮድስን በመገሠጹ ታሰረ። በቅዱስ ወንጌል "ዮሐንስም የአራተኛው ክፍል ገዢ ሄሮድስን የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን ስለ ማግባቱና ሄሮድስ ያደርገው ስለነበረው ክፉ ነገር ሁሉ ይገሥጸው ነበር። ደግሞም ከዚህ ሁሉ በላይ ጨምሮ ዮሐንስን ተቀየመውና በግዞት ቤት አስገባው" (ሉቃ.፫፥፲፱) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንግሥቲቱ አውዶክስያ የድሃዪቱን መሬት በመቀማቷ ገሠጻት እርሷም ለምን ድሃዪቱን አትበድዪ ተባልሁ ብላ ወደ እስር ቤት አስገባችው።

ዛሬም በጥፋታቸውም ይሁን ያለጥፋታቸው በእስር ቤት ያሉ አሉ፤ ባለ ሥልጣናቱ እንደ ጥንቱ ለብልሹ አገዛዛቸው የሚያሰጋ ሲመስላቸው ምክንያት እየፈለጉ ወደ እስር ቤት ማስገባት የተለመደ ነው። በዚህ ሁሉ ሐዋርያው "ከእነርሱ ጋር አብራችሁ እንደታሰራችሁ ሆናችሁ እስረኞችን ዐስቡ" በማለት የእነርሱን መከራቸውን፣ ችግራቸውን፣ ግፋቸውን፣ እያሰብን የሚቻለንን ሁሉ እንድናደርግ፣ ለእነርሱ በቀጥታ የምናደርግላቸው ነገር ባይኖረን እንኳን እነሱን እያሰብን ወደ እግዚአብሔር ጸሎት እንድናቀርብ ያስተምረናል።

## መ. መከራ የጸናባቸውን ማሰብ

መከራ በልዩ ልዩ መንገድ ይመጣል:: የመከራ መምጫ ምክንያቶችን መዘርዘሩን እንተወውና ዛሬ በርካታ ሰዎች ከቤታቸው ወጥተው፣ ከሀገራቸው ተሰድደው፣ በባዕድ ሀገር ተጠልለው፣ ሀብት ንብረታቸው ተዘርፎባቸው፣ የሚበሉት የሚጠጡት አጥተው እየተቸገሩ በጽኑ መከራ ውስጥ ይገኛሉ:: እነዚህን አካላት ቢቻል በአካል ሂዶ መጎብኘት፣ ባይቻል ደግሞ ባሉበት ቦታም ቢሆን ከእነርሱ ጋር እንዳሉ ሁኖ ማሰብ ያስፈልጋል:: ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ "እኔ በሥጋዬ ከእናንተ ጋር ባልኖር በመንፈስ ከእናንተ ጋር አለሁ::" (፩ቆሮ.፭፥፫) በማለት እንደተናገረው ባለንበት ሁነንም ቢሆን እያሰብናቸው እንደሆንን እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል::

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "በሥጋ ከእነርሱ ጋር እንዳላችሁ ሆናችሁ መከራ የጸናባቸውን ዐስቡ" ሲለን በአካል ሥጋ መኖርና አለመኖር የራሱ የሆነ ዋጋ ስላለው ነው:: ይህ ልዩነት የሚኖረው በቅዱሳኑ ዘንድ አይደለም:: በቅዱሳኑ ዘንድ በያሉበት ቦታ ሁነው የፈቀዱትን ማድረግ ይችላሉ:: ታሪኩ በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ እንደምናገኘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የመቶ አለቃው "ቃል ብቻ ተናገር ልጄ ይድናል" (ማቴ.፰፥፰) ባለና በለመነው ጊዜ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የመቶ አለቃውን ፍጹም እምነት ዐይቶ "እንደ ወደድህ ይሁንልህ" (ማቴ.፰፥፲፫) ሲለው ልጁ ተፈውሷል:: ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ " እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ እርሱም ይሠራል፤ ከዚያም የሚበልጥ ይሠራል::" (ዮሐ.፲፬፥፲፪) በማለት ጽኑ ቃል ኪዳን እንደገባላቸው በፍጹም እምት ጸንተው በበጎ ምግባር እየተመላለሱ የሚኖሩ ቅዱሳን በአካል ሥጋ መገኘት ሳይጠቅባቸው ሁሉን ማድረግ ይችላሉ::

ይሁን እንጂ እንደ መቶ አለቃው ያለ ፍጹም እምነትና እንደ ቅዱሳኑ ያለ ብቃት ለሌለው ሰው በጎ የሚያደርገውና በጎ የሚደረግለት ሰው በአካል መገናኘት ያስፈልጋቸዋል:: በጎ አድራጊው በአካል ተገኝቶ የችግረኛውን ሁኔታ ሲመለከት እጅግ ውስጡ ይራራና የሚችለውን ያህል መልካም ነገር ለማድረግ ይፋጠናል:: በጎ ነገር የሚደረግለት አካል ደግሞ በጎ አድራጊውን በአካል ሲመለከተው የሚደረግለት ነገር ቢያንስ እንኳን በተደረገለት ጥቂት ነገር አእምሮው ሊጽናና ይችላል:: ሐዋርያው "በሥጋ እንደተገኛችሁ ሆናችሁ መከራ የጸናባቸውን ዐስቡ" ያለውም ስለዚህ ነው::

ረኃብ ክፉ ነው፤ ዐቅም ያሳጣል፤ መልክ ይለውጣል፤ ጸባይ ያጠፋል፤ ሲበረታም ይገድላል:: ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ "በሰይፍ የሞቱት በራብ ከሞቱት ይሻላሉ፤ እነዚህ የምድርን ፍሬ አጥተው ተወግተውም ዐልፈዋል" (ሰቆ.፬፥፱) በማለት እንደተናገረው የአሟሟታቸው ሁኔታም እጅግ የሚዘገንን ይሆናል:: በዚህ ጊዜ መድረስ ያስፈልጋል:: መድረስ ብቻ አይደለም በአካል ከእነርሱ ጋር ተገናኝቶ በአንደበትም በተግባርም የሚቻለውን ያህል ማገዝ በእነርሱ ሕይወት ላይ እጅግ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል::

> "በሥጋ ከእነርሱ ጋር እንዳላችሁ ሆናችሁ መከራ የጸናባቸውን ዐስቡ"

በአጠቃላይ ሰዎች በኑሯቸው ሁሉ ብቻቸውን ማከናወን የማይችሉትን ከሌሎች ጋር ሲሆኑና አንዱ ከሌላው ጋር በፍቅር እየተሳሰቡ መኖር ሲችሉ፣ የአንዱን ክፍተት ሌላው እየሞላ እርስ በእርስ ሲረዳዱ፣ ለብቻ ሲሆኑ እጅግ የሚያስቸግረውን የሕይወት ውጣ ውረድ ማቃለልና የተመቻቸ ኑሮ መኖር ይችላሉ:: ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ በልዩ ልዩ ምክንያት በእስር ቤት ያሉትን፣ ፍትሕ የጎደለባቸውን፣ ዳኛ የበደላቸውን፣ ኀዘን የበዛባቸውን ልንጠይቃቸውና ልናረጋጋቸው ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከቦታቸው ተፈናቅለው፣ ሀብት ንብረታቸው ተወስዶባቸው፣ የሚጎርሱት፣ የሚለብሱት አጥተው መከራ እየተፈራረቀባቸው ያሉ ችግረኞችን እያሰብን አስፈላጊውን ርዳታ ልናደርግላቸው ይገባል:: በዚህ መልካም ሥራ ሁላችንም ተሳትፈን ከበጎ ሥራ የሚገኘውን በረከት እንዲያድለን እግዚአብሔር ይፍቀድልን አሜን::

# የወደቀው መልአክ

## ኪነ ጥበብ

*በመዝሙርና ሥነ ጥበባት አገልግሎት ማስተባበሪያ*

“አብዬ…”

“አንተ…” ትለኛለች፡፡

አያቴ ናት፡፡ የቤቱ ደጃፍ ላይ ቁጭ ብየ ከራሴ ጋር ብይ እየተጫወትኩ ነበር፡፡ ቅዳሜ ከቀኑ አሥር ሰዓት ገደማ ይሆናል፡፡ ከቤት ውስጥ መስኮቱ ባለበት ግድግዳ በኩል የተሠራ መደብ ላይ ተኝታ ነው ምትጠራኝ፡፡ የመጀመሪያውን ጥሪዋንም ሰምቸዋለሁ… ለምን እንደሆነ አላውቅም ብዙ ጊዜ በሁለተኛው ጥሪ ነው መልስ የምሰጠው፡፡ የጠራኝ ሰው አንድ ጊዜ ብቻ ተጣርቶ ካቆመ በቃ እኔም እየሰማሁት ሳልመልስ እሱም ሳይደግም እንለያያለን፡፡ ለዚህ ነው አያቴ ስትጠራኝ መጀመሪያ ስሜን አቆላምጣ ትጠራኝና እንደሰማሁ ስለገባት በሁለተኛው “አንተ..” ትለኛለች፡፡ ለምን እንደዚህ እንደማደርግ ለኔም አይገባኝም፡፡

“ኧ ኧ ኧ…” የተለመደ መልሴ ነው፡፡ አቤት የምለው ለማላውቀው ሰው ነው፡፡ ለምን? እንደሆነ እኔ እንጃ!

“ነገ ጠዋት በተስኪያን ህደህ የቅዳሴ ጸበል እንድታመጣልኝ እኔ አሞኛል እግሬ እሽ አይለኝም፡፡” አለች፡፡

“እሺ፡፡” አልኩ፡፡ ቀዝቀዝ አድርጌ ህጄ ብይ ማንከባለሉን ሳላቆም፡፡

እግሯን ያማታል፡፡ “ቁርጥማት ነው” ስትል እሰማለሁ፡፡ እኔ አይገባኝም፡፡ ሳስበው እግሯ ውስጥ የሆነ የሚበላት የሚነክሳት ነገር ያለ ነው የሚመስለኝ፡፡ ሲያማት ባቷን በእጆቿ እያሸች ጥርሷን ነክሳ የሕመም ስሜት ስታሳይ እና “እሁሁሁ…” ስትል የማደርገውን ነገር አቁሜ እግሯን አያለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በእጆቼ አሸላታለሁ ግን ትንንሽ መዳፎቼ እና ልፍስፍስ ጉልበቴ አያረካትምና ተቀብላኝ ታሸዋለች፡፡

አያቴን ሳስታውሳት የምትመስለኝ፡፡ ድ……..ሮ ጀምሮ ገና ስትወለድ መሀል ላይ አንድ ትልቅ ቁልፍ ያለው ነጫጭ የአበባ ስዕል ያለበት ጥቁር ሹራብ የለበሰች፡፡ ድ……ሮ ጀምሮ ቢጫ ቆብ የለበሰች፡፡ ድ….ሮ ጀምሮ ከርደድ ያለ ቀሚስ ያላት እና መቁጠሪያዋ በአንገቷ አልፎ እስከ ሆዷ የደረሰ፡፡ ድ…ሮ ጀምራ የዋህ….

ዛሬ ባያማት ኖሮ እሁድ በጠዋ…ት ትነሣና “አብዬ…. አንተ…. ተነሣ ልብስህን ልበስ፡፡ ንቃ ታጠብ ፊትህን…” ብላ ትቀሰቅሰኝና ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዛኝ ትሄዳለች፡፡ አንዳንድ ቀን ከእንቅልፌ መነሣት ቢመረኝም ብዙውን ጊዜ ግን አላማርርም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ደጀ ሰላሙ ላይ ስንደርስ መቋሚያዋን አንደኛዋ የበሩ ጥግ ላይ ታስደግፍና ከበሩ መካከል ፊት ለፊት መካከሉ ላይ ትቆምና ወፍራሙን ነጠላዋን አስተካክላ እጆቿን አንስታ “በስመ አብ…” ስትል እሰማታለሁ፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ያለው አይሰማኝም፡፡ ዝም ብዬ አያታለሁ እስከ ምትጨርስ፡፡ ይበርደኛል፡፡ አካባቢው ከዛፎች እንቅስቃሴ እና ከወፎች ድምፅ በተጨማሪ ከቤተ ክርስቲያኑ ሄድ መለስ እያለ ከሚመጣው የቄሶች ቅዳሴ ድምፅ ውጭ ምንም አይሰማም፡፡

ተሳልማ ስትጨርስ እና የበራፉን ሁለቱን መቃኖች ስትስም እኔም ሄጄ እስማለሁ፡፡ ወደ ውስጥ እንሄዳለን እንደገና የቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ በር ላይ ስንደርስ ትሳለማለች እኔ አጠገቧ እቆማለሁ፡፡ “የሴቶች መግቢያ” የምትለውን ጽሑፍ እንደተለመደው ደጋግሜ አነባታለሁ፡፡ ግን ቃላቱን ቦታ በማቀያየር ሌላ አዲስ ቃል ለመመሥረት እሞክራለሁ፡፡ ገልብጬ ደግሞ አነበዋለሁ፡፡ “ያቢግመ ችቶሴየ…” በመካከል አያቴ መሳለሟን ትጨርሳለች፡፡ እንገባለን፡፡ ሌሎች የተቀመጡ መነኮሳትን ድምጿን ቀንሳ ሰላም ትላለች፡፡ “….ችሁ” የምትለዋ ድምፅ ብቻ ናት የምትሰማው፡፡ ሰዎቹን በስም አላውቃቸውም እነርሱም እንደ አያቴ መነኵሴ ናቸው፡፡ ሁልጊዜ እሑድ እሑድ እዚህ ስለማገኛቸው እዚህ የሚኖሩ ነው የሚመስለኝ፡፡ ደግሞ የሚገርመኝ ተሳስተው እንኳን የሚቀመጡበት ቦታ ተቀያይሮ አያውቅም፡፡ ለዚያ ነው እዚህ የሚኖሩ የሚመስለኝ፡፡

አያቴ የምትቆምበት ቦታ ላይ ስትደርስ እንደገና ትሳለምና ዝቅ

ብላ እያየችኝ በጣቷ ወደ መሬት ትጠቁመኛለች ስለሚገባኝ አንገቷ ላይ ክር የታሰረባትን የጸበል እቃ ክዳኗን ከፍቼ ከፊት ለፊታችን አስቀምጣታለሁ፡፡ አያቴ አታወራኝም፡፡ ከፊት ለፊቴ ግድግዳ ላይ የተሳሉትን ስዕሎች ማየት እጀምራለሁ፡፡ አንዳንዶቹን አያቴ ስለነገረችኝ አውቃቸዋለሁ፡፡ በፈረስ ዘንዶ የሚወጋ… ሰው የሚመስል ነገር በራሱ የተሸከመ ከጎኑ የሆነ ወታደር የሚመስል ሰውዬ ሲከተለው… የማርያም (የሆነ ሰው እጁን ደረቱ ላይ አድርጎ ከማርያም እግር ስር ሆኖ “ቅዱስ ኤፍሬምን እንደባረከችው” የሚል ጽሑፍ ያለበት) … ጌታችን ተሰቅሎ በመጋረጃ ተሸፍኖ… ሌላም ብዙ ሳይ እቆይና ይደክመኛል፡፡ አያቴን ቀና ብየ አያታለሁ፡፡ ፊት ለፊት እያየች ዝም ብላለች፡፡ አታየኝም፡፡ ቀስስስ ብዬ ወደ ግድግዳው ተጠግቼ አያቴ እግር ስር እቀመጣለሁ፡፡ እንቅልፌ ይመጣል፡፡ የሆነ ሰዓት ላይ እጆን ነቅነቅ ነቅነቅ ስታረገኝ ብንን እልና ቀና ስል ወዲያው ዲያቆኑ በተቀመጥኩበት ፊቴን በመጽሐፍ ያሳልመኝና ያልፋል፡፡ ትንሽ ግራ ይገባኝና ያለሁበት ትዝ ይለኛል፡፡ ግራና ቀኝ ያሉትን ሰዎች ትንሽ እቃኝና ተመልሼ አንገቴን ስደፋ እንቅልፍ ይዞኝ ይሄዳል፡፡

ቅዳሴው ሊያልቅ እግዚኦታ ሰዓት ላይ ተነሥቼ እቆማለሁ፡፡ አብሬ እግዚኦ ለማለት እሞክራለሁ… በትክክል አልለውም፡፡ ሲጠናቀቅ ጸበል ጠጥተን አስቀድተን መክፈልት በልተን ከሌሎች መነኮሳት ጋር አያቴ እያወራች ወደ ቤት እንሄዳለን፡፡ መንገድ ላይ ቀስስ… እያሉ እያወሩ የሚሄዱት ነገር ትንሽ ያናድደኛል፡፡ እኔ ቶሎ ቶሎ በልጅ እግሬ ስሄድ እነሱ አይከተሉኝም፡፡ አያቴን ትቼ ወደ ቤቴ መሄድ ደግሞ አልችልም፡፡ ትቀየመኛለች፡፡ ስለዚህ በየመሀሉ እየቆምኩ መንገድ ላይ ባገኘሁት ነገር ለመጫዎት እሞክራልሁ፡፡

ዛሬ ግን አያቴ እግሯን ስላመማት ብቻየን ነው የምሄደው፡፡ እሑድ ጠዋት ቀድሞ አያቴ ስትቀሰቅሰኝ እነሣበት ከነበረው ሰዓት ረፈድፈድ ብዬ ተነሣሁ፡፡ አያቴ ተኝታለች፡፡ እንቅልፍ ግን አልወሰዳትም፡፡ ፊቴን ታጥቤ ነጠላዬን እሷ ስታለብሰኝ እንደምታደርገው አድርጌ ለመልበስ ሞከርኩ፡፡ ዝም ብላ በተኛችበት ታየኛለች፡፡ የጸበል እቃዋን ከራስጌዋ አንሥቼ ከቤት ወጥቼ መንገድ ጀመርኩ፡፡ ወደ በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን፡፡ የጸበል እቃዋ ነጭ ናት፡፡ ዙሪያዋን ዳር ዳሯን በጥርሴ ነክሻታለሁ፡፡ የጥርሴ አሻራ ታትሞባታል፡፡ ለምንድነው የምነክሳት?? ስነክሳት ትምቡክ ትምቡክ ስለምትል ደስ ስለምትለኝ ይመስለኛል፡፡

ከረፈደ ስለ ተነሣሁና በመንገድም ላይ ቀስ እያልኩ ስለሄድሁ ቅዳሴ ገብተው ደረስኩና ደጀ ሰላሙ አንድ ጥግ ላይ ቆሜ ማስቀደስ ጀመርኩ፡፡ ስለተለያየ ነገር ሳስብ ቅዳሴው አለቀና ጸበል አስቀድቼ እሑድ በመጣ ቁጥር እንዲያልፉኝ ለማልፈልጋቸው ሁለት ነገሮች ተዘጋጀሁ፡፡

የመጀመሪያው ተአምረ ማርያም ሲነበብ ታሪኩን መስማት ነው፡፡ መጽሐፉን ገልጠው ከሚያነቡት ቄስ እግራቸው ስር ሔጄ እቆምና ሌላ ነገር ሳላስብ የሚነበበውን ታሪክ እሰማለሁ፡፡ እግራቸው ስር ሔጄ የምቆመው ድምፃቸው በደንብ እዲሰማኝ እና ሲጨርሱ መጀመሪያ እኔን እንዲያሳልሙኝ ነው፡፡ የተአምረ ማርያም መግቢያውን ዘወትር ከመስማቴ የተነሳ በቃሌ ሸምድጀዋለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከሚያነበው ቄስ ጋር አብሬ ለራሴ አነበንባለሁ፡፡ የዕለቱ ታሪክ ሲደርስ አዲስ ያልሰማሁት እንዲሆን በልቤ እመኛለሁ፡፡ የሰማሁትን ፈጽሞ አልረሳውም፡፡

ሁለተኛው ትልቅ እና ተጠባቂ ነገር ደግሞ ከተአምረ ማርያም በኋላ የሚኖረው መክፈልት ነው፡፡ መጀመሪያ ተሳልሜ መክፈልት ወደ ሚበላበት ስፍራ ሔጄ ቁጭ ብዬ እጠባበቃለሁ፡፡ ሰዎቹ እስኪሳለሙ ሁሉም ሰው እስኪመጣ መጠበቅ ግድ ነው፡፡ ይዘገዩብኛል፡፡ ሁሉም ካልመጡ ደሞ የአያቴ ጓደኛ መክፈልቱን መስጠት አይጀምሩም፡፡ በጸበል እቃዬ እየተጫወትኩ ጥበቃዬን እቀጥላለሁ፡፡ ትልልቅ ሰዎች ተቀምጠው ሲጨርሱ መክፈልት መሰጠት ይጀምራል፡፡ ሁልጊዜም እዚያ ጫፍ ላይ ከተቀመጡት ሽማግሌ ሰውዬ ነው የሚጀመረው፡፡ “ለምንድነው እኛ ካለንበት ቦታ መስጠት የማይጀምሩት?” የሚል ጥያቄ ይመጣብኛል፡፡ ግን አይቀየርም፡፡ የአያቴ ጓደኛ ብቻዬን መቀመጤን ሲያዩ

“አንተ አያትህ ምን ሆነው ቀሩ ዛሬ?” አሉኝ ይተዋወቃሉ፡፡ ጓደኛ ናቸው፡፡

“እግሯን አሟት ተኝታለች፡፡” አልኩ፡፡

“አዬዬዬ…ያ ቁርጥማት ተነሣችባቸው ደግሞ?” አሉ፡፡ መልስ አልሰጠሁም፡፡ ዐይኔም ልቤም በሰፊ ሰፌድ ከያዙት ዳቦ ላይ ነው፡፡

“በል እንካ ከመክፈልቱ ውሰድላቸው….” ብለው ፫ የዳቦ ቁርሥራሾች እቅፌ ላይ አደረጉልኝ፡፡ በጣም ውስጤ ፈነደቀ፡፡ ደስታዬን ፊቴ ላይ ላለማሳየት ሞከርኩ፡፡ አልቻልኩም ፈገግ

አልኩ ሳላውቀው:: ከዚያ በኋላ የተናገሩትን አልሰማሁም እንጂ የሆነ ነገር ተናግረዋል:: መክፈልቱን በፍቅር አየሁት:: ቀስ አድርጌ በትክክል በአራት ማዕዘን የተቆረሰውን መክፈልት አንደኛውን ጎን ቆረስ አድርጌ ወደ አፌ አልኩት:: ሁሌም እንደተገረምኩ ነው:: እጅግ በጣም ነው ሚጣፍጠው:: ሽታው ብቻ ለኔ ልዩ ነገር ነው:: ስበላው ምንም ነገር አላስብም እሱን ብቻ ነው በአፌም በልቤም የማላምጠው:: ጥያቄዎቼን አስከትላለሁ:: “ምን ቢያደርጉበት ነው እንዴህ የሚጣፍጠው?... ለምንድን ነው እኛ ቤት የሚጋገረው መክፈልት እንደዚህ የማይጣፍጠው?... መጋገሪያው ቤት ውስጥ ስንት መክፈልት ይኖር ይሆን...” ተደጋጋሚ ናቸው ጥያቄዎቼ:: አይሳካም እንጂ ሁልጊዜም እንዲደግሙኝ እፈልግ ነበር:: ግን አይደግሙኝም:: እኔም ድገሙኝ ብዬ አላውቅም:: “ምናለበት ከቤት ፻ ሙሉ ሙሉ መክፈልት አምጥቼላቸው እዚህ ባለው መክፈልት ቢቀይሩኝ...” እያልሁ አስባለሁ::

ሳላውቀው እማሆይ ከሰጡኝ መክፈልት ሁለቱን በላሁት:: ሦስተኛውንም ብደግመው ደስታዬ ነበር ግን ለአያቴ መውሰድ አለብኝ:: እጄ ላይ የቀረውን አንድ መክፈልት አፌን እያጣጣምኩ አየሁት:: እንዳልሳሳት በነጠላዬ ሸፈንኩት:: ወደ ቤቴ መሄድ ብፈልግም ትልልቅ ሰዎች ጨርሰው ሳይነሡ መነሣት ስለማይቻል ተቀምጬ መጠበቁን ተያያዝኩት:: ልክ ከትልልቆቹ አንደኛው ከመቀመጫው ብድግ ሲል እኔም ላጥ ብዬ ተነሣሁ :: ለካ ሰውየው የተነሣው ለተሰበሰበው ሰው የሆነ ነገር ሊናገር ነበር እንጂ ሊሄድ አልነበረም:: ከጎኔ የተቀመጡት ሰውዬ ሲያዩኝ ትንሽ እፍረት ቢጤ ያዘኝና ተመልሼ ቁጭ አልኩ::

የሚነገረው ነገር ተነግሮ ሰዎቹም ተነሥተው መንገድ ስንጀምር ከኋላ ተነሥቼ ከፊት እገኛለሁ:: ቤት ልደርስ ትንሽ ሲቀረኝ ለአያቴ የያዝኩትን መክፈልት አየሁት ... ተቀነጣጥቦ ግማሽ ደርሷል:: አያቴ እንደምትታዘበኝ ገባኝ:: ያም ሆኖ የቀረውን ይዤ ቤቴ ስገባ አያቴን በረንዳ ላይ ተቀምጣ ፀሐይ ስትሞቅ አገኘኋት:: የጸበል እቃውን እና ከመቀነጣጠብ የተረፈ መክፈልቱን እሰጣታለሁ:: ትመርቀኝና ከጸበሉ ጠጥታ መክፈልቱን ትበላለች:: በልታ ስትጨርስ አፍ አፏን አያታለሁ:: አንድ ነገር እንድትጠይቀኝ እፈልጋለሁ:: ካልጠየቀችኝ ቅር ይለኛል:: እንደ ሁል ጊዜው እያጣጣመች ትጠይቀኛለች::

“ዛሬ ምን ዓይነት ታምር ተነገረ ንገረኝ እስኪ..?” ስትለኝ ከአፏ ነጠቅ አድርጌ

“ዛሬማ ታምር ላይ ... የሆነ አገር ላይ አዲስ የማርያም ቤተ ክርስቲያን እየተሠራ ነበር:: ከዚያ እዚያ ሰፈር ግመል የሚጠብቅ አንድ እስላም ሰውዬ ነበረ:: ግመሉን ሲጠብቅ ሳያያት አንዷ ግመል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገባችበት:: ከዚያ ደንግጦ ሔደና ሊያስወጣት ቢል እምቢ አለችው:: ከዚያ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዳልገባ ብሎ ከውጭ ሆኖ ወደ ውስጥ ድንጋይ መወርወር ጀመረ:: ከዚያ በድንጋይ ግመሏን አስወጣት:: አንድ ቀን ሲሞት ሰማይ ቤት ሊኰነን ሲል ማርያም ደግሞ መጥታ ጌታችንን “ይሄን ሰው ማርልኝ” አለችው:: ከዚያ “አልምርልሽም በሥላሴ አላመነም አልተጠመቀም” አላት:: ከዚያ “ቤተ መቅደስሽን ያሠራውን እምርልሻለሁ ብለኸኝ አልነበር:: ይህም ሰው ግመል ለማባረር ብሎ የወረወረው ድንጋይ አዲስ ከሚሠራው ቤተ መቅደሴ ላይ አርፎ ሕንጻው ተሠርቶበታል::” ስትለው “እሺ እምርልሻለሁ” ብሎ ማረላት:: ሰውየውም ዳነ::”

አያቴ ዐይን ዐይኔን በዝምታ እያየች ነው የምታዳምጠኝ:: ታሪኩን በገባኝ መንገድ ስለሆነ የምነግራት ግማሹን አልነግራትም:: አያቴ ግን ይገባታል:: ታሪኩን ስለምታውቀው ይሁን ዐላውቅም:: በጭንቅላቴ ውስጥ ያለውን ሁሉ አልነግራትም አንዳንዱን እዘለዋለሁ ዋና ዋና የመሰለኝን ነው ምነግራት::

ስጨርስ “ጎሽ” ትለኝና ቁርሴን እንጀራ በሽሮ ትሰጠኛለች:: ከመክፈልት የጎደለውን በሽሮ እሞላና ወደ ጨዋታዬ እወጣለሁ:: አያቴ ከቤት አትወጣም:: ተመልሼ ስመጣም በረንዳ ላይ ተቀምጣ ጥጥ እየፈተለች በእግሯ ደግሞ ጠርዝ ጠርዙ የተጨማደደ ደብተሬን እንዲስተካከል ረግጣ ይዛ አገኛታለሁ:: ደብተሬን እየተኮሰችው ነው:: አያቴ የአስኳላ ትምህርት ስላልተማረች ነው እንጂ ብታስጠናኝ ደስ ይላታል:: ግን... ያላት አማራጭ የተጨማደደ ደብተሬን ማስተካከል ብቻ ነው::

የሆነ ቀን አያቴ ሌላም ተጨማሪ ሕመም አሟት ብዙ ቀን ከተኛች በኋላ ከጨዋታ ስመለስ እቤታችን ሰው ሲንጫጫ ደረስኩ:: አያቴ ሞታለች:: አላለቀስኩም:: የምር አልመሰለኝም ነበር:: እየቆዬ ሲመጣ ግን አያቴ ስለምትናፍቀኝ ብቻዬን ማልቀስ ጀመርኩ::

ሁልጊዜም እሑድ በመጣ ቁጥር አያቴ በምትቀሰቅሰኝ ሰዓት ወደ ቅዳሴ እየሄድኩ በአያቴ የጸበል እቃ ጸበል እያመጣሁ ማስቀመጡን ሥራ ብዬ ተያያዝኩት:: ዝምታዬ ግን እየበረታ መጣ ብዙ ነገር አላወራም:: ውዳሴ ማርያም ተምሬ ዳዊት ደግሜ ከድርገት በፊት ቅኔ ማሕሌት ላይ ሃይማኖተ አበው ማንበብ ጀመርኩ:: ከትምህርቴ ባሻገር ከቤተ ክርስቲያን ደጃፍ አልጠፋም:: ዕድሜዬ እየጨመረ ዝምታዬ ቦታውን ሳይለቅ አደግሁ::

ልጅነቴ አልፎ ሃያዎቹ ዕድሜ ውስጥ ከገባሁ በኋላ የልጅነት አመሌ እየተለወጠ የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን መሞከር ጀመርኩ:: የሥጋዊ ስሜቴ እየፈተነኝ ያንገዳግደኝ ጀመር:: ከዕለታት አንድ ቀን በአጋጣሚ ከአንድ በዓለማዊ ትምህርት ከገፋና የፍልስፍና ባለሙያ ነኝ ከሚል ሰው ጋር ተቀምጠን በምናወራበት ጊዜ ከወሬ ወሬ ተነሣና

“ግን ለምንድን ነው ሰው የሚያስፈልገውን ነገር እንደፈለገ መፈጸም የማይችለው?”

በመባባል ረጅም ሰዓት አወራን:: አብሮ ከሚያወራኝ ሰውም በርከት ያሉ የፍልስፍና አመለካከቶችን አነሣን::

ከዚያን ቀን ጀምሮ አመለካከቴ ተቀየረ:: “ሰው እንዴት ከራሱ ስሜት ጋር ጦርነት ይገጥማል?” ለምን አያስተነፍሰውም? የሚል አስተሳሰብ አደረብኝ:: አዋዋሌ ተቀየረ:: ጓደኞቼ በዙ:: ያላደግሁበትን ከሴቶች ጋር መዋል ማደር መጫወት መቃለድ ጀመርኩ:: ስለ ቅዳሜ ያለኝ አመለካከት ተለወጠ:: እንደተሰማኝ እንዳየሁት ዘና ማለት ጀመርኩ:: ያደግሁ የተለወጥኩ መሰለኝ:: ውስጤ ደስተኛ ሆነ:: ባለኝ ነገር እዝናናለሁ:: ከሌለኝ ደግሞ አብረውኝ ከሚውሉ ጓደኞቼ ጋር በተገኘው ነገር እዝናናለሁ:: እንደተለመደው ቅዳሜ ዕለት ስልኬ ጠራ ሔድኩ፤ ተሰባሰብን፤ ተቃለድን፤ ተጫወትን፤ ሳቅን፤ በላን፤ ጠጣን፤ እየመሸ ሲሄድ ሥጋዊ ስሜት አሸነፈ:: መጋረጃ ተዘጋ ከሰው ዐይን በግድግዳ ተከለልሁ “ሰው እንዴት ሥጋዊ ስሜቱን ሊቋቋመው ይችላል?” የምትለዋ አመለካከቴ እንደ መፈክር በድርጊቴ ወደፊት እንድሰግር አደረገችኝ:: ጋለብሁ....ጋለብሁ... ሰይጣን በማላውቀው ሜዳ እንደ ፈረስ አስጋለበኝ.... አዲስ ደስታ በመሰለኝ ነገር ሁሉ ደረስሁ:: በአግራሞት ለእኔ ደስታ በሚመስለኝ ግን ወደ ቁልቁለት ወረድሁ....ወረድሁ... አዲስ ጥበብ እንዳገኘ ፈላስፋ አዲስ ቀለም እንዳገኘ ፀሐፊ... ባየሁት በነካሁት ነገር ሁሉ በደስታ ባሕር እየዋኘሁ ልጓሙን እንደፈታ ባዝራ ፈረስ ደስ ባለኝ እየረገጥሁ ልቤ መፈክሩን እየደጋገመ ልክ ነህ እያለኝ ሄድኩ ሄ....ድኩ... ሄ....ድ.....ኩ::

ሌሊት አንዳች ነገር ውስጤን አስበርግጎኝ አፈፍ ብዬ ከተኛሁበት ተነሣሁ:: ያለሁበትን አየሁ ስሜቴ ተደበላለቀ:: ከእንቅልፌ ብቻ ሳይሆን ከአዚማም ሕይወት የባነንኩ መሰለኝ:: ልጅነቴና የቀድሞ ሕይወቴ ፊቴ ላይ ተዘረጋ:: ድንጋጤ ከበበኝ:: ይህ ሰዓት አያቴ ከእንቅልፌ የምትቀሰቅሰኝ ሰዓት ነበር:: ልብሴን ለባብሼ በር ከፍቼ ወጥቼ ስሮጥ በባዶ እግሬ እንደሆንኩ ያስታወስኩት ሻፎ ድንጋይ እንቅፋት ሆኖ የእግሬን አውራ ጣት ሲያወልቀኝ ነው:: አመመኝ ደማ:: ባለቅስ ደስ ባለኝ ነበር ግን መሄድ አለብኝ:: በመንገድ ላይ የሰው ዘር አይታይም:: ጥርሴን ነክሼ አውራ ጣቴን መሬት እንዳይነካት ወደ ላይ አንከርፍፌ እግሬን ጎተት እያደረግሁ መንገዴን ቀጠልሁ:: አውራ ጣት ሲመታ ለምንድን ነው እንደዚህ ሰውነት ሁሉ የሚነዝረው ግን? ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ደረስኩ:: የቤተ ክርስቲያኑ መብራት ብቻ ነበር የሚታየኝ ትልቁ በር ስለተዘጋ እያነከስኩ ወደ ትንሹ በር ለመግባት ስሄድ...

“ወዴት ነው!?” አለኝ:: ጥበቃ ሠራተኛው ነው::

በጣቴ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ጠቆምኩት:: ትንፋሼ ይቆራረጣል::

“አይቻልም!”

“ለ...ምን?”

“አይቻልም:: በወረርሽኙ ምክንያት መግባት ተከልክሏል::... ምነው ባገር አልነበርክም እንዴ ጌታው?”

ምንም አልተናገርኩም:: ሽርተ...ት ብዬ በሩ ሥር ተቀመጥኩ:: እግሬ እየደማ ነው:: ሰውዬው ዐይኑን ሳይነቅል ያየኛል:: “አዬዬዬ... ባገር ብኖርማ...” ትንፋሼ ተቆራረጠ... ልቤ ተሰበረ:: ከንቱነቴ ተሰማኝ:: ውድቀቴን የምገልጽበት ቃል ሞቴን የምስልበት ቀለም አጠረኝ:: አያቴ በአካል ቆማ በትዝብት ዐይን የምትመለከተኝ መሰለኝ:: ከእፍረቴ የሚሸሽገኝ ነገር አጣሁ:: ፊቴን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዞሬ ማዬት አልቻልኩም:: አጥሩን ተደግፌ እግሬን ዘርግቼ በተስፋ መቁረጥ ስሜት ተቀምጬ አይኖቼን ጨፍኜ ውስጤን ሳዬው ቆሽሾ ለማየት የከፋ፣ ለማሽተት የከረፋ

ሆነብኝ። እንባዬ ፈሰሰ። ንጽሕናዬን አጣሁት። ልጅነቴ ሻከረብኝ። ያበላሸሁት እኔነቴ አስጠላኝ። ሐሳቤን ሰብሰብ ለማድረግ ሞክሬ የቅዳሴውን ድምፅ ለማዳመጥ ሞከርሁ።

"… ባርክ እግዚኦ ነገረ ዘእምወንጌለ ማቴዎስ ረድኡ ወሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ሎቱ ስብሐት ወትረ እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን።

የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፭ ከቍጥር ፩ እስከ ፲፫፦

በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች። ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ። ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤ ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ። ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ። እኩል ሌሊትም ሲሆን። እነሆ፥ ሙሽራው ይመጣል፥ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ውካታ ሆነ። በዚያን ጊዜ እነዚያ ቆነጃጅት ሁሉ ተነሡና መብራታቸውን አዘጋጁ። ሰነፎቹም ልባሞቹን። መብራታችን ሊጠፉብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው። ልባሞቹ ግን መልሰው። ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ወደሚሸጡት ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ አሉአቸው። ሊገዙም በሄዱ ጊዜ ሙሽራው መጣ፥ ተዘጋጅተው የነበሩትም ከእርሱ ጋር ወደ ሰርግ ገቡ፥ ደጁም ተዘጋ። በኋላም ደግሞ የቀሩቱ ቈነጃጅት መጡና። ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ፥ ክፈትልን አሉ። እርሱ ግን መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ አላውቃችሁም አለ። ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።

ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም አለ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ።…"

ልቤ ጸጸቱ በእጥፍ ጨመረ። ለእኔ ብቻ ተብሎ የተነገረ ወንጌል መሰለኝ። እውነት ነው… ዛሬ ስዘናጋ በስህተት ጎዳና ሳዘግም በሩ ቢዘጋብኝ ይሔ በር ነገ ይከፈታል። የመንግሥተ ሰማይ በር ግን ከተዘጋ እጣ ፋንታዬ ሲኦል ነው። ዛሬ ለንስሓ የማይመች ለኑዛዜ የማይሆን ጊዜ ላይ ልቤ ቢነቃም ይህ ክፉ ጊዜ እስኪያልፍ እጠብቀዋለሁ። አምላኬ እያዩኝ ነው። ውኃ እና ንስሓ የማያጸዳው ቆሻሻ የለም። እንደ ልጅነቴ የሥጋም የነፍስም ድንግልናዬን መመለስ ባልችል በኑዛዜ ፈጽሞ ንጹሕ መሆን እችላለሁ። እንደ ቀልድ በወሬ መካከል የተነገረች አንዲት ቃል ሕይወቴን ዘውራው ወደ ገደል ብትመራውም የሥጋ እስትንፋሴ እስካለች ድረስ መመለስና ወደ ቀናው ጎዳና ለመገስገስም ጊዜው አልረፈደም። ነገ ይሁን ዛሬ ሞታችን በማይታወቅበት ጊዜ በእሳት ጨዋታ ደቂቃ ለማይቆይ ደስታ መሳይ ሳቅ በጆርባው እልፍ ስፍር ጸጸትን ባዘለ ቡረቃ መሮጥ መጨረሻው የሞት ሞት ነው።

በልጅነቴ ከቤተ ክርስቲያን ጉያ ስር ተቀምጨ የማገኘውን ውስጣዊ ደስታ እና ሰላም የሚወዳደር ነገር እንደሌለ አይቻለሁ። ግን ተጎድቶ ከመማር፣ ከመስማትና ከመተግበር እጅጉን የተሻለ ነበር።


ቅዳሴው በተቀመጥኩበት አለቀ። ነጋ። የእግሬ ደም ደርቆ አውራ ጣቴ ማበጥ ጀምሯል። ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንደወትሮው አስቀዳሽ ምዕመናን አይታዩም። እንዴት ዓይነት ክፉ ዘመን ቢሆን ነው ሰውን ከፈጣሪው ደጅ እንዳይደርስ ያደረገው?… መቼ ነው የንስሓ አባቴ የሚዳስሱኝ?… ድጋሚ ማንባት ብፈልግም እንባዬ ደርቆ ነበር።

**እንደ ቀልድ በወሬ መካከል የተነገረች አንዲት ቃል ሕይወቴን ዘውራው ወደ ገደል ብትመራውም የሥጋ እስትንፋሴ እስካለች ድረስ መመለስና ወደ ቀናው ጎዳና ለመገስገስም ጊዜው አልረፈደም።**

# ዐቢይ ጾም በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት

## ከዓለም ማዕዘናት

*ዲ/ን ኀሊና በለጠ*




በዓለም ላይ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት አብዛኞቹ ምእመኖቻቸው ዐቢይ ጾምን እንዲጾሙ ያዛሉ። በተለይ የምሥራቅና የኦሪየንታል ኦርቶዶክሶች በጉጉት ከሚጠብቋቸው ጊዜያት አንዱ ይህ ወቅት ነው። የሶሪያ አብያተ ክርስቲያናት ይህን ታላቁን ጾም ‹‹Sawma Rabba›› ይሉታል - ጾመ ረቢ - ጾመ ኢየሱስ እንደ ማለት ነው። ጾሙን የሚቀበሉት ከበዓለ ትንሣኤው ከአምሳ ቀናት በፊት ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዐቢይ ጾም ሥርዓት ሳምንታቱ የየራሳቸው ስያሜ እንዳላቸው ኹሉ በሶሪያውያንና በሌሎችም የምሥራቅና የኦሪየንታል ኦርቶዶክሶች ዘንድ ስያሜያቸው የሚታወቁ ዕለታት አሉ። ከእነዚህም አንዱ ‹‹ንጹሕ ሰኞ›› (Clean Monday) ነው። ‹‹ንጹሕ ሰኞ›› የሚሉት ዐቢይ ጾምን የሚጀምሩበት ዕለተ ሰኞን ነው። እንደሚታወቀው የጾሙ የመጀመሪያ ዕለት ሰኞ ሲሆን፡ ጾም ከብዙ ኃጢአት የምንታቀብበት፣ በንስሐ ሳሙና የምንታጠብበትና የንጽሕና ምግባራትን የምንፈጽምበት በመሆኑ፡ ይህን ያመለክት ዘንድ የመጀመሪያውን የጾሙን መግቢያ ዕለት ንጹሕ ሰኞ ብለውታል።

በሶሪያ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የዐቢይ ጾምን ስድስተኛ ዓርብ ‹‹የአልዓዛር ዓርብ›› ይሏታል። ሰባተኛዋን ሰንበት ደግሞ ‹‹ሰንበተ ኦሻና›› (የሆሣዕና ሰንበት) ብለው ይጠሯታል። ምሴተ ሐሙስ፣ የስቅለቱ ዓርብና ቀዳም ስዑርም ከበዓለ ትንሣኤ በፊት የሚታሰቡ ዕለታት ናቸው። (የተጠቀምናቸው ምንጮች ሌሎቹ ዓርቦችና ሰንበታት ስያሜ ይኑራቸው፣ አይኑራቸው አይገልጹም)።

አንዳንዶች የምዕራባውያኑ አጠራር ተጽዕኖ አድርጎባቸው ‹‹ንጹሕ ሰኞ››ን፡ ‹‹የአመድ ሰኞ›› (Ash Monday) ብለው ይጠሩታል።

ምዕራባውያኑ፡ ዐቢይ ጾምን የሚጀምሩት እንደ ኦርቶዶክሳውያኑ በሰኞ ዕለት ሳይሆን በረቡዕ ነው። ስለዚህ የሚጀምሩበትን ረቡዕ ‹‹የአመድ ረቡዕ›› (Ash Wednesday) ብለው ይጠሩታል። ይህንንም ያሉበት ምክንያት ልክ እኛ በደመራ በዓል ጊዜ እንደምናደርገው በዕለቱ በግንባራቸው ላይ ከአመድ የመስቀል ምልክትን በማድረግ ስለሚያከብሩት ነው። ይህንንም የንስሐ ምልክት እንደ ሆነ ይገልጻሉ። አመዱም የሚገኘው ቀደም ባለው ዓመት በሚከበረው የሆሣዕና በዓል ላይ ከሚያቃጥሉት የዘንባባ ቅጠል ነው።



በዐቢይ ጾም ውስጥ ከሚታሰቡ በዓላት መካከልም በዓለ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌምን፣ በዓለ ቅዱስ ዮሴፍንና በዓለ ትስብእትን ያከብራሉ፡፡

በግብፅ የቅብጥ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ከዐቢይ ጾም በፊት ያሉት ሳምንታት ስያሜ ያላቸው ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ሰንበት የትኞቹ ምንባቦች እንደሚነበቡና ምን እንደሚታሰብባቸው እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር፡-

ጾሙ ከመጀመሩ በፊት ያለው ሰንበት የ‹‹ቅድመ ጾም›› ሰንበት ሲሆን የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፮፥፩-፲፰ ያለው ይነበብበታል፡፡ ሁለተኛው ሰንበት ‹‹ሀብተ ሰማያት›› የሚታሰቡበት ነው፡፡ ሦስተኛው እሑድ ‹‹የፈተና ሰንበት›› የሚባል ሲሆን፡ በአራተኛው የጠፋው ልጅ፣ በአምስተኛው ሳምራዊቷ ሴት፣ በስድስተኛው ሳምንት ሽባ የነበረው ሰው (The Paralized man - *መጻጉዕ*)፣ በሰባተኛው ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው፣ በስምንተኛው ሆሣዕና ይታሰባሉ፡፡

ከምሥራቅ ዐቢያተ ክርስቲያናት መካከል የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ለሰንበታቱ ስያሜዎች አሏት፡፡ የመጀመሪያውን ሰንበት ‹‹የኦርቶዶክሳዊነት ሰንበት›› የምትለው ሲሆን ኦርቶዶክሳውያን በቅዱሳት ሥዕላት ምክንያት የደረሰባቸውን መከራና በኋላም በነዮሐንስ ዘደማስቆ አማካኝነት ድል ማድረጋቸውን የምትዘክርበት ዕለት ነው፡፡

ከሰንበታቱ መካከል ሁለተኛውን ጎርጎርዮስ ፓላማስ የተባለው የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ሊቅ እንዲዘከርበት በስሙ የሰየመች ሲሆን ሦስተኛው ሰንበት ‹‹ቅዱስ መስቀልን የማክበር ሰንበት›› ይባላል፡፡ በዐራተኛው ዮሐንስ ዘሰዋስውን ስትዘክር እናታችን ቅድስት ማርያም ግብፃዊትም የምትዘከርበት ሰንበት አለ፡፡

*(ምንጭ፡- www.st-takla.org, www.goarch.org, www.oca.org, www.saintbarbarafw.org, www.syrianorthodoxchurch.org)*